__ማረሚያ__ በሽፋኑ ላይ ራእ. 20፥22
የሚለው ራዕ 22፥20 ተብሎ ይነበብ

# ማራናታ

ከመስፍን ተስፋዬ

ራዕይ አሳታሚ
1991 አዲስ አበባ

# ማራናታ

## መጀመሪያ በ1972 ዓ.ም. ታተመ።

ያሳታሚው መብት የተጠበቀ ነው።

ሁለተኛ እትም
3M RPRP10

ራዕይ አሳታሚ
የመ. ሣ. ቁ. 101539
አዲስ አበባ

## ማሳሰቢያ

«ማራናታ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የአማርኛ ትርጉሙ «ጌታችን ሆይ ና!» ማለት ነው (1ቆሮ. 16፥22፤ ራእ. 22፥20)

የጌታችንን ተመልሶ መምጣት ለሚፈልጉና ለሚጠባበቁ ክርስቲያኖች በመጠኑም ቢሆን ትምህርት ቢያገኙ መልካም ነው ብዩ በማለብ በ1972 ዓ.ም. ላይ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ለመድረስ ተነሣሣሁ፤ በዚያን ጊዜ መጽሐፉን አይተው እንዲታተም የገፋፉኝ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ። አሁን ደግሞ በዚህ ዘመን ስለ ክርስቶስ ተመልሶ መምጣት ብዙ ሰዎች ማወቅ ስለሚፈልጉ እንደገና ቢታተም ይጠቅማል ብዩ ለላስብኩ ራዕይ አሳታሚ ድርጅት እንደገና ለማሳተም በመፍቀዱ፥ ለራዕይ አሳታሚ ድርጅትም ከፍ ያለ ምስጋናዩን አቀርባለሁ፤ ድርጅቱንና አገልጋዮቹንም ጌታ ይባርካቸው።

ለጌታችን ተመልሶ መምጣት ሁላችንም የተዘጋጀን መሆን አለብን፤ ይሁን እንጂ እርሱ በምን ቀን ወይም በምን ሰዓት ተመልሶ እንደሚመጣ የሚያውቅ የለም (ማቴ. 24፥42)፤ «የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ስለሚመጣ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ» የተባልነውም በዚሁ ምክንያት ነው። ጌታ ኢየሱስ መቼ እንደሚመጣ የሚያውቅ እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው (ማቴ. 24፥36)

መንፈስ ቅዱስና ሙሽራይቱ «ና!» ይላሉ፤
የሚሰማም «ና!» ይበል፤

አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!
ማራናታ!

ወንጌላዊ መለፍን ተስፋዩ
የመ. ሳ. ቁጥር 3852
አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ


መቅድም ........................................ 3

ክፍል 1 ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል ........................................ 4

ክፍል 2 ስለ መነጠቅ ........................................ 7

ክፍል 3 የንጉሡ ሕልም ........................................ 10

ክፍል 4 የዳንኤል ሕልም ........................................ 13

ክፍል 5 እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት መቼ ነው? ........................................ 18

ክፍል 6 የቤተ ክርስቲያን ዘመን ........................................ 23

ክፍል 7 ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ ........................................ 30

ክፍል 8 አንድ ሽህ አስደሳች ዓመታት ........................................ 36

ክፍል 9 ወደፊት የሚመጡ ታላላቅ መሪዎች ........................................ 40

ክፍል 10 የግማሽ ሳምንት መከራ ........................................ 45

ክፍል 11 ወቅታዊ ሁኔታዎች ........................................ 53

ክፍል 12 አንዳንድ ነገሮች መሆን ጀምረዋል ........................................ 56

ችሎታችሁን ላኩ ........................................ 62

የጥያቄ መልሶች ........................................ 65

ዳግም ምፅአት ተጨማሪ ........................................ 67




## መቅድም

ስለ ዳግም ምፅዓት ማጥናት ከፍተኛ ፍላጎት ያደረብኝ በ1960 ዓ.ም. ለጥቂት ወጣቶች የዮሐንስን ራእይ ማታ ማታ ማስተማር ከጀመርሁ ወዲህ ነው። ከዚያ ወዲህ ብዙ የትንቢት መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ይህችን የትንቢት መግቢያ የሆነች ትንሽ መጽሐፍ ያዘጋጀሁት ከነዚሁ ካነበብኋቸው መጻሕፍት ነው። አብዛኛው አሳብ የተወሰደው «ኋት ኔክስት» ከሚለው አር ኢ ሃርላው ካዘጋጀው የመላላክ ትምህርት ነው።

ይህችን የትንቢት መግቢያ የሆነች መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ያነሳሳኝ «የነገርሁህን ቃል ሁሉ በመጽሐፍ ጻፍ» የሚለው ጥቅስ ነው <ኤር. 30:2>። ይዚህች መጽሐፍ አቀራረብ ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች ቅደም ተከተል ተራ በማስያዝ ትንቢትን በቀላል ሁኔታ ለማጥናት እንደሚመች ሆኖ ነው። ስለሆነም የተራቀቀ የድርሰት ይዞታ የለውም። የሥነ ጽሑፉን አቃቂር ከመመልከት ይልቅ ፍሬ አሳቡን የሚ ከታተል ብዙ ጥቅም ያገኝበታል ብዬ እገምታለሁ።

ማራናታ— ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!

የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ
መስፍን ተስፋዬ።

# ክፍል 1
## ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን ብዙ ሰዎች ጠልተውታል፤ ይሁን እንጂ ወዳጆችም ነበሩት። ጠላቶቹ ብዙ ጊዜ ሊገድሉት ሞክረው ነበር፤ በኋላም ተሳክቶላቸው በእንጨት ላይ ሰቅለው ገድለውታል። ወዳጆቹ ግን እስከ መጨረሻ ከእርሱ ጋር ጸንተዋል። ጌታ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ለወዳጆቹ ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር ነግሮአቸዋል። በዚህም ደቀ መዛሙርቱ አገልጋዮቹ ብቻ ሳይሆኑ ወዳጆቹም እንደሆኑ አረጋግጦአል (ዮሐ. 15፥15)።

አሳዳሪ አገልጋዮቹ ማድረግ የሚገባቸውን ይነግራቸዋል እንጂ የእርሱን ዓላማ ወይም እቅድ አይገልጥላቸውም። ጌታ ኢየሱስ ግን ለተከታዮቹ የእርሱንና የአባቱን ፈቃድ ገለጠላቸው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ፊት ብዙ ነገሮች እንደሚፈጸሙ ለወዳጆቹ ነገራቸው። ከነዚህም ነገሮች በጣም የሚያስደንቀው «እንደገና መጥቼ እወስዳችኋለሁ» የሚለው ቃል ነው (ዮሐ. 14፥3)፤ ስፍራ ሊያዘጋጅላቸው እንደሚሄድና ተመልሶም እንደሚመጣ ነገራቸው። እርሱ በሚኖርበት እንዲኖሩ ፈልጎ ነበር፤ እርሱ ያለው በመንግሥተ ሰማያት ነው፤ እኛም ከእርሱ ጋር በመንግሥተ ሰማያት እንድንሆን ይፈልጋል። እኛ በራሳችን ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ ስለማንችል እርሱ መጥቶ እንደሚወስደን ተስፋ ሰጥቶናል። «ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶናል» የሚለው ቃል ልናጠናው የሚገባን ታላቅ እውነት ነው።

ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ተስፋ የሰጠን ለምንድን ነው? አንደኛው ምክንያት ስለሚወደንና ከእርሱ ጋር እንድንሆን ስለሚ ፈልግ ነው፤ ሌላው ምክንያት እግዚአብሔር ዘላለም የሚነግሥ ንጉሥ ለእስራኤል እንደሚሰጥ አስቀድሞ ስለተናገረ ነው። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታ ተጠቅሰዋል። በዚህ ዓይነት ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ንጉሥ ይሆናል ማለት ነው (ኤር. 23፥5–6)። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የሚመለስበት ሦስተኛው ምክንያት የሚከተለው ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅ በመጀመሪያ ጊዜ መጥቶ አባቱ እንዲያደርግ የፈለገውን ሁሉ በትክክል አድርጎአል፤ እግዚአብሔርም በልጁ ደስ እንደተሰኘ ተናግሮአል (ማቴ. 3፥17፤ 17፥5)፤ ጌታ ኢየሱስን ያልተቀበሉ ሰዎች እንዲመቱት፣ እንዲተፉበት፣ እንዲገድሉት እግዚአብሔር ፈቅዶላቸው ነበር፤ በኋላ ግን እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው ወደ መንግሥተ ሰማያትም ወስዶ በራሱ



ዙፋን ላይ አስቀመጠው (ሐ.ሥ. 5፥30–31፤ ዕብ. 8፥1)። በዚህ ዓይነት ዛሬ በመንግሥተ ሰማያት ያሉ ሁሉ ክርስቶስን ያከብራሉ፤ በምድር ያለነውም እንዲሁ ልናደርግ ይገባናል። እግዚአብሔር ክርስቶስን እንደ መረጠውና እንደ ተቀበለው ሰዎች ሁሉ ማወቅ ይገባቸዋል።

ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ልጁን የዚህ ዓለም ንጉሥ አድርጎ እንደሚልክ ተስፋ ሰጥቶ ነበር፤ ምንም እንኳ ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ያሳታቸው ቢሆንም፥ የእነርሱ ዘር ሰይጣንን ድል እንደሚነሳ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶአል (ዘፍ. 3፥15)፤ በእርሱ ዘር አማካይነት ሕዝቦች ሁሉ እንደሚባረኩ ለአብርሃም እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶት ነበር (ዘፍ. 22፥16፤ ገላ. 3፥16)፤ የዳዊት ልጅ ወይም ዘር ለዘላለም እንደሚነግሥ እግዚአብሔር አስቀድሞ በተናገረ ጊዜ የክርስቶስን መምጣት አመልክቶአል (2ሳሙ. 7፥16)።

ክርስቶስ ከአሁን በፊት መጥቶአል፤ ነገር ግን በዓለም ላይ አልነገሠም። ሁለተኛ በሚመጣበት ጊዜ ግን በብሉይ ኪዳን የሚገኙት የተስፋ ቃሎች ሁሉ ይፈጸማሉ (መዝ. 2፥6–7)፤ የእግዚአብሔር አብና የራሱም የተስፋ ቃሎች እንዲፈጸሙ ክርስቶስ ራሱ ተመልሶ መምጣት ያስፈልገዋል፤ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛ ሙርቱን አነጋግሮአል፤ ብዙ ነገርም አስተምሮአቸዋል፤ በሌላ አነጋገር ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስን አይተውታል፤ ሲነጋገር ሰምተውታል፤ ሰውነቱንም በእጃቸው ዳስሰዋል። አንድ ቀን በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ከእነርሱ ጋር ሲነጋገር ሳለ በደመና ወደ ላይ ሲነጠቅ አይተውታል። በዚያን ጊዜ ሁለት መላእክት መጥተው ኢየሱስ ወደ ሰማይ እንደወጣ ነገሩአቸው፤ ወደ ሰማይ ሲወጣ ባዩትም ሁኔታ ተመልሶ እንደሚመጣ ነገሩአቸው (ሐ.ሥ. 1፥11)። ጌታ ኢየሱስ የሰጠን ተስፋ ወደ ምድር ተመልሶ እንደሚመጣ ብቻ ሳይሆን፥ በቶሎ እንደሚመጣም ጭምር ነው (ራእ. 22፥7፤ 12፥20)፤ ይህን የተስፋ ቃል ከተናገረ ወደ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ ሆኖታል፤ አንዳንድ ሰዎች መጠበቁ ስለ ሰለቻቸው በሉቃ. 12፥45 እንደተጠቀሰው አገልጋይ ወደ ዓለም ኃጢአት አዘንብለዋል። የቀሩት ደግሞ አንድ ስሕተት ይኖራል በማለት የጌታን ተስፋ ቃል በመሰላቸው ይተረጉማሉ፤ ነገር ግን ሦስት ነገሮችን ልንገነዘብ ይገባናል፤

አንደኛ እኛ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ከምንናፍቀው ይበልጥ ጌታ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ይፈልጋል።

ሁለተኛ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔር የጸጋ ዘመን ይፈጸማል። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ከክፉ ሥራቸው ተመልሰው እንዲድኑ ይፈልጋል (2ጴጥ. 3፥9)።

ሦስተኛ ጊዜው ለእኛ ረጅም ቢመስለንም ለእግዚአብሔር ግን አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው (2ጴጥ. 3፥8)።

የተወሰነው ቀን ሲቀርብ ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል። ጌታ ኢየሱስ የሚመጣውም በቶሎ ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመውጣቱ በፊት መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክልን ተስፋ ሰጥቶናል። «እኔ ብሄድ . . . አጽናኝ እልክላችኃለሁ» (ዮሐ. 16፥7)፤ «እኔ ብሄድ... ተመልሼ እመጣለሁ» (ዮሐ. 14፥3)፤ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ሲያስተምረንና ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች ሲያሳየን መጥቶአል (ዮሐ. 14፥28፤ 16፥13)፤ መንፈስ ቅዱስ ያስተማረው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል፤ ገና ወደፊት የሚሆኑትንም ነገሮች ነግሮናል።

ለምሳሌ፦

በ1ተሰ. 4 ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እንደሚመጣ እናገኛለን።

በዳን. 2 ስለ አራት ታላላቅ መንግሥታት እናገኛለን።

በዳን. 7ና8 ስለ አራቱ ታላላቅ መንግሥታት በሰፊው እንረዳለን፤ በተለይም በመጨረሻ ቀኖች ለሚመጣው ስለ አራተኛው መንግሥት እንረዳለን።

በማቴ. 24 ጌታ ከመምጣቱ በፊት ለሚሆኑት ነገሮች እንረዳለን። በራእ. 2ና3 ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ስላላት ሁኔታ እንረዳለን።

በራእ. 19 እስከ 21 ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ለሚሆኑት ነገሮች እንረዳለን።

በ2ተሰ. 2 ስለ ዓመፀኛው ሰው እንረዳለን።

በራእ. 13 ስለ አውሬውና ስለ ሐሰተኛው ነቢይ እንረዳለን።

በራእ. 6 እስከ 16 ስለ ታላቁ መከራ እንረዳለን።

በራእ. 17ና18 ስለ ታላቂቱ አመንዝራ ሴት ስለ ባቢሎን እንረዳለን።



# ክፍል 2
## ስለ መነጠቅ

ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ በሰጠን የተስፋ ቃሎች ተረድተናል። ከመምጣቱም በፊት ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራን መንፈስ ቅዱስን ልኮልናል (ዮሐ. 18፥13)፤ ሃያ ሰባቱን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዲጽፉ ሰዎችን የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ከነዚህ መጻሕፍት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተጻፉት በሐዋርያው ጳውሎስ ነው። በዚህ ክፍል ከሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ሁለቱን እንመለከታለን። እስቲ በመጀመሪያ በ1ተሰ. 4፥13–18 ያለውን አሳብ እንመልከት።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ጥቂት ክርስቲያኖች በመሞታቸው ያዘኑ ይመስላሉ (1ተሰ. 4፥13)፤ በተሰሎንቄ የነበሩ ክርስቲያኖች ብዙ ጠላቶች ስለነበሩአቸው ምናልባት አንዳንድ ክርስቲያኖች ሳይገደሉ አልቀሩም (ሐ.ሥ. 17፥5)፤ ጳውሎስ በተሰሎንቄ የቆየው ሦስት ሳምንት ብቻ ቢሆንም ስለ ጌታ መመለስ አስተምሮአቸው ነበር (1ተሰ. 1፥10፤ 2ተሰ. 2፥5)፤ ምንም እንኳ ጌታ ተመልሶ እንደሚመጣ ቢያምኑም፥ ወዳጆቻቸው ሲሞቱ በጣም አዝነው ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ «በእግዚአብሔር እንደማያምኑ ሰዎች አትዘኑ» ብሎ መከራቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ እንደ ሞተና ከሞት እንደተነሣ ያምናል። እንዲሁም ወደ ምድር እንደሚመለስና የሞቱትንም አማኞች ይዞ እንደሚመጣ ማመን አለብን (1ተሰ. 4፥14)፤ አማኝ ሲሞት አንቀላፋ የሚባለው ጌታ ሲመለስ ከሞት መነሣቱን ለማመልከት ነው፤ ለምሳሌ አልዓዛር ሞቶ ሳለ «አንቀላፍቶአል» ብሎ ጌታ ተናግሮ ነበር (ዮሐ. 11፥11–13)፤ አማኝ ጌታ እስኪመጣ ሥጋው በመቃብር ያርፋል እንጂ ሞቶ አይቀርም። ይህም ሲባል አያስብም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም አማኝ ሲሞት መንፈሱ ወዲያውኑ ወደ ክርስቶስ ስለሚሄድ እንደሚደሰት ሐዋርያው ጳውሎስ አመልክቶናል (ፊል. 1፥23)፤ እዚህም ላይ ክርስቶስ አማኞችን ይዞ እንደሚመጣ ስለሚናገር የሞቱት አማኞች ከክርስቶስ ጋር መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። ጳውሎስ ስለነዚህ ነገሮች ያስተማረው ጌታ አስተምሮት ስለነበር ነው (1ተሰ. 4፥15)። ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ያለውን አሳብ ከመጻፉ በፊት ሐዋርያት እንኳ ስለዚህ ነገር አያውቁም ነበር። በመጀመሪያ የምንማረው ነገር እኛ በሕይወት ያለነው የሞቱትን ቀድመን ወደ ሰማይ እንደማንሄድ ነው።

እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች ከነቅደም ተከተል ተራቸው እንደሚያውቅ እንገነዘባለን። እንዲሁም እግዚአብሔር በኃይሉ ሁሉን ነገር ይቆጣጠራል። እግዚአብሔር ወደ ፊት ለለሚሆኑት ነገሮች አስቀድሞ የነገረን ስለሚወደን ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ወጥቶአል። እርሱ ራሱ ተመልሶ ይመጣል። ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ሦስት ዓይነት ድምፅ ይሰማል፦ የትእዛዝ ድምፅ፣ የመላእክት አለቃ ድምፅና የእግዚአብሔር መለከት ድምፅ (1ተሰ. 4፥16)፤ ጌታ ኢየሱስ አማኞች ተነሥተው እንዲገናኙት ያዛቸዋል።

የመላእክት አለቃ ሚካኤል መሆኑን በይሁዳ 9 ላይ እንረዳለን። እርሱ ለእስራኤል ከተዋጉት መሳፍንት አንዱ ነበር (ዳን. 10፥13፣ 21፤ 12፥1፤ ራእ. 12፥7)፤ መለከት የሚነፋው ሰዎችን ወደ አንድ ስፍራ ለመሰብሰብ ሲፈልግ ነው (ዘኁ. 10፥3፤ 5፥6)፤ እያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ የጌታን ትእዛዝና የመለከቱን ድምፅ እንደሚሰማ የተረጋገጠ ነው። ጌታ ለወገኖቹ ሲመጣ የሞቱት ክርስቲያኖች ይነሣሉ፤ እኛ በሕይወት ያለነው የትእዛዝ ድምፅ ሰምተን ከእነርሱ ጋር እንነጠቃለን። ፊልጶስ በበረሃ የነበረውን ተግባር ባከናወነ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ነጠቀው (ሐ.ሥ. 8፥39)። እንዲሁም አማኞችን ሁሉ በአንድ አፍታ ነጥቆ ለመውሰድ የእግዚአብሔር ኃይል ታላቅ ነው። ስለዚህ፦

«ከሌሎች አማኞች ጋር በደመና

ጌታን ለመገናኘት በአየር እንነጠቃለን» (1ተሰ. 4፥15–17)። የምንነጠቀው በእግዚአብሔር ኃይል ስለሆነ ይህ ሁኔታ «መነጠቅ» ይባላል። ደግሞም እንደ ሄኖክ ስለምንለወጥ አንዳንድ ጊዜ «መለወጥ» ይባላል (ዕብ. 11፥5)። ጌታን በአየር ከተገናኘን በኋላ ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንሆናለን፤ በዚያን ጊዜ የጌታ ምኞትና ጸሎት ይፈጸማል (ዮሐ. 12፥26፤ 14፥3፤ 17፥24)፤ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ጸልዮልን ስለንበር አብረነው ስንሆን ደስ ይለዋል። እኛም ከእርሱ ጋር በመሆናችን ደስ ይለናል (ዮሐ. 17፥24)። በምናየው ጊዜ እርሱን እንመስላለን (1ዮሐ. 3፥2)፤ እርሱ ወደሚሄድበት እንሄዳለን። በሰማይ ቢሆን በሰማይ እንሆናለን። ወደ ምድር ሲመጣ አብረነው እንመጣለን። ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንሆናለን።

እንግዲህ በዚህ በአንደኛ ተሰሎንቄ በምዕራፍ አራት ውስጥ የተረዳነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለገዛ ወገኖቹ እንደሚመጣና እኛም ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንደምንኖር ነው። ይህ ተስፋ ዛሬ በሕይወታችን ምን ውጤት ይሰጠናል? ምናልባት ብዙ ችግር የደረሰብን እንኖራለን፤ ወይም የዚህ ዓለም ሰዎች የሚጠሉንና



የሚጎዱን እንኖራለን። ጌታ አንድ ቀን ስለሚመጣ ደስ ይበለን! (1ተሰ. 4፥16)።

አንዳንድ አማኞች ቸልተኞች ናቸው። ስለሆነም ከዓለም ሰዎች ጋር ወዳጅነት ይዘዋል። ይህም ሊሆን የቻለው ከልባቸው ለእግዚአብሔር ስለማይታዘዙ ነው (ሮሜ 12፥2)። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ከዓለም ርኩሰት ነጽተው የጌታን መምጣት በመጠባበቅ መኖር ይገባቸዋል (1ዮሐ. 3፥3፤ 1ጢሞ. 5፥22፤ ያዕ. 1፥27)።

ሌሎች ክርስቲያኖች ጌታን ይወዳሉ ሊያገለግሉትም ይሞክራሉ። እነርሱም ቢሆኑ በመከራና በችግር ላይ የሚገኙትን መርዳትና ጌታ በቶሎ እንደሚመጣ ማስተማር ይኖርባቸዋል።

አሁን ደግሞ በአንደኛ ቆሮንቶስ 15፥51–54 ያለውን ሐሳብ በጥንቃቄ እንመርምር። እዚህ ላይ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ በቅጽበት ዓይን እንደምንለወጥ እንረዳለን (1ቆሮ. 15፥51–52)፤ ይህ ታላቅ ለውጥ የሚሆነው የመጨረሻውን መለከት በምንሰማበት ጊዜና ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ነው። ጌታ ሲመጣ ይህ የአሁኑ ሰውነታችን ይለወጣል። እኛ ከመለወጣችን በፊት የሞቱት ክርስቲያኖች ይነሣሉ። ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ጋር እንነጠቃለን (1ተሰ. 4፥16–17)፤ ሞት ራሱ ይጠፋል (1ቆሮ. 15፥26–54)፤ መነጠቅ ለጌታ ኢየሱስም ሆነ ለአማኞች ደስ የሚያሰኝ ሁኔታ ነው። መቼ ነው የሚሆነው? ጌታስ የሚመጣው መቼ ነው? ጌታ የሚመጣበትን ጊዜ በትክክል አናውቅም። ሆኖም በቅርብ እንደሚሆን እናምናለን። ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን ከእግዚአብሔር አብ በቀር የሚያውቅ ማንም የለም (ማር. 13፥32)፤ የወደፊት ሁኔታዎችን ሁሉ የሚቆጣጠር እግዚአብሔር አብ እንደሆነ ጌታ ኢየሱስ ነግሮናል (ሐ.ሥ. 1፥7)፤ ይሁን እንጂ ከመነጠቅ በኋላ ለለሚሆኑት ነገሮች እግዚአብሔር ለእኛም ነግሮናል። እግዚአብሔር አሁን ዓለምን የሚያዘጋጀው ለነዚህ ወደ ፊት ለሚሆኑት ነገሮች እንደሆነ እናምናለን። አንዳንድ ሰዎች ጌታ የሚበጣበትን ቀን ለመወሰን ሞክረው ነበር። ነገር ግን አልሆነላቸውም። አብ የወሰነው ቀን እስኪደርስ በትዕግሥት መጠባበቅ ይኖርብናል።

ጌታ በሚመጣበት ጊዜ አማኞች ሁሉ ደስ ይላቸዋል። ሆኖም አንዳንዶቹ ከሌሎቹ ይልቅ ደስ ይላቸዋል። ከመነጠቅ በኋላ አንድ ታላቅ ነገር እንደሚፈጸም መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ይህም «የክርስቶስ የፍርድ ወንበር» የተባለው ነው (ሮሜ 14፥10–12፤ 2ቆሮ.

5፥8-10)። ሁላችንም በእግዚአብሔር ልጅ ፊት ስፍርድ እንቆማለን። በሥራ የደከሙና ጌታን ያስደሰቱ ክርስቲያኖች ታላቅ ሽልማት ይቀበላሉ። ይህን ያላደረጉ ክርስቲያኖች ግን የዘላለም ሕይወት ቢኖራቸውም ሽልማት አያገኙም (1ቆሮ. 3፥15)። ክርስቶስ ሲመጣ ወደ ሰማይ የሚሄዱትና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቆሙት እውነተኞች አማኞች ብቻ ናቸው። የማያምኑ ሰዎች የሚፈረድባቸው «በታላቁ ነጭ ዙፋን» ፊት ነው። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ምን ይሆናል? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አክሊልና ስለ ሽልማት ይናገራል። አንዳንዶቹ የጽድቅ አክሊል ይቀበላሉ (2ጢሞ. 4፥8)። ሌሎች የክብር አክሊል ይቀበላሉ (1ጴጥ. 5፥4)። አንዳንዶች በጌታ ፊት ቆመው ጌታ «መልካም አንተ በጎና ታማኝ ባሪያ» ሲላቸው ይሰማሉ (ማቴ. 25፥21-23)። እነዚህ አማኞች ይህን በሚሰሙበት ጊዜ እጅግ ደስ ይላቸዋል። እስቲ የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር እንመልከት። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ብቻ እኛን ኃጢአተኞችን ያድናል። ወደ ሰማይ ለመሄድ መልካም ሥራ አያስፈልገንም። ነገር ግን ከፍቅር የተነሣ ብናገለግለው እርሱ ብርታት ይሰጠናል። በሰማይም ታላቅ ሽልማት ይሰጠናል። ይህም ሽልማት ለዘላለም ከእኛ ጋር የሚኖር ነው። ስለዚህ ላሳየን ፍቅር ሁሉ ጌታን ማመስገን ይገባናል።

## ክፍል 3

## <u>የንጉሡ ሕልም።</u>

እስከ አሁን በአዲስ ኪዳን ያሉትን አንዳንድ የተስፋ ቃሎች ተመልክተናል። አሁን ደግሞ በብሉይ ኪዳን ያሉትን የተስፋ ቃሎች እንመለከታለን። ከኢሳይያስ እስከ ሚልኪያስ ያሉትን ዐሥራ ሰባት መጻሕፍት የጻፉት ነቢያት የሚባሉ ዐሥራ ስድስት የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። ከእነዚህም አንዱ ዳንኤል ነበር። ዳንኤል ነቢይ እንደነበረ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መስክሮለታል (ማቴ. 24፥15)። እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚሆኑትን ብዙ ነገሮች ለዳንኤል ነግሮት ነበር። ከእነዚያም ነገሮች አንዳንዶቹ ከዚህ በፊት ተፈጽመዋል። ሌሎቹ ደግሞ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ይፈጸማሉ። ዳንኤል እንደ ኖኅና እንደ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑ ተመስክሮለታል (ሕዝ. 14፥14-20)። ዳንኤል እግዚአብሔርን ማገልገል የጀመረው ገና ወጣት ሳለ ነው። የባቢሎን ንጉሥ ዳንኤልንና የእርሱን ሦስት ጓደኞች ምርኮኞች አድርጎ ወስዶአቸው ነበር። የባቢሎን ጠቢባን እንዲሆኑም ሊያስተምራቸው ፈልጎ ነበር። ከራሱ ማዕድ ምግብና መጠጥ



እንዲሰጣቸው አዞ ነበር። ነገር ግን ዳንኤል የእርሱን ምግብ ለመመገብ፥ ከመጠጡም ስመጠጣት አልፈለገም። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ስባቢሎን ሐሰተኞች አማልክት የተሠው ነበሩ። ዳንኤል ግን የእሥራኤልን አምላክ ይሖዋን ብቻ ማገለገል ፈለገ። የእርሱ ሦስት ጓደኞችም እንዲሁ አደረጉ። እግዚአብሔር ጥበብ ሰጥቶአቸው ስለነበር የባቢሎን ንጉሥ ከሁሉ የበስጠ ጠቢባን እንደሆኑ ተረዳ (ዳንኤል ምዕራፍ አንድን ያንብቡ።)

ዳንኤል እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ መጠቀም ጀመረ (ዳን. 2፥1-23)። አንድ ሌሊት የባቢሎን ንጉሥ ሕልም አስመ። ነገር ግን በማግሥቱ ሕልሙን ምን እንደሆነ ስማወቅ አልቻስም። የባቢሎን ጠቢባን የሐሰተኞች አማልክት ካህናት ነበሩ። እነርሱ ንጉሡ ያየውን ሕልም ሊናገሩ አልቻሉም። ዳንኤልና ጓደኞቹ ንጉሡ ያየውን ሕልም እንዲገልጥላቸው እግዚአብሔርን ለመኑ። እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ ዳንኤል ሕልሙን ከነትርጓሜው ማወቅ ቻለ። እግዚአብሔር ወደ ፊት ያለውን ዕቅድ ማወቅ ትፈልጋስህን? ዳንኤል እግዚአብሔርን ይወድ እንደ ነበርና ስጣዖት የተሠዋውን ምግብ አልበላም እንዳስ አስተውል። እርሱ ራሱን ከዓለም እንደለየ እኛም ከዓለም መለየት አስብን (ሮሜ 12፥2)። እርሱ ጥበብን ለማግኘት እንደጸለየ እኛም መጸስይ አለብን (ያዕ. 1፥5)። እግዚአብሔር የዳንኤልን ጸሎት ሰማ።

ዳንኤልም እግዚአብሔርን አመሰገነ (ዳን. 2፥30)። ጥበብ የምንፈልገው ለጥምክህት ከሆነ እግዚአብሔር ጥበብ አይሰጠንም (1ጴጥ. 5፥8)። እንግዲህ የእግዚአብሔርን የወደፊት ዕቅድ ለማወቅ ከፈለግን ዳንኤል እንዳደረገው ማድረግ አለብን። ታዲያ ንጉሡ በሕልሙ ያየው ምን ነበር? ንጉሡ ያየው ታላቅ የሰው ምስል ነበር። ራሱ ወርቅ፥ እጆቹና ግማሽ ሰውነቱ ብር፥ የቀረው ሰውነቱና ከቅልጥሞቹ ግማሹ ክፍል ነሐስ፥ የታችኛው ቅልጥምና እግሮቹ ብረትና ሸክላ ቅልቅል ነበሩ። በድንገት ድንጋይ በእግሮቹ ላይ በወደቀ ጊዜ ምስሉ በሙሉ ተሰባበረ። እነዚህ የተለያዩ ብረታ ብረቶች በሙሉ ደቅቀው እንደ አመድ ሆኑ። ያ ድንጋይ ግን ምድርን ሁሉ የሚሸፍን ታላቅ ድንጋይ ሆነ (ዳን. 2፥31-35)። የንጉሥ ናቡከደነፆር ሕልም ትርጉም ምን ነበር? የምስሉ አራት ክፍሎች የሚያመለክቱት በተከታታይነት የሚመጡትን አራት መንግሥታት እንደሆነ ዳንኤል ተናግሮአል። የወርቁ ራስ የናቡከደነፆር መንግሥት ምሳሌ ነው። ከእርሱ በኋላ ዓለምን የሚገዙ ሁስት ነገሥታት ይመጣሉ። ሆኖም እንደ መጀመሪያው ክብር አይኖራቸውም። አራተኛው መንግሥት

ለጥቂት ጊዜ ሁሉን ነገር እንደሚለባብር ብረት ብርቱ ነበረ። በኋላ ግን ብረቱ ከሸክላ ጋር ተደባለቀ። ይህም ደካማነቱን የሚያመለክት ነው። ይህ መንግሥት ይከፋፈላል፣ ግማሽ ጎኑም ደካማ ይሆናል (ዳን. 2፥38–43)፤ ድንጋዩ ምንድን ነው? (ዳን. 2፥44–45)፤ አራቱ ብረታ ብረቶች በተለያየ ጊዜ የሚመጡትን አራት መንግሥታት እንደሚያመለክቱ አይተናል። በመጨረሻ መንግሥታትን ሁሉ የሚደመስስ መንግሥት እግዚአብሔር ራሱ ያቋቁማል። ድንጋዩ የዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ነው። ያለ እጅ የተቆረጠው ድንጋይ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ነው።

መሢሕ ወይም ክርስቶስ የሚባል ንጉሥ እንደሚመጣ በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታ እንረዳለን። እርሱ ተራ ሰው አይደለም። እርሱ አምላክ ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የእርሱ መንግሥት ከሰዎች መንግሥታት ይበልጣል። እርሱ ለዘላለም ይነግሣል። እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር በሕልም ያሳየው አራት መንግሥታት እንደሚመጡ ነው፤ ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ንጉሥ የሆነው መሢሕ ይመጣል። ከአራቱ መንግሥታት የመጀመሪያው የባቢሎን መንግሥት ነው (ዳን. 2፥37–38)፤ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ሌሎች ሦስት መንግሥታት ይመጣሉ፤ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል። የናቡከደነፆርን ሕልም ስላወቀ ለዳንኤል ነገረው። እኛ ያለፈውን ነገር ከምናውቀው ይበልጥ እግዚአብሔር የወደፊቱን ያውቃል፤ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሁሉንም የሚቆጣጠር ነው። ናቡከደነፆርን ታላቅ ንጉሥ ያደረገው እርሱ ነው (ዳን. 2፥37)፤ ከናቡከደነፆር በኋላ ሌሎች ነገሥታትንም ያስነሣቸው እርሱ ነው (ዳን. 2፥39)። በመጨረሻም የራሱን ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዘላለም እንዲነግሥ ያደርገዋል (ዳን. 2፥44)።

የመጨረሻዎቹን ዐሥራ ለባት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከጻፉት ዐሥራ ስድስት ነቢያት አንዱ ዳንኤል ነበረ። ከነዚህ ነቢያት አብዛኞቹ ክርስቶስ ስለሚመጣበት ጊዜ አለቀድመው ተናግረዋል (ኢሳ. 40፥3፤ 42፥1፤ 53፥7–8፤ 61፥1)፤ ሁሉ ነገር እግዚአብሔር እንደተናገረው ተፈጽሞአል። ነገር ግን በነቢያት መጻሕፍት ከተነገሩት አንዳንዶቹ ገና አልተፈጸሙም። ጌታ ሲመለስ እንደሚፈጸሙ እናምናለን። ነቢያት ስለ ክርስቶስ መጀመሪያ መምጣት የተናገሩት እውነት ነበር። ስለዚህ ስለ ዳግም ምፅአቱ የተናገሩትም እውነት እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።



# ክፍል 4

## የዳንኤል ሕልም

ከትንቢተ ዳንኤል የመጀመሪያዎቹ ስድስት ምዕራፎች የሚናገሩት በዳንኤልና በጓደኞቹ እንዲሁም በንጉሥ ናቡከደነፆር ላይ የደረሰውን ነው። በምዕራፍ ሁለት ስለ ንጉሡ ሕልም አንብበናል። በምዕራፍ አራት ንጉሡ ሌላ ሕልም እንዳለመና ዳንኤል እንደተረጎመለት እናገኛለን። ንጉሡ እግዚአብሔር የሁሉ በላይ መሆኑን እስኪገነዘብ ድረስ ለጊዜው አእምሮውን አጥቶ ነበር። በምዕራፍ አምስት ከተማይቱንና መንግሥቱን የፋርስ ሰዎች እንደሚወስዱበት ዳንኤል ለንጉሥ ብልጣሶር በድፍረት ነገረው። በምዕራፍ ስድስት ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጠለ። ጠላቶቹ ወደ አናብስት ጉድጓድ ሲጥሉት እግዚአብሔር አዳነው።

ዳንኤል በእግዚአብሔር በመታመን ጸና። እግዚአብሔርም አከበረው። ወደፊት የሚሆነውንም ነገር በዝርዝር ነገረው። ዳንኤል ሕልም አልሞአል፣ ራእይም አይቶአል (7፥1፤ 8፥1)፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገር ተምሮአል (9፥2)፤ እግዚአብሔር ብዙ ነገር በየጊዜው ገልጦለታል (10፥1)።

በመጀመሪያ ስለ ዳንኤል ሕልም እንመለከታለን (7፥1–14)፤ ዳንኤል በሕልሙ አራት እንስሳት አየ። አንበሳ (7፥4)፥ ድብ (7፥5)፥ ነብር (7፥6)፥ ዐሥር ቀንዶች ያሉት ሌላ እንስሳ (7፥7)፥ አንድ ትንሽ ቀንድ ተገልጦ ከዐሥሩ ቀንዶች የሦስቱን ቦታ ሲይዝ አየ። ይህ የመጨረሻው እንስሳ ተደመሰሰ (7፥11)፥ የመጀመሪያዎቹ ሦስት እንስሳት ኃይላቸውን አጡ (7፥12)፥ የሰው ልጅ በሰዎችና በመንግሥታት ላይ ሥልጣን አገኘ (7፥13–14)።

እስቲ እነዚህን እንሰሳዎች እንመልከታቸው (7፥2–4)፤ ባሕሩ ዕረፍት ያጡትን የዚህ ዓለም ሰዎችና መንግሥታት ያመለክታል(ኢሳ. 57፥20)፤ ነፋሉ በሰዎች መካከል ሁከት የሚፈጥረውን የመናፍስት ኃይል ያመለክታል። አራት እንስሳት በየተራ ከባሕሩ ወጡ። የመጀመሪያው አንበሳ ይመስላል። አንበሳ ብርቱና ደፋር እንስሳ ነው (1ሳሙ. 1፥23)፤ አንዳንድ ጊዜ የእንስሳት ንጉሥ ይባላል። ይህ አንበሳ እንደ ንስር ይበራል። ነገር ግን ቆይቶ ክንፎቹ ተነቀሉ። የሰው ልብ የሚመስል አዲስ ልብም ተሰጠው። ይህ አንበሳ የሚያመለክተው ንጉሥ ናቡከደነፆርን ነበር። እርሱ የነገሥታት ንጉሥ ነበር (2፥37)፤

ነገር ግን በጣም ከማታበዩ የተነሳ ልቡ ተለወጠ (4፥18)፤ አእምሮውንም አጥቶ ለብዙ ጊዜ እንደ እንስሳ ኖረ፤ ጠጉሩና ጥፍሮቹ በጣም አደጉ (4፥33)፤ በመጨረሻ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ወደ አእምሮው ተመለሰ (4፥38)፤ ይህም ሁኔታ በ7+4 እንደ ተገለጠው አንበሳ ነው። ብዙ ሥጋ ይበላ የነበረው ሁለተኛው እንስሳ ድብ ይመስል ነበር (7፥5)፤ ሦስተኛው እንስሳ አራት ክንፎችና አራት ራሶች ያሉት ነብር ነበር። ይህም እንስሳ የመግዛት ሥልጣን ተሰጠው (7፥8)፤ ዳንኤል በመጀመሪያ የሕልሙን ትርጓሜ ለማወቅ አልቻለም። ስለዚህ ሌላ ሰው እንዲያስረዳው ጠየቀ (7፥16)፤ እነዚህ አራት እንስሳት የታላላቅ ነገሥታት ምሳሌዎች እንደሆኑ ተረዳ (7፥17)፤ በምዕራፍ ሁለት አራት መንግሥታት እንደሚነሡና ከነዚህም የመጀመሪያው ባቢሎን እንደሚሆን ተረድተናል። ብልጣሶር በባቢሎናውያን ወይም በከለዳውያን ላይ የነገሠው አያቱ ናቡከደነፆር በሞተ ጊዜ ነው። ብልጣሶር በሜዶን ንጉሥ በዳርዮስ ተገደለ (5፥30–31)፤ በዚህ ምክንያት የባቢሎን መንግሥት በሜዶን መንግሥት ተተካ። አራተኛውስ እንስሳ የምን ምሳሌ ነው? ይህ እንስሳ ዐሥር ቀንዶች ነበሩት። የትዕቢት ቃል የምትናገር አንድ ትንሽ ቀንድም ነበረችው (7+8)፤ እነዚህ ዐሥሩ አንድ ቀንዶች ዐሥሩ አንድ ነገሥታትን የሚያመለክቱ ናቸው (7+24)፤ ትንሽቱ ቀንድ በስተኋላ መጥታ ሦስት ነገሥታትን ድል አደረገች። ይህች ትንሽ ቀንድ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ተናገረች። የእግዚአብሔርንም ሰዎች ተቃወመች (7፥25)፤ ለጥቂት ጊዜ ሥርዓቶችን ሁሉ ለዋወጠች። በመጨረሻው ግን ተደመሰሰች (7፥11፤ 28)፤ እዚህ ቦታ ትንሽ ቀንድ የተባለው ንጉሥ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ ነው። ስለ እርሱ ወደ ፊት ብዙ እናጠናለን። በዳንኤል ምዕራፍ ሁለት የተጠቀሰው አራተኛው መንግሥት እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ እንደሚቀጥል ተመልክተናል። ድንጋዩ በምስሉ እግሮች ላይ በወደቀ ጊዜ ሁሉንም ነገር አፈራረሰው (2፥34–35)፤ በዳንኤል ምዕራፍ ሰባትም አራተኛው መንግሥትና ትንሹ ቀንድ ክርስቶስ እስኪመጣ ይቆያሉ (7፥21–22)፤ ዳንኤል የሰውን ልጅ የሚመስለውን ሰው አየሁ ይላል (7፥13–14)፤ ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ "የሰው ልጅ" የሚለውን ስም እንደተጠቀመበት እንረዳለን፤ የሰው ልጅ በሰማይ ደመና መጣ። በዘመናት የሸመገለው የዘላለም አምላክ ታላቅ ሥልጣን ሰጠው፤ ጌታ ኢየሱስ ይህን ሥልጣን ገና ድሮ ተቀብሎአል። በደመናም እመጣለሁ ብሎአል (ማቴ. 24፥30፤ 26፥64፤ 28፥18)፤ የሰው ልጅ መሳውን ዓሰም ይገዛል። የእግዚአብሔር ሰዎች የመንግሥቱ ተካፋዮች እንዲሆኑ ይፈቅዳል (ዳን. 7፥14፤ 18፥27፤ ራእ. 11፥14፤ 20፥6፤ 22+5)።



ዳንኤል ምዕራፍ ሰባትን ትተን ከመሄዳችን በፊት ስለ አራተኛው እንስሳ ልንገነዘብ የሚገባን ነገር አለ።

1/ አራተኛው እንስሳ ከሌሎቹ የተለየ ነው (7+7–19)፤ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የሚያውቁአቸው አውሬዎችን ይመስላሉ። አራተኛው ግን የተለመደ አውሬ አይደለም።

2/ የዚህ አስደናቂ አውሬ ትንሽ ቀንድ ትዕቢተኛ ነበረ። በእግዚአብሔር ላይ እንኳ ሳይቀር ከባድ የስድብ ቃል ይናገር ነበር (7፥8፤ 20+25)።

3/ እግዚአብሔርን ይሳደባል፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያሳድዳል (7፥21፥25)።

4/ ለትቂት ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ድል ነሣ «እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ» (7፥25)፥ ዳንኤል ሕልም ባለመ በሁለተኛው ዓመት ራእይ አየ (ምዕራፍ ስምንትን ይመልከቱ)። ዳንኤል በራእይ ሁለት እንስሳትን አየ። እነርሱም አውራ በግና አውራ ፍየል ነበሩ። የመጀመሪያው እንስሳ ማለትም አውራው በግ ሁለት ቀንዶች ነበሩት። አንደኛው ቀንድ ከሌላው ከፍ ያለ ነበር (8፥3)። በምዕራፍ ሰባት አራቱ እንስሳት የአራት መንግሥታት ምሳሌዎች እንደነበሩና ሁለተኛው እንስሳ የሜዶን መንግሥት ምሳሌ እንደነበረ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ሁለት ቀንዶች ያሉት አውራ በግ የሚዶንና የፋርስ ነገሥታት ምሳሌ እንደሆነ እናያለን (8፥20)። ታዲያ በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት ያለው ሁለተኛው እንስሳና በዳንኤል ምዕራፍ ስምንት ያለው አውራ በግ አንድ ናቸውን? የመጀመሪያው መንግሥት ባቢሎን የፋርስ ንጉሥ እስከመጣ ድረስ መቀጠሉን እናውቃለን (2ዜና 36፥20–23)፤ በዳንኤል 5፥31 የባቢሎን መንግሥት የሜዶኑ ዳርዮስ ከተማይቱንና ሕዝቡን እስከ ማረከ ድረስ እንደቀጠለ እንመለከታለን። በዳንኤል ምዕራፍ ስምንት ደግሞ ሁለቱ መንግሥታት ፋርስና ሜዶን በአንድነት ተጣምረው ታላቅ መንግሥት እንደሆኑ እናያለን። አንዱ ቀንዱ ከፍ ብሎ መታየቱ የፋርስን መንግሥት ሲያመለክት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ከሜዶን መንግሥት ይልቅ ስለ ፋርስ መንግሥት ብዙ እናገኛለን።

ዳንኤል በራእይ ያየው ሁለተኛው እንስሳ አውራ ፍየል ነበር (8፥5–8)፤ በዓይኖቹ መካከል አንድ ትልቅ ቀንድ ነበረው። በጉንም በቶሎ አሸነፈው፤ ፍየሉ ታላቅ ሆነ። ነገር ግን ቀንዱ በቶሎ ተሰበረ። በአንዱ

ቀንድ ቦታ አራት ትልልቅ ቀንዶች በቀሉ። ይህ ፍየል የግሪክ ንጉሥ ምሳሌ ነው (8፥21)፤ ስለ ግሪክ መንግሥት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ አናነብም። ሆኖም በሌሎች የጥንት መጻሕፍት ብዙ እናነባለን። እስክንድር የተባለ ታላቅ የግሪክ ንጉሥ የፋርስን ሰዎች አሸነፋቸው። ነገር ግን በጣም ጠጪ ስለነበረ ገና በወጣትነቱ ሞተ፤ መንግሥቱም ለአራት ተከፈለ። እያንዳንዱም ለብዙ ዘመናት የራሱ ንጉሥ ነበረው (6፥22)፤ በ7፥6 ላይ ነብሩ አራት ቀንዶች እንደነበሩት እናስታውሳለን።

ዳንኤል በራእይ ያየው አውራ ፍየል በመጀመሪያ ታላቅ ቀንድ ነበረው። ይህም ቀንድ የታላቁ እስክንድር ምሳሌ ነው። ይህ ቀንድ ሲሰበር ሌሎች አራት ቀንዶች በቀሉ። እነርሱም የእስክንድርን መንግሥት የተከፋፈሉት አራት ነገሥታት ናቸው። ከቀንዶቹ በአንዱ ላይ የበቀለው ትንሽ ቀንድ በጣም ታላቅ ሆነ (6፥9–12)፤ ይህ ትንሽ ቀንድ የሚያመለክተው ከአራቱ ነገሥታት በኋላ ከእስክንድር መንግሥት በጥቂቱ ክፍል ላይ ነግሥ የነበረውን ንጉሥ ነው። እርሱ መልካሚቱ ምድር የተባለችውን እስራኤልን ወጋት (ዳን. 8፥6፤ ሕዝ. 20፥6)፤ የይሖዋንም ቤተ መቅደስ አረከሰ። አይሁዳውያንም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳያቀርቡ ከለከለ። ይህን ሁሉ ያደረገው አንቲኦኩስ ኤፒፋኒስ የተባለ ንጉሥ እንደነበረ ከሌሎች የታሪክ መጻሕፍት እንረዳለን።

እስከ አሁን ስለ ሁለት ትንንሽ ቀንዶች አንብበናል። በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት ትንሹ ቀንድ የአራተኛው መንግሥት ንጉሥ ነበረ። እርሱ ክርስቶስ መጥቶ እስከሚያድናቸው ድረስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስጨንቃል። በዳንኤል ምዕራፍ ስምንት ያለው ትንሹ ቀንድ የታላቁ የግሪክ መንግሥት ክፍል ንጉሥ ነበር፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ሰዎችና የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ተቃውሞአል። ግሪክ ሦስተኛው መንግሥት ነበረ። በአራተኛው መንግሥት የተተካውም ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ነው። ስለዚህ እነዚህ ትንንሽ ቀንዶች በተለያየ ዘመን እንደኖሩ እናያለን። አንደኛው ክርስቶስ ከመምጣቱ ከብዙ ዘመን በፊት ነበረ። ሁለተኛው ደግሞ ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ይኖራል።

ራእዩ በመጨረሻው ጊዜ እንደሚሆን መልአኩ ለዳንኤል ነግሮታል (ዳን. 8፥17–19)፤ በዳንኤል 8፥9 የተጠቀሰው ትንሽ ቀንድ የአንቲኦኩስ ኢፒፋኒስ ምሳሌ እንደሆነ ተረድተናል። ይህ ክፉ ሰው የግሪክ መንግሥት ክፍል የነበረችውና ከእስራኤል በስተሰሜን የነበረችው የሶሪያ ንጉሥ ነበረ። ይህ ሰው እስራኤልን ድል ነስቶ ወደ ይሖዋ ቤተ መቅደስ ገብቶ ነበር። ለራሱ አማልክት በቤተ መቅደሱ



ውስጥ አሳማ በመሠዋቱ ቤተ መቅደሱን አረከሰ። ይህም አስጸያፊ ኃጢአት የተፈጸመው ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ቀናት ወይም ስድስት ዓመት ያህል ነበር (6፥14)። ከዚያም በኋላ አይሁዳውያን ቤተ መቅደስን እንዲይዙና እንዲጸልዩ እግዚአብሔር ኃይል ሰጣቸው።

የመጀመሪያዎቹ ሦስት መንግሥታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክ እንደነበሩ ከዳንኤል ተረድተናል። አራተኛው መንግሥት ግን እንደሆነ ብሉይ ኪዳን አይነግረንም። በአዲስ ኪዳን ግን ሮም በብዙ አገሮች ላይ እንደሠለጠነ እናያለን። እንዲያውም የሮማ ነገሥታት የነበሩ ሦስት ሰዎች ተጠቅሰዋል (ሉቃ. 2፥1፤ 3፥1፤ ሐ.ሥ. 11፥28) ከሌሎች የጥንት መጻሕፍት ሮም ግሪክን ድል እንደነሣ እንረዳለን።

| | ዳንኤል 2 | ዳንኤል 7 | ዳንኤል 6 |
|---|---|---|---|
| 1. | ወርቅ | አንበሳ | – |
| 2. | ብር | ድብ | አውራ በግ |
| 3. | ነሐስ | ነብር | አውራ ፍየል |
| 4. | ብረትና ሸክላ | ዐሥር ቀንዶች | – |
| | | ያሉት አውሬ | |

| የመንግሥቱ ስም፦ | የአንድ ንጉሥ ስም፦ |
|---|---|
| ባቢሎን | ናቡከደናጾር፣ ብልጣሶር |
| ሜዶንና ፋርስ | ዳርዮስ፣ ሳይረስ |
| ግሪክ | እስክንድር |
| ሮም | አውግስጦስ፣ጢባርዮስ፣ ቀላውዴዎስ |

እነዚህ አራት መንግሥታት ለብዙ ዘመን ቆይተዋል። ይህም ዘመን «የአረማውያን ዘመን» በመባል ይታወቃል። ከኤርምያስና ከዳንኤል ቀኖች እንሥቶ የአረማውያን ነገሥታት በእስራኤል ምድር ላይ ነግሠዋል። ባቢሎን እስራኤልን ድል እንደሚነሣና የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርም እየሩሳሌምን እንደሚያፈርስ ኤርምያስ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር (ኤር. 21፥7፤ 22፥26፤ 52፥4)፤ ዳንኤል ደግሞ ከባቢሎን ቀጥሎ ሦስት መንግሥታት እንደሚነሱና አራተኛው መንግሥት ክርስቶስ እስከሚመጣ እንደሚቆይ ተናግሮ ነበር፤ ጌታ ኢየሱስ ራሱ የአረማውያን ዘመን እስኪፈጸም አረማውያን ኢየሩሳሌምን በቁጥጥራቸው ሥር እንደሚያደርጉአት ተናግሮአል። ከዚያ በኋላ ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ክብር ይመለሳል (ሉቃ. 21፥24፥27)።

የአረማውያን ዘመን በቅርቡ ተፈጽሞአል። በ1667 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በሙሉ የአይሁዳውያን ሆናለች። በቅርቡ የእግዚአብሔር የጸጋ ዘመን ያከትማል። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር በኩል ያለነው ሰዎች ደስ ቢለንም፣ እግዚአብሔርን የሚከዱ ሰዎች ግን የጭንቅ ጊዜ ይጠብቃቸዋል።

# ክፍል 5
## እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት መቼ ነው?

እነዚህ ነገሮች ሁሉ መቼ እንደሚፈጸሙ በትክክል አናውቅም። ማንም ሰው ቀን ሊወስን ወይም ወደ ፊት ይሚሆኑትን ነገሮች በትክክል አውቃለሁ ሊል አይገባውም። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ የሚመጣበትን ቀን ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔር ልጅ እንኳ እንደማያውቅ ይናገራል። እግዚአብሔር አብ ይህን ሥልጣን ለራሱ ብቻ አድርጎታል (ሐ.ሥ. 1፥7)፤ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኋለኛው ዘመን የሚይስተምረውን በጥንቃቄ ማጥናት እንችላለን። ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣና የራሱን ወገኖች እንደሚወስድ ነግሮናል። የሞቱ ክርስቲያኖች ይነሣሉ። ጌታንም በደመና ለመገናኘት ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። ይህ የሚሆነው መቼ ነው?

በአረማውያን ዘመን አራት መንግሥታት ተከታትለው እንደሚነሡ እግዚአብሔር ለዳንኤል ነግሮታል። በአራተኛው መንግሥት መጨረሻ ላይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያስጨንቅ ጨካኝ ንጉሥ ይነሣል። እርሱም ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ይደመሰሳል። አይሁዳውያን እነማን ናቸው? ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ዘሩን እንደሚያበዛና እንደሚባርክ ለአብርሃም ቃል ገብቶለት ነበር (ዘፍ. 12፥2–3)፤ በኋላ እግዚአብሔር ዘሩ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንደሚሆን ለዳዊት ቃል ገባለት (2ሳሙ. 7፥11–16)፤ ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ረሱ። እርሱንም በደሉ። በመጨረሻም ይህ ነገድ በጣም ከፉ ስለነበረ እግዚአብሔር በብርቱ ቀጣው። የመጀመሪያው የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን እንዲያቃጥልና ሰዎቹንም ለሰባ ዓመት ምርኮኞች እንዲያደርጋቸው ፈቀደለት (ኤር. 25፥6–11)፤ አይሁዳውያን ንሰሐ በገቡ ጊዜ እግዚአብሔር የመጀመሪያው የፋርስ ንጉሥ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ እንዲፈቅድላቸው አደረገ (ዕዝ. 1፥1–3)፤ ኋላም መሢሑ መጣ። ነገር ግን አይሁዳውያን አልተቀበሉትም። ጌታ ኢየሱስን ገደሉት። እግዚአብሔርም እንደገና አገራቸውን ትተው እንዲሰደዱ አደረጋቸው።

ታዲያ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት የሰጠው የተስፋ ቃል እንዴት ሆነ? እግዚአብሔር ወገኖቹ ሲበድሉ ይቀጣቸዋል። ነገር ግን የተናገረውን የተስፋ ቃል አይለውጥም (ዕብ. 6፥13–14፥16)፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን ገና እንደሚባርካቸው አንጠራጠርም። የአረማውያን ዘመን ያከትማል። ጌታ ኢየሱስ መጥቶ በእስራኤልና በመላው ዓለም ላይ ይነግሣል። እግዚአብሔር የራሱን



ሕዝብ እስራኤልን ጠርቶአል። አይሁዳውያን በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ አስፈላጊ ናቸው። ጌታ ኢየሱስ የተወለደው የዳዊትና የአብርሃም ዘር ከሆነው ከእስራኤል ሕዝብ ነው (ማቴ. 1፥1፣ ሮሜ 9፥4–5)፤ በማቴዎስ 24 ጌታ የተናገረው አይሁዳውያን ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ነው። ከቤተ መቅደስ ወጥተው ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ደብረ ዘይት ሄዱ። እዚያ ሆነው የአይሁዳውያንን ቅድስት ከተማ ኢየሩሳሌምን ማየት ይችላሉ። እንዲሁም የማምለኪያ ስፍራቸው የነበረውን ቤተ መቅደስ ማየት ይችላሉ። ጌታ ቤተ መቅደሱ እንደሚፈርስ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው (ማቴ. 24፥2)፤ በዚያን ጊዜ ሁለት ጥያቄዎች አቀረቡለት።

1. ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ቤተ መቅደሱስ የሚፈርሰው መቼ ነው?
2. በዘመን መጨረሻ የመምጣትህ ምልክት ምንድን ነው?

ጌታ ለመጀመሪያው ጥያቄ የሰጠውን መልስ ሉቃስ በወንጌሉ አስፍሮታል (ሉቃ. 21፥20–24)፤ ከሌሎች ጥንታውያን ዩታሪክ መጻሕፍት እንደምንረዳው ጌታ ይህን መልስ ከሰጠ ከአርባ ዓመት በኋላ በ70 ዓ.ም. ላይ ቤተ መቅደሱ በሮማውያን እጅ ፈርሶአል። በዚህ በማቴዎስ ወንጌል ጌታ በዘመናት መጨረሻ ሲመጣ ምልክቶቹ ምን ምን እንደሆኑ ተናግሮአል።

የምጥ ጣር መጀመሪያ (ማቴ. 24፥4–8)፤
ታላቁ መከራ (ማቴ. 24፥9–22)፤
የሰው ልጅ መምጣት (ማቴ. 24፥23–31)።

## የምጥ ጣር መጀመሪያ (ማቴ. 24፥4–8)

እዚህ ላይ አራት ምልክቶች እናገኛለን፡– 1. «እኔ ክርስቶስ ነኝ» የሚሉ ብዙ ሰዎች ይነሳሉ። ብዙ ሰዎች እነዚህን ሐሰተኞች ነቢያት ይከተላሉ (ማቴ. 24፥5)፤ 2. ከዘመኑ ፍጻሜ በፊት ብዙ ጦርነቶች ይደረጋሉ (ማቴ. 24፥6)፤ 3. ብዙ ሰዎች ይራባሉ (ማቴ. 24፥7)፤ 4. በዓለም ላይ ብዙ የምድር መናወጥ ይሆናል። ሰዎችም ይሸበራሉ (ማቴ. 24፥7)፤ ጦርነት ረሀብ የምድር መናወጥ ምን ጊዜም አለ። ሰዎችን የሚያሳስቱ ሐሰተኞች ነቢያት ከድሮ ጀምሮ አሉ (ማቴ. 7፥15፣ ሐ.ሥ. 5፥36–37፣ 1ዮሐ. 2፥18፤ 4፥1)፤ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ጌታ ከመምጣቱ በፊት እየከፉ ይሄዳሉ። እዘውትረውም ይሆናሉ። ሆኖም እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።

## ታላቁ መከራ (ማቴ. 24፥9–22)

ይህ ጊዜ ለሰዎች ሁሉ በተለይም ለአይሁዳውያን በጣም አሠቃቂ ይሆናል።

1. በክርስቶስ የሚያምኑት የተጠሉ ይሆናሉ (ማቴ. 24፥9–10)።

2.ሐሰተኞች ነቢያት እውነት ያልሆነ ነገር ያስተምራሉ (ማቴ. 24፥11)።

3. በዓለም ላይ ብዙ ክፋት ከመኖሩ የተነሣ አንዳንድ አማኞች ለጌታ ያላቸውን ፍቅር ይተዋሉ (ማቴ. 24፥12)፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል (ማቴ. 24፥13)።

4. ብዙዎች ጌታን ከመውደዳቸው የተነሣ የምሥራቹን ቃል ለዓለም ያደርሳሉ (ማቴ. 24፥14)።

5. በእስራኤል ያሉ አይሁዳውያን መሸሽ ይኖርባቸዋል (ማቴ. 24፥15–20)፤ በተቻለ ፍጥነት አገራቸውን ለቀው እንዲወጡ ጌታ መከሮአቸዋል። ትርፍ ልብስ ለመውሰድ እንኳ እንዳይዘገዩ አሳስቦአቸዋል። ነፍሰ ጡሮች የበለ ችግር ይገጥማቸዋል። ሽሽታቸው በክረምት ወይም በሰንበት ቀን ከሆነ አሠቃቂ ሁኔታ ይደርስባቸዋል።

ጌታ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ዓይነተኛ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። ይህንንም ምልክት በሚያዩበት ጊዜ በተቻለ ፍጥነት እንዲሸሹ አሳስቦአቸው ነበር። ይህም ምልክት የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰ ስፍራ መቆሙ ነበር (ማቴ. 24፥15፤ ዳን. 7፥29፤ 11፥31፤ 12፥11)፤ የተቀደሰው ስፍራ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው። አይሁዳውያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳያቀርቡ ትንሹ ቀንድ እንደሚከለክል ዳንኤል ተናግሮ ነበር (ዳን. 8፥11)፤ አንቲአከስ ኤፒፋኒስ የተባለ የግሪክ ንጉሥ ይህን ማድረጉ ይታወሳል። ሆኖም እርሱ ወደ ፊት ስሚመጣው ታላቅ መሪ ምሳሌ ነበር። ይህ ታላቅ መሪ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ታላቅ መሠዊያ ያረክሳል። አይሁዳውያን ለይሖዋ መሥዋዕት እንዳያቀርቡም ይከለክላል። ከዚያ በኋላ ይህ ታላቅ መሪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማሳደድ ይጀምራል። በዚህ ዓይነት ታላቁ መከራ ይጀምራል። እንግዲህ ታላቁ መከራ የሚጀመረው በጥፋት ርኩሰት ነው። በሰዎች ላይ ከቶ ደርሶ የማያውቅ ከባድ የመከራ ጊዜ ይሆናል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችም ይሞታሉ (ማቴ. 24፥21)፤ እግዚአብሔር በምሕረቱ ጊዜውን ባያሳጥር ብዙ ሰዎች ይሞታሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር በታላቁ መከራ ሰው ሁሉ እንዲያልቅ አይፈቅድም። እርሱ የመረጣቸው ሰዎች ይድናሉ (ማቴ. 24፥22)፤ ታላቁ የመከራ ዘመን የሚቆየው ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ መሆኑን ከማቴዎስ 24 እንረዳለን።



## የሰው ልጅ መምጣት

ክርስቶስ ሲመጣ ሰው ሁሉ ያየዋል (ማቴ. 24፥23–31)፤ እርሱ ከመምጣቱ በፊት «እኔ ክርስቶስ ነኝ» የሚሉ ብዙ ሰዎች ይነሣሉ። ከእነርሱም ብዙዎቹ ብዙ ምልክት እያደረጉ ብዙ ሰዎችን ያስታሉ። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እነዚህን ሰዎች እንዳይከተሉ አስጠንቅቆአል። ጌታ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ እዚህ መሆኑን ሰው ሁሉ ያውቃል። ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትም ይጨልማሉ። ጌታም እንደ ታላቅ የመብረቅ ብልጭታ ሰማይን ሞልቶ ይመጣል። በኃይልና በክብር በደመና ሆኖ ይመጣል። መላእክትም በምድር ላይ የተበተኑትን የእርሱን ወገኖች ይሰበስባሉ።

ጌታ የሚመጣው በድንገት መሆኑን ተረድተናል። እርሱ በሚመጣበት ጊዜ የዓለም ሰዎች ያለቅሳሉ (ማቴ. 24፥30፤ ራእ. 1፥7)፤ አማኞች ግን ጌታን ሲያዩ ደስ ይላቸዋል፤ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ስለሚሆኑት አንዳንድ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንረዳ እንችላለን። ሆኖም አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ ቢያዩ እንኳ አያምኑም ወይም አይዘጋጁም፤ ስለዚህ ጌታ ሌላ የማስጠንቀቂያ ትምህርት ሰጥቶናል (ማቴ. 24፥32–33)፤ በእስራኤል በጋ እንደቀረበ የሚታወቀው ዛፎች ቅጠሎቻቸውን ሲያራግፉ ነው፤ በተለይ የበለስ ዛፍ ቅጠሉን ሲያረግፍ በጋ መድረሱ ይታወቃል፤ እኛም የክርስቶስ መምጫ እንደቀረበ ከስጠን ምልክቶች መረዳት አለብን። ጌታ ኢየሱስ ስለ አንድ የበለስ ዛፍ የተናገረው ታሪክ አለ (ሉቃ. 13፥6–9)፤ የበለሱ ዛፍ ፍሬ አልሰጥም ቢል የአትክልቱ ጌታ ለአትክልተኛው ይህን በለስ ቁረጠው ብሎ አዘዘው። አትክልተኛው እስቲ አንድ ዓመት እንሞክረው ብሎ ጌታውን አስፈቀደ። ይህ ታሪክ የእስራኤል ምሳሌ ነው። ከኃጢአታቸው ባይመለሱ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚቀጣ እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር። በእርግጥም ከኃጢአታቸው ስላልተመለሱ በ70 ዓ.ም. እግዚአብሔር ሰርማውያን አሳልፎ ሰጣቸው። ጌታ ኢየሱስ ይህንኑ ታሪክ በማቴ. 21፥19 ተናግሮታል። በማቴ. 24፥32 በጋ ከመምጣቱ በፊት የበለስ ዛፍ እንደምትለመልም ተናግሮአል። ጌታ ከመመለሱ በፊት አይሁዳውያን በኢየሩሳሌም እንደሚኖሩ ማቴ. 24 ያስረዳናል። አይሁዳውያን በቤተ መቅደሳቸው ለይሖዋ መሥዋዕት ያቀርባሉ። አንድ ክፉ ሰው መሥዋዕት እንዳያቀርቡ እንደሚከለክላቸው ጌታ ኢየሱስ አስተምሮአል። ከዚያ በኋላ በፍጥነት ከኢየሩሳሌም ወጥተው መሸሽ ይኖርባቸዋል (ማቴ. 24፥15–16)፤ አይሁዳውያን በ70 ዓ.ም. ከአገራቸው ተባርረው ነበር። እስከ 1948 ዓ.ም. ድረስ አገራቸው በእነርሱ እጅ አልነበረም። ምንም

እንኳ ኢየሩሳሌምን በ1967 ዓ.ም. በቁጥጥራቸው ሥር ቢያውሉአትም ቤተ መቅደሳቸውን መልሰው ለመሥራት አልቻሉም። ሆኖም ይህ ሁሉ ለውጥ በእስራኤል በመሆኑ እግዚአብሔር ለልጁ መመለስ ዓለምን እንደሚያዘጋጅ እንገነዘባለን።

በማቴዎስ 24 ጌታ ኢየሱስ ስለ አይሁዳውያንና ስለ አረማውያን ብዙ ነገር ገልጦልናል። ስለ ቤተ ክርስቲያንስ ምን ተነግሮአል? ጌታ ኢየሱስ በድምፅ እንደሚመጣና የሞቱት ክርስቲያኖች አስቀድመው እንደሚነሡ ተረድተናል። ጌታ ኢየሱስ እርሱን ወደምናገኝበት ወደ ሰማይ በደመና ይወስደናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን (1ተሰ. 4፥17)፤ በማቴ. 24 ያለው ሁኔታ ለየት ያለ ነው። ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትም ይጨልማሉ። ጌታ እንደ ታላቅ መብረቅ ብልጭታ በሰማይ ላይ ይታያል። በኃይልና በክብርም ይመጣል። እንግዲህ ማቴ. 24 እና 1ተሰ. 4 ጌታ ስለሚመጣበት ጊዜ ያስተምራሉ። ነገር ግን እያንዳንዳቸው የሚናገሩት ስለተለያየ ጊዜ ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚሆነው ክርስቶስ በኃይልና በክብር ከምምጣቱ በፊት ነው።

## ዐሥሩ ልጃገረዶች

ጌታ ኢየሱስ ስለ ዐሥር ልጃገረዶች አንድ አስደናቂ ታሪክ ተናግሮ ነበር (ማቴ. 24፥1–11)፤ ከሠርግ የሚመለሰውን ሙሽራ ይጠባበቁ የነበሩ ዐሥር ልጃገረዶች ሙሽራው በመዘግየቱ እንቅልፍ ይዞአቸው ተኙ። ሙሽራው በተመለሰ ጊዜ ሊቀበሉት የተዘጋጁት አምስቱ ብቻ እንደሆኑ አየ። ጌታ ኢየሱስ ይህን ታሪክ የተናገረው የሚመጣበትን ቀን ስለማናውቅ ተዘጋጅተን እንድንጠብቀው ነው። ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ እንደሚመለስ እንኳ አያውቁም። ሌሎቹ ደግሞ በቶሎ እንደሚመለስ አያስተውሉም፤ እኛ ጌታ ተመልሶ እንደሚመጣ እናውቃለን። ነገር ግን ጊዜውን በትክክል አናውቅም። በዓለም ላይ ብዙ ነገሮች ሲደረጉ ስለምናይ ጌታ ሲመጣ እንዳናፍር መዘጋጀት ይኖርብናል (ማቴ. 24፥36–51)።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ሦስት አገልጋዮች የሚናገር ሌላ ታሪክ ተናግሮአል። አሳዳሪያቸው ለእያንዳንዳቸው ገንዘብ ሰጣቸውና ወደ ሩቅ አገር ሄደ። እዚያም ብዙ ጊዜ ቆየ። በተመለሰ ጊዜ ከአገልጋዮቹ ሁለቱ በደንብ ስላገለገሉት ደስ አለው። ጌታ ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ እያንዳንዳችንን ጠርቶ ምን እንዳደረግን ይጠይቀናል። በታማኝነት ያገለገሉት ካሉ ያመሰግናቸዋል፤ ይሸልማቸዋልም። የክርስቶስ የፍርድ ወንበር ከመነጠቅ በኋላ አማኞች ብቻ ባሉበት ይሆናል። ጌታ ኢየሱስ



በኃይልና በክብር ከተመለሰ በኋላ በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ለፍርድ በፊቱ ይሰበሰባሉ (ማቴ. 25፥31–46)፤ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ ጌታም ሰዎችን በሁለት ይመድባቸዋል። በበጎች የተመሰሉት አማኞች ከጌታ በስተቀኝ ይቆማሉ። ሌሎቹ ከጌታ በስተግራ ይቆማሉ። በቀኝ ያሉት በታላቁ መከራ ዘመን ለእርሱ ሕዝብ ለእስራኤል ደግነት በማሳየታቸው ይመሰገናሉ። ስለዚህ ወደ ክርስቶስ መንግሥት ገብተው በዚህ ዓለም ይኖራሉ። በግራ በኩል ያሉት በታላቁ መከራ ዘመን እስራኤልን ባለመርዳታቸው ለሰይጣን ወደተዘጋጀው ስፍራ ይሄዳሉ።

# ክፍል 6

## የቤተ ክርስቲያን ዘመን

ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣና ቤተ ክርስቲያኑን ከዚህ ዓለም እንደሚወስድ ከዚህ በፊት ተመልክተናል። እንዲሁም ታላላቅ የትንቢት ምዕራፎችንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልክተናል (ዮሐ. 14፤ 1ተሰ. 4፤ ዳን. 2፤ 7፤ 8፤ ማቴ. 24፤ 25)፤ አሁን ደግሞ ከራእይ ምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ያለውን አሳብ እንመለከትና ስለ ቤተክርስቲያን ምን ስመማር እንደምንችል እንረዳ።

እስቲ በመጀመሪያ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች እንወቅ። በኤፌሶን መልእክት ቤተክርስቲያን በአካል ተመስላ እናገኛለን። በዚህ ዓይነት የአካሉ ክፍሎች ምዕመናን ናቸው (ኤፌ. 4፥15፤ 5፥30)፤ ቤተክርስቲያን በሙሽሪት ወይም በሚስት ትመሰላለች። በዚህ ዓይነት ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ይወዳታል፤ ይንከባከባታልም (ኤፌ. 5፥25–27)፤ ምንም እንኳ በክርስቶስ የሚያምኑ አይሁዳውያን የክርስቶስ አካል የሆነችው የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ለመሆን ቢችሉም ቤተክርስቲያን ከእስራኤል የተለየች ናት (1ቆሮ. 10፥32)፤ ቤተክርስቲያን የምታቅፈው በአሁኑ ዘመን በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ነው። ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የተለየ ስፍራ እንዳላት የተረጋገጠ ነው።

ቤተክርስቲያን የተጀመረችው መቼ ነው? ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደሆነችና እውነተኞች አማኞች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አባሎች እንደሆኑ ተመልክተናል። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመሄዱ በፊት ከጥቂት ቀኖች በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁ ለደቀ መዛሙርቱ ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር። በዚህም ተስፋ መሠረት

በጰንጠቆስጤ ቀን በመንፈስ ከዱስ ተጠመቁ (ሐ.ሥ. 1፥5፤ 2፥4)፤ መንፈስ ቅዱስ በብዙ አማኞች ላይ ስስወረደ እነዚያን ሰዎች ሁሉ አንድ አካል ወይም ቤተክርስቲያን አደረጋቸው። ስስዚህ ቤተክርስቲያን የተጀመረችው በጰንጠቆስጤ ቀን ነው። ዛሬ በክርስቶስ የሚያምኑት የሚጨመሩት ወደዚያው ወደ አንዱ አካል ነው (1ቆሮ. 12፥13)፤ ብዙ አማኞች ሞተዋል። ብዙዎቹም በእምነታቸው ምክንያት ተገድስዋል። ቤተክርስቲያን ግን አሁንም ሕያው ሆና ትሠራስች። ክርስቶስ አማኞችን ወደ ሰማይ ስመውሰድ እስከሚመጣበት እስከ መነጠቅ ድረስ እዚሁ ትሆናስች። ከጰንጠቆስጤ አንስቶ እስከ መነጠቅ ያስው ጊዜ የቤተክርስቲያን ዘመን ይባላል። የሐዋርያት ሥራ የተባስው መጽሐፍ የሚነግረን ቤተክርስቲያን እንዴት አንደ ተጀመረችና እንደተስፋፋች ቢሆን፥ የዮሐንስ ራእይ የተባስው መጽሐፍ ደግሞ ስስ ጌታ መምጣት ይነግረናል። በሐዋርያት ሥራና በራእይ መካከል 21 መልእክቶች አሉ። እነርሱ የተጻፉት በጳውሎስ፥ በጴጥሮስ፥ በያዕቆብ፥ በዮሐንስና በይሁዳ ነው። እነዚህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መልእክቶቹን ስአብያተ ክርስቲያናትና ስግስሰቦች እንዲጽፉ የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። አብያተ ክርስቲያናትም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በመልእክቶቹ አማካይነት እግዚአብሔር መመሪያ ሰጥቶአል። በቤተክርስቲያን ዘመን ምን ማድረግ እንደሚገባን የሚያሳየን አዲስ ኪዳን የተባስው መጽሐፍ ነው። በቀድሞ ጊዜ በገላትያ፥ በቆሮንቶስ፥ በፊልጵስዩስና በቆላስያስ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ታላላቅ ችግሮች ነበሩአቸው። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ችግሮቻቸውን እንዴት ማቃስል እንደሚገባቸው ነገራቸው። ከዚያን ወዲህ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትም ብዙ ችግር ገጥሞአቸዋል፥ አሁንም እየተጠማቸው ነው። ስስዚህ የአዲስ ኪዳንን መመሪያ እየተከተሉ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባቸዋል። አሁንም ቢሆን ክርስቶስ፥ አካሉ የሆነችው የቤተክርስቲያን ራስ ነው። እንዲሁም የእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባሎች ክርስቶስን የሚወዱና የሚታዘዙ ከሆነ ክርስቶስ የዚያ ቤተክርስቲያን ራስ ይሆናል። ስስዚህ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የአዲስ ኪዳንን ትምህርት መከተልና የክርስቶስንም ትእዛዝ መፈጸም ይኖርበታል። የእያንዳንዱን ሰው ሰውነት የሚመራውና የሚቆጣጠረው ራስ እንደሆነ ሁሉ፥ ክርስቶስ አካሉ የሆነችው የቤተክርስቲያን ራስ ነው (ኤፌ. 1፥22-23፤ 4፥15)።

በራእይ ምዕራፍ 1 ክርስቶስ የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪ በመሆን ቆሞ እናየዋስን (ራእ. 1፥10-20)፤ ሐዋርያው ዮሐንስ ሰው የሚመስሰውን፥ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን አምላክ አየ (ራእ. 1፥13፤ 1፥17፤ ኢሳ. 44፥6)፤ እርሱ ሞቶ ነበር፤ ነገር ግን ከሞት ተነሥቶአል (ራእ. 1፥18)፤ ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ልጅ የተባሰው ከሞት የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ነው። ዮሐንስ ያየው የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ በሆኑት በሰባቱ መቅረዞች መካከል እንደቆመ ነው (ራእ. 1፥20)፤ ጌታ በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት ይዞ ነበር። እነዚህ ከዋክብት በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ወይም መልእክተኞች የሚመስሉ ናቸው። ከእነዚህ ጥቅሶች የምንረዳው የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተቆጣጣሪ ክርስቶስ እንደሆነ ነው። እነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የት ነበሩ? (ራእ. 1፥4፤ 11)።



የእስያ ክፍስ ሀገር ከሮማውያን ግዛት አንዱ ክፍል ነበር። ዛሬ ቱርክ የሚባሰው አገር ነው። እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የተስያየ ችግር ስስነበረው ጌታ ስእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን መልእክት አስተላልፎአል። ምንም እንኳ መልእክቱ የተላከው ስእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን መሪ ቢሆንም መልእክቱ የተላከው ስአማኞች ሁሉ ነበር። እነዚህ መልእክቶች በዚህ ዘመን ስምንገኝ አማኞችም ጭምር ይጠቅማሉ። ጌታ በኤፌሶን ቤተክርሰቲያን ያየውን ሁኔታ ዛሬም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሊያይ ይችላል። ስስሆነም በኤፌሶን ቤተክርስቲያን የሰጠውን መአልክት ስእነርሱም ይሰጣቸዋል። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሰምርኔስ እንደ ፊላደልፍያ እንደ ሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ተገኝተው ይሆናል። እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት መንፈሰ ቅዱስ የሚናገራቸውን መስማት አስባቸው። እነዚህ በራእይ ምዕራፍ ሁስትና ምዕራፍ ሦስት የሠፈሩት መልእክቶች ዛሬ ስእኛ ይጠቅማሉ። በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመን እንኳ እንደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያሉ ሌሎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያሉ አማኞች የመጀመሪያ ፍቅራቸውን ጥስዋል። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጌታን በማመስገንና ስስ ክርስቶስ በመመስከር ትተጋ ነበር (ሐ.ሥ. 2፥46-47፤ 8፥4)፥ ቆይቶ ግን አማኞች እርስ በርሳቸው መጨቃጨቅና መጣላት ጀመሩ (1ቆሮ. 1፥11፤ ፊል. 4፥2-3)፤ ድሮ ስጌታ ኢየሱስ የነበራቸው ፍቅር አሁን ጠፋ። በኋላም አብያተ ክርስቲያናት በታላቅ መከራ ውስጥ አስፉ። ብዙ አማኞች ታሰሩ። ብዙዎችም ተገደሉ። ነገር ግን በሰምርኔስ እንዳሉ አማኞች ብዙዎቹ በእምነታቸው ጸኑ (ራእ. 2፥8-11)፤ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ስስ ደረሰው ነገር ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልንረዳ እንችላስን።

በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰባት ክፍል ጊዜዎች አሉ። በእያንዳንዱ ክፍስ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በራእይ ምዕራፍ ሁስትና

ምዕራፍ ሦስት ላይ እንደተጠቀሱት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ሆኖ እናገኘዋለን። የመጀመሪያው መልእክት የተላከው ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ነበር (ራእ. 2፥1–7)፤ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መልካም ነገር አይቶአል (ራእ. 2፥2–3)፤ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በዚህ ምክንያት በሐሰት «ሐዋርያት» ነን የሚሉትን ለመለየት ይችሉ ነበር። የኒቆላውያንንም ሥራ ልክ ጌታ እንደሚጠላው ዓይነት ይጠሉ ነበር (ራእ. 2፥6)፤ ይህን ሁሉ ማድረጋቸው መልካም ሲሆን፥ ጌታን በመጀመሪያ እንደሚወዱት አሁን አይወዱትም (ራእ. 2፥4)፤ የቀድሞውን ነገር እንዲያስታውሱ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ለእርሱ እንዲሠሩና በእውነት እንደሚወዱት እንዲያሳውቁት መከራቸው። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ማወቅ ሐሰተኞች መምህራንንም መለየት ጥሩ ነገር ነው (1ቆሮ. 1፥5፤ 1ዮሐ. 4፥1)፤ ነገር ግን ጌታን ከመውደድ የሚበልጥ ነገር የለም።

ሁለተኛው መልእክት የተላከው ለሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ነበር (ራእ. 2፥8–11)፤ ከሰባቱ መልእክት በጣም አጭር የሆነው ይህ መልእክት ነው። የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ችግር ያየችና ገናም የምታይ ነች። አማኞች በዓለም ላይ ብዙ ነገር ለላልነበራቸው ሰዎች ድሆች አድርገው ይቆጥሩአቸው ነበር። ክርስቶስ ግን በሰማይ ያላቸውን ዋጋ ለለሚያውቅ ሀብታሞች መሆናቸውን ገለጠ። አንዳንድ ሐሰተኞች መምህራን አይሁዳውያን ነን ይሉ ነበር። ነገር ግን የሰይጣን ወገኖች ነበሩ፤ ብዙ አማኞች ተገድለዋል፤ ነገር ግን እያንዳንዳቸው የሕይወት አክሊል እንደሚያገኙ ጌታ ተስፋ ሰጥቶአል። ሐዋርያት በሕይወት ሳሉ ብዙ አማኞች አሠቃቂ መከራ ደርሶባቸዋል። ለምሳሌ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ (ሐሥ. 7)፤ ጳውሎስ ለብዙ ዓመታት በእስር ቤታ ቆየ። ዮሐንስ ከሞተ በኋላ ግን አንዳንድ የሮማውያን ነገሥታት መጽሐፍ ቅዱስን አቃጠሉ፤ ክርስቲያኖችንም ገደሉ። ይህም ለ200 ዓመታት በመደጋገም ተደረገ። ዛሬም ቢሆን አንዳንድ ገዥዎች አብያተ ክርስቲያናትን ለማጥፋት ይፈልጋሉ። በዚህ ጊዜ አማኞች ጌታ የሰጠውን ተስፋ ማስታወስ ይኖርባቸዋል (ራእ. 2፥10–11)፤ በቀድሞ ጊዜ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማኞች ለጌታ ኢየሱስ ሕይወታቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች ሆኑ። በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መከራ ትቀበል ነበር።

ሦስተኛው መልእክት የተላከው ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ነበር። መልእክቱም የሚያወሳው ስለ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ሦስተኛ ክፍል



ነው (ራእ. 2፥12–17)፤ እነዚህ አማኞች የኖሩት የሰይጣን ዙፋን ባለበት ስፍራ ቢሆንም ለክርስቶስ ታማኞች ነበሩ። ጌታ በዚህ ነገር ቢያመሰግናቸውም በሌላ ነገር ወቅሶአቸዋል። በሰምርኔስ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ኃጢአት የመራቸውን የተንኮለኛውን ነቢይ የበለዓምን ትምህርት ተከትለው ነበር። በለዓም ይህን ያደረገው ከንጉሥ ባላቅ ገንዘብ ለማግኘት ብሎ ነው (ዘኁ. 31፥16)፤ በጴርጋሞን የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የኒቆላውያንን ትምህርት ተከትለው ነበር። ስለዚህ ጌታ ከዚህ ኃጢአታቸው እንዲመለሱ ነገራቸው። አብያተ ክርስቲያናት በአሠቃቂ መከራ ውስጥ እንዳለፉ አይተናል። ነገር ግን ይህ መከራ ወዲያው ቆመ። ቆስጠንጢኖ የተባለ ታላቅ የሮማውያን ንጉሠ ነገሥት ክርሲትያኖች እንደ ሌሎች ሰዎች በነፃነት እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ሕግ አወጣ። እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን ታዋቂ እየሆነች ስለሄደች ብዙ የዓለም ሰዎች የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ብለው ክርሲትያኖች ነን ማለት ጀመሩ። በጴርጋሞን የነበሩ አማኞች የሚኖሩት የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው የሰይጣን ዙፋን ባለበት ስፍራ ነበር (ሉቃ. 4፥6፤ ዮሐ. 12፥31)፤ ለብዙ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ወዳጅ ነበረች። ኃጢአት ምንም እንዳልሆነ የሚቆጥሩ ሐሰተኞች መምህራን በቤተ ክርስቲያን ተገኙ። ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ክፍለ ጊዜ እንደ ጴርጋሞን ቤተክርስቲያን ነበረ።

አራተኛው መልእክት የተላከው ለትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ነበር (ራእ. 2፥16–29)፤ ጴርጋሞን በመንፈሳዊ ይዞታ ከኤፌሶን የከፋች እንደሆነች አይተናል፤ የትያጥሮን ይዞታ ግን ከሁሉም የከፋ ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን እምነትና ፍቅር ሥራም ነበራት (ራእ. 2፥19)፤ ጌታም ስለነዚህ ነገሮች አመስግኖአታል። ነገር ግን ሰዎቹ አንዲት ሴት ኃጢአት እንዲያደርጉ እንድታስተምራቸው ፈቅደውላታል። ኤልዛቤል በእስራኤል ላይ የነገሠች ጨካኝ ሴት ነበረች (1ነገ. 18፥21)፤ ጌታ በትያጥሮን የነበረችውንም ሴት ኤልዛቤል ብሎአታል። ኤልዛቤል ከበለዓም የከፋች ነበረች። እንዲሁም ትያጥሮን ከጴርጋሞን የከፋች ነበረች። በጴርጋሞን የበለዓምን ትምህርት የተከተሉ ሰዎች ነበሩ። በትያጥሮን ግን ይህች ሴት ሰዎች ኃጢአት በግልጽ እንዲያደርጉ ታስተምር ነበር። በቤተ ክርስቲያን ዘመን አራተኛው ክፍል እንደ ቲያጥሮን ነበረ። ለብዙ መቶ ዓመታት የቆየች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በዚህች ቤተ ክርስቲያን ሰዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ትተው የሐሰት ትምህርት ይቀበሉ ነበር። በመልካም ሥራቸው የሚድኑ ስለሚመስላቸው ብዙ መልካም ነገር ለማድረግ ይጥሩ ነበር። ቀሳውስቱ «ገንዘብ ከከፈላችሁ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአታችሁን ይቅር

ትላችኋለች» እያሉ በማስተማር ሕዝቡን ያሳስቱ ነበር። ይህም ከኤልዛቤል ትምህርት ያላነሰ ክፉ ነገር ነበር። በትያጥሮን የኤልዛቤል ትምህርት ያልተቀበሉ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ። ጌታ እነዚህን ሰዎች የያዛችሁትን እውነት እኔ እስክመጣ ድረስ ጠብቁ እንጂ ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም አላቸው (ራእ. 2፥24–25)፤ የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እስከ ቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ድረስ እንደሚቀጥል እናያለን። ከዚህ በላይ የተጠቀሰችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ሆና ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ በብርታትዋ ትቀጥላለች። ነገር ግን በውስጥዋ ብዙ እውነተኞች አማኞች አሉ። ጌታንም በእርግጥ ይወዳሉ፤ ድል የሚነሡት ሽልማት እንደሚያገኙ ጌታ ተናግሮአል (ራእ. 2፥26–28)።

አምስተኛው መልእክት የተላከው ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ነበር (ራእ. 3፥1–8)፤ በሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሰዎች የዘላለም ሕይወት ያላቸው ይመስላቸው ነበር። ነገር ግን ይህ እውነት አልነበረም (ራእ. 3፥1)፤ ጌታ ሥራቸው ፍጹም እንዳልሆነ ተናግሮአል። ባልጠበቁትም ሰዓት እንደሚመጣባቸው ነግሮአቸዋል (ራእ. 3፥2–3)፤ ነገር ግን ንጽሕናቸውን የጠበቁ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። እነርሱ ከጌታ ጋር ስመሄድ የተገባቸው ሆነዋል (ራእ. 3፥4)፤ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አምስተኛው ክፍል ከቤተክርስቲያን ተሐድሶ በኋላ የተገኙ አብያተ ክርስቲያናት ጊዜ ነው። የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እየከፋ በመሄዱ ብዙ ክርስቲያኖች ከዚያ ወጥተው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን አቋቋሙ። የእነርሱ እምነት «ደኅንነት የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው» የሚል ነበር። በሰርዴስ ጥቂት እውነተኞች አማኞች ነበሩ። ለእነርሱ አስደናቂ ተስፋ ተሰጥቶአቸዋል (ራእ. 3፥4–5)፤ የሰርዴስም ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እስከ ቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ድረስ ይቀጥላል። ብዙዎች የዘመኑ ክርስቲያኖች የጌታን መምጣት አይጠባበቁም። ስለዚህ ጌታ በድንገት ይመጣባቸዋል (ራእ. 3፥3)።

ስድስተኛው መልእክት የተላከው ለፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ነበር (ራእ. 3፥7–13)፤ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሉ አማኞች ኃይላቸው ትንሽ ቢሆንም ጌታ እንዲያገለግሉት በር ከፍቶላቸዋል (ራእ. 3፥8)፤ ቃሉን ስለጠበቁም ከታላቅ መከራ እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶላቸዋል። በትያጥሮንና በሰርዴስ ብዙ ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርት ሲከተሉና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሞቱ ሲሆኑ ጌታን የሚወዱና ለእውነት የቆሙ ጥቂት አማኞች እንደነበሩ አይተናል። በፊላደልፍያ ግን በዚህ ሁኔታ የሚገኙ ጥቂት ሰዎች አልነበሩም፤ ነገር ግን ራሷ



የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ጥቂት እውነተኞች አማኞችን የያዘች ነበረች። ጌታም ምንም የሚነቀፍ ነገር አላገኘባትም። ከፊላደልፍያና ከሰምርኔስ አብያተ ክርሲትያናት በቀር ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ንስሓ እንዲገቡና ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ጌታ ነግሮአቸዋል (ራእ. 2፥5፤ 16፥22፤ 3፥3፥ 19)፤ በትያጥሮንና በሰርዴስ የነበረው ሁኔታ እስከ ቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ድረስ እንደሚዘልቅ ተመልክተናል። በፊላደልፍያ ላሉት አማኞች ጌታ በቶሎ እመጣለሁ ስላላቸው የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ጌታ እስከሚመጣ እንደሚቀጥል እንረዳለን (ራእ. 3፥11)፤ የፊላደልፍያ ክፍለ ጊዜ መቼ ተጀመረ? ከቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በኋላ የተገኙ አብያተ ክርስቲያናት አጀማመራቸው መልካም እንደነበርና ደኅንነት የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው ብለው እንዳስተማሩ ተመልክተናል። ነገር ግን ብዙ ሳይቆዩ ጌታ በመንፈሳዊው ሕይወት ሙታን መሆናቸውን ገለጠ። ብዙ እውነተኞች አማኞች ከታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ወይም የሃይማኖት ክፍሎች ወጥተው የጌታን ትምህርት በጥንቃቄ መከተልና ጌታንም በትጋት ማገልገል ጀመሩ። ስለዚህ የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርሲትያን ዘመን ስድስተኛው ክፍል ምሳሌ እንደሆነችና እስከ መጨረሻውም እንደምትዘልቅ እንመለከታለን።

ሰባተኛው ወይም የመጨረሻው መልእክት የተላከው ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ነበር (ራእ. 3፥14–22)፤ በሎዶቅያ የነበሩ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል አልጣሉም። ነገር ግን ለጌታ ያላቸው ፍቅር በጣም ተቀንሶአል። ቀዝቃዛም አልነበሩም፤ ሙቅም አልነበሩም፤ ለብ ያሉ በመሆናቸው ጌታ ሊተፋቸው ደርሶአል (ራእ. 3፥15–18)፤ ሀብታሞች የሆኑ መስሎአቸው ነበር። ጌታ ግን ድሆች እንደሆኑ ነገራቸው (ራእ. 3፥17–18)፤ ነገር ግን ጌታ ፍቅሩን አላቋረጠባቸውም። እንዲያውም የሚጋብዙት ከሆኑ ወደ ልባቸው እንደሚገባ ነገራቸው (ራእ. 3፥19–20)፤ ዛሬ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ይህን የሚመስል ነው። እኛ የምንገኘው በቤተ ክርስቲያን ዘመን በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ነው። አሁንም «ብዙ ሀብት አለኝ፤ የሚጎድልብኝም ምንም የለም» በሚል ትምክህት የሚመላለሱ ብዙዎች ናቸው፤ በዚህም ዓይነት ሁሉን ነገር ትተው ጌታን ለማገልገል የሚገፋፋ ፍቅር የላቸውም።

እንግዲህ ለባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ለሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ክፍለ ጊዜዎች ምሳሌ ናቸው። ጌታ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያንና በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የነበረውን መልካም ነገርና ክፉ ነገር አይቶአል። ነቀፌታ ያላገኘባቸው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት

ብቻ ናቸው። የቀሩት ግን በክፋት ላይ ክፋት እየጨመሩ ሄደዋል። ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አራቱ እስከ መጨረሻው የሚዘልቁ ናቸው። የእነርሱም ሁኔታ ዛሬ በዓለም ላይ የምናየው ነው። ብዙ ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርት ይከተላሉ። ሌሎች ደግሞ እውነትን የሚያውቁ ቢሆንም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሞተዋል። ጥቂቶች ጌታን ይወዳሉ፥ ያገለግሉታልም። ብዙ ሰዎች በገንዘብ ሀብታሞች ናቸው። ነገር ግን መንፈሳዊ ሀብት የላቸውም። አንዳንድ ሰዎች እንደ ትያጥሮን፥ እንደ ሰርዴስ፥ እንደ ሎዶቅያ በመሰለ ቤተክርስቲያን በመገኘታቸው ይበሳጫሉ። ምንም ነገር ማድረግ የማይቻላቸው ይመስላቸዋል። ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደነርሱ ላሉት ጥቂት አማኞች ጌታ የሰጠውን ተስፋ ማስታወስ ይኖርባቸዋል (ራእ. 2፥24–25፤ 3፥4፥ 20)፤ በእያንዳንዱ መልእክት ድል ለሚነሡት የተሰጠ ተስፋ አለ። በቤተ ርክስቲያን ዘመን መጨረሻ ጌታ የሚወዱትንና ቃሉን የሚጠብቁትን ያውቃል። እነርሱ በፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። ጌታም በቅርብ ጊዜ ከሚመጣው ታላቅ መከራ እውነተኞች አማኞችን ይጠብቃል።

# ክፍል 7

## ከቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ።

ጌታ ሊመጣ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ያበቃል። በመነጠቅ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ጋር ለመሆን ትሄዳለች። ከመነጠቅ በኋላስ ምን ይሆናል? በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ጌታ ለሕዝቡ ሽልማቶችን ወይም አክሊሎችን እንደሚሰጥ ቀደም ብለን ተመልክተናል። በምድር ላይ ሕይወታቸውን ያባከኑ አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ጊዜ ሙልጫቸውን ይወጣሉ (1ቆሮ. 3፥15)፤ ከዚህ በኋላ ግን በሠርግ ግብዣ ላይ እንዳለ ታላቅ የደስታ ጊዜ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ እንደሆነች ከዚህ በፊት ተረድተናል። በዮሐንስ ራእይ ጌታ ኢየሱስ 28 ጊዜ በግ ተብሎ ተጠርቶአል። ሰዎች ገድለውታል። ነገር ግን ታላቅ ምስጋናና ክብር ያገኛል (ራእ. 5፥12)፤ በሠርጉ ግብዣ ላይ ዋና የሚሆነው ክርስቶስ ስለሆነ ግብዣው «የበጉ የሠርግ ግብዣ» በመባል ይታወቃል (ራእ. 19፥5–9)፤ ቤተ ክርስቲያን የበጉ ሙሽራ በመሆን ነጭ ልብስ ለብሳ እዚያ ትገኛለች፤ ሌሎች አማኞችም በግብዣው ላይ እንዲገኙ ይጠራሉ። እነዚህ አማኞች ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በፊት የዳኑ ናቸው። ስለሆነም የክርስቶስ አካል አባሎች አይደሉም (ዮሐ. 3፥29፤ ዮሐ. 10፥16)። ከሁሉም የሚያስደስተው ነገር የእግዚአብሔር በግ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እዚያ



መገኘቱ ነው። የበጉ የሠርግ ግብዣ የሚሆነው በሰማይ ነው። በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ምን ይሆናል? ጌታ ወደ ምድር እንደሚመለስና ንጉሥ ሆኖ እንደሚገዛ ተመልክተናል። ከዚያ በፊት ግን ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ስለ ጭንቅ መጀመሪያ፥ ስለ ታላቁ መከራ፥ ስለ ሰው ልጅ መምጣት በማቴዎስ 24 ተመልክተናል። በዚያን ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይጠላሉ። ሊያጠፉአቸውም ይሞክራሉ። በዚያን ጊዜ አይሁዳውያን መሸሽ ይኖርባቸዋል (ማቴ. 24፥16–20)፤ ትንሹ ቀንድ የተባለው የአረማውያን ንጉሥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ የእግዚአብሔርን ወገኖች ያሳድዳል (ዳን. 7፥21–22)፤ በራእይ 19 ጌታ መጥቶ ጠላቶቹን በድንገት እንደሚያጠፋቸው እንረዳለን። በራእይ 19፥11–16 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ እናየዋለን። አራት ስሞች አሉት፦

1/ ታማኝና እውነተኛ (ቁ. 11)

2/ እርሱ ራሱ ብቻ የሚያውቀው ስም (ቁ. 12)

3/ የእግዚአብሔር ቃል (ቁ. 13)

4/ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ (ቁ. 16)። እርሱ የሚመጣው በዓለም ሊፈርድ ሕዝቡን ሊያድንና ጠላቶቻቸውንም ሊያጠፋ ነው።

በመጀመሪያ አንድ መልአክ ወፎቹን ሁሉ ይጠራል። የእግዚአብሔርንም ጠላቶች ሥጋ ይበላሉ (ራእ. 19፥17–16)፤ የምድር ነገሥታት የእግዚአብሔርን ልጅ ለመውጋት ወታደሮቻቸውን ያከማቻሉ (ራእ. 19፥19)፤ ሆኖም ጦርነቱ ብዙ አይቆይም። መሪዎቹ ይያዛሉ፥ ወታደሮቻቸውም ይደመሰሳሉ (ራእ. 19፥20–21)፤ የእግዚአብሔር ልጅ ጠላቶቹን ሁሉ ሲያጠፋ ሁለቱ ግን ከነሕይወታቸው ይያዛሉ። እነርሱም አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ናቸው (ራእ. 19፥19–20)፤ ዳንኤል አራት እንስሳት በሕልም እንዳየና እነርሱም የአራት ታላላቅ ነገሥታት ምሳሌዎች እንደነበሩ እናስታውሳለን (ዳን. 7፥17)፤ እዚህ ላይ የዓለም ነገሥታት የእግዚአብሔርን ልጅ ሊወጉ በሚሄዱበት ጊዜ መሪ የሚሆናቸው ይህ አውሬ እንደሆነ እንመለከታለን (ራእ. 19፥19)፤ ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ታላላቅ ተአምራት የሚያደርጉ ሐሰተኞች መሢሖችና ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሡ ከዚህ በፊት ተረድተናል (ማቴ. 24፥24)፤ ከነዚህ ከሐሰተኞች ነቢያት አንዱ ሰዎች አውሬውን እንዲያመልኩ ያደርጋል። ስለ አውሬውና ስለ ሐሰተኛው ነቢይ ወደፊት በይበልጥ እንረዳለን። እዚህ ላይ እነዚህ ክፉዎች ሰዎች ከነሕይወታቸው ወደ እሳት ባሕር እንደሚጣሉ እንመለከታለን (ራእ.

19፥20)፤ በዚህ ዓይነት ሁለት ታላላቅ ጠላቶች ይወገዳሉ። አሁን ደግሞ የሰዎች ዋና ጠላት ለሺ ዓመት እንደሚታሰር እንመለከታለን (ራእ. 20፥1–3)፤ ይህም ጠላት አራት ስሞች አሉት፦

1/ ዘንዶ (ደራጎን)፦ ይህ የሚያስፈራ አውሬ በዮሐንስ ራእይ የሰይጣን ምሳሌ ነው።
2/ የቀድሞው እባብ፦ ሰይጣን በእባብ ተመስሎ ሔዋንን አስቶ ነበር (ዘፍ. 3፥1)።
3/ ዲያብሎስ፦ ይህ ቃል ሰይጣን ከሳሽ መሆኑን የሚያመለክት ነው (ራእ. 12፥10)።
4/ ሰይጣን፦ ይህ ስም የሚያመለክተው የእግዚአብሔርና የሰው ጠላት መሆኑን ነው (1ተሰ. 2፥16)።

እዚህ ላይ መልአኩ ዘንዶውን በሰንሰለት አስሮ ወደ ጥልቅ ጉድጓድ እንደሚጥለው እንረዳለን። ሰይጣን ለሺ ዓመት ሰዎችን ሊያስት አይችልም። በዚህ በሺ ዓመት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ሁሉ ላይ ይነግሣል። ይህም ጊዜ «የሺ ዓመት መንግሥት» በመባል ይታወቃል። ስለ ሺ ዓመት መንግሥት ወደፊት በሰፊው እንረዳለን። የነገሥታት ንጉሥ ክርስቶስ ለሺ ዓመት በዓለም ላይ ይነግሣል። የእርሱም ሕዝቦች አብረውት ይነግሣሉ (ራእ. 20፥4–6)፤ በታላቁ መከራ ዘመን ብዙ አማኞች ስለ ክርስቶስ በመናገራቸውና አውሬውን አንከተልም በማለታቸው ይገደላሉ። እነርሱም ክርስቶስ ሲመጣ ከሞት ተነሥተው ከእርሱ ጋር ይነግሣሉ። በመነጠቅ ጊዜ ክርስቶስ ሊገለጥ አማኞች ሁሉ ከሞት እንደሚነሡ ተመልክተናል። ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው።

በታላቁ መከራ ዘመን ብዙ አይሁዳውያን ወደ ጌታ ይመለሳሉ። ወደ አረማውያንም ሄደው ወንጌልን ይሰብካሉ (ማቴ. 24፥14)፤ በዚያን ጊዜ ከሚያምኑት አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን አብዛኞዎቹ ይገደላሉ። ክርስቶስ በኃይልና በክብር በሚመጣበት ጊዜ ከሞት ስለሚነሡ የመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋዮች ይሆናሉ። ኃጢአተኞችም ከሺ ዓመት መንግሥት በኋላ ከሞት እንደሚነሡ ወደፊት እንረዳለን። ጌታ ኢየሱስ ለሺ ዓመት በምድር ላይ ሲነግሥ ሁሉ ነገር በጣም አስደሳች ይሆናል። ስለ ሺ ዓመት መንግሥት ወደፊት በሰፊው እንረዳለን። እዚህ ላይ ግን ስለ ሺ ዓመት መንግሥት መጨረሻ እንመለከታለን (ራእ. 20፥7–10)፤ ከሺ ዓመት በኋላ ሰይጣን ይፈታል። ወዲያውኑ ሰዎችን ማሳት ይጀምራል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሰዎች በመውጋት እግዚአብሔርን እንዲወጉና ኢየሩሳሌምንም እንዲወስዱ



ይገፋፋቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር በቶሎ ይፈርድባቸዋል። ከሰማይ እሳት አውርዶም ያጠፋቸዋል። ሰይጣንም ወደ እሳት ባሕር ተጥሎ ለዘላለም እንዲሠቃይ ይደረጋል። ሰዎች ሁሉ ከሞት ይነሣሉ (1ቆሮ. 15፥21–22)፤ አማኞች በመጀመሪያው ትንሣኤ ይነሣሉ። የቀሩት ሰዎች በሁለተኛው ትንሣኤ ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ ይቆማሉ። በራእይ 20፥12–15 ስለ ታላቁ ነጭ ዙፋን እናነባለን።

1/ ሰማይና ምድር ስለሚያልፍና መሸሸጊያ ስፍራ ስለማይኖር ማንም ሊያመልጥ አይችልም (ራእ. 20፥11)።
2/ ከፉዎች ሰዎች ሁሉ በዚያ ይገኛሉ (ራእ. 20፥12)።
3/ ማንም ኃጢአት አላደረግሁም ብሎ ሊከራከር አይችልም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ያደረገው በመዝገብ ተይዞአል (ራእ. 20፥12)። ሌላው መዝገብ የዘላለም ሕይወት የሚያገኙትን ስም ዝርዝር የያዘ ነው። አማኞች ሁሉ ከሺ ዓመት በፊት ተነሥተዋል። ኃጢአተኞች ሁሉ በዚህ ጊዜ ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ። ዮሐንስ በታላቁ ነጭ ዙፋን ላይ ተቀምጦ በፊቱ በቆሙት ላይ የሚፈርድ ማን እንደሆነ አይቶአል። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል (ራእ. 20፥12)፤ በዮሐንስ 5፥22፤ 23፥27 እንደምናገኘው የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንረዳለን። ሰዎች የሚፈረድባቸው አምላክም ሰውም በሆነው በሰው ልጅ ነው። አምላክ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች ያደረጉትን ሁሉ ያውቃል። ሊቀጣቸውም ሥልጣን አለው። የሰው ልጅ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች ደካሞች መሆናቸውንና ምን እንደሚሰማቸውም ያውቃል። የሰው ልጅ ለሰዎች ኃጢአት ሞቶአል። ስለዚህ እርሱን ያልተቀበሉትን ይፈርድባቸዋል። ዛሬ ብዙ ሰዎች ክርስቶስን መቀበል አይፈልጉም። በኋላ ግን ሳይወዱ በግድ በእግሩ ሥር በጉልበታቸው ይንበረከካሉ (ፊል. 2፥10)።

ኃጢአተኞች ሁሉ ከሰይጣን ጋር ወደ እሳት ባሕር ከተጣሉ በኋላ ምን ይሆናል? እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን አጥፍቶ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጥራል። የሰዎች ኃጢአት በዚህች ምድር ላይ እርግማን አምጥቶአል። ርኩሳን መናፍስትም በሰማያዊ ስፍራ ይኖራሉ (ዘፍ. 3፥17፤ ኤፌ. 6፥12)፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በእሳት ያጠፋል። ለዘላለም የሚኖሩም አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን ይፈጥራል (2ጴጥ. 3፥10፤ ኢሳ. 65፥17፤ 66፥22)፤ በራእይ 21፥1 ዮሐንስ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንዳየ እናነባለን። በአዲሊቱ ምድር ኃጢአት ወይም ክፋት እንደማይኖር ጴጥሮስ ይነግረናል። በዚያ የሚኖሩት ጻድቃን ብቻ ናቸው (2ጴጥ. 3፥13)።

መንግሥተ ሰማያት ምን ትመስላለች? ከራእይ 21፡1 እስከ ራእይ 22፡5 ያለው ክፍል ስለ መንግሥተ ሰማያትና ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ያስረዳናል። በመንግሥተ ሰማያት ለባት ነገሮች አይኖሩም።

1/ ሐዘን ወይም ሥቃይ (21፡4)።

2/ ቤተ መቅደስ (21፡22)። ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ እዚያ ይገኛል።

3/ ፀሐይ ወይም ጨረቃ (21፡23)። ምክንያቱም እግዚአብሔር ብርሃን ስለሆነ ነው።

4/ ሌሊት (21፡25፤ 22፡5)።

5/ ኃጢአት ወይም ኃጢአተኛ (21፡27)።

6/ እርግማን (22፡3)።

7/ ረሀብ ወይም ጥማት (7፡16)።

በመንግሥተ ሰማያት የሚኖሩ ነገሮች።

1/ ብርሃን (21፡23)።

2/ ሕይወት (21፡27)። በዚያ የሚገኙት ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ብቻ ናቸው።

3/ የሕይወት ውሃ ወንዝ (22፡1)።

4/ የሕይወት ዛፍ (22፡2)።

5/ የእግዚአብሔር ዙፋንና በጉ (22፡3)።

6/ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፣ ፊቱንም ያዩታል (22፡3-4)።

7/የእግዚአብሔር ስም በግንባሮቻቸው ላይ ይጻፋል (22፡4)።

ገሃነመ እሳትና የእሳት ባሕር ምን ይመስላሉ? በዮሐንስ ራእይ የተጠቀሰው የእሳት ባሕር ነው።

1/ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደዚያ ይሄዳሉ (19፡20)።

2/ ዲያብሎስ ወደዚያ መሄድ ይኖርበታል (20፡10)።

3/ ኃጢአተኞች ሁሉ ወደዚያ ይሄዳሉ (20፡15፤ 21፡8)። ማንም አማኝ ወደ እሳት ባሕር አይሄድም (2፡11፤ 20፡6)፤ ወደ እሳት ባሕር የገባ ማንም ከዚያ ሊያመልጥ አይችልም (20፡10)። ወደ እሳት ባሕር መጣል ሁለተኛ ሞትነው (20፡14፤ 21፡8)። በእሳት ባሕር ያሉ ሰዎች ያዝናሉ፣ እግዚአብሔርንም ይቆጣሉ (ማቴ. 13፡42)።



መንግሥተ ሰማያትና ገሃነመ እሳት የት ነው የሚሆኑት? አንዳንድ ሰዎች መንግሥተ ሰማያት በሰማይ ላይ፣ የእሳት ባሕር ደግሞ በምድር ውስጥ የሚሆኑ ይመስላቸዋል። መንግሥተ ሰማያትና የእሳት ባሕር የት እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም። ነገር ግን መንግሥተ ሰማያት ጌታ ኢየሱስ ያለበት ቦታ እንደሆነ እናውቃለን። እርሱ ባለበት እንድንሆን አባቱን ለምኖልናል (ዮሐ. 17፡24)፤ ስለ መንግሥተ ሰማያት ዋናው ነገር ይህ ነው። ኃጢአተኞች ሁሉ የእሳት ባሕር ወደተባለው ስፍራ ይሄዳሉ። ይህ ሥፍራ ከእግዚአብሔር መኖሪያ በጣም የራቀና በጣም የጨለመ ነው (2ጴጥ. 2፡7፤ ይሁዳ 13)፤ ክፉዎች በወንጌል ባለማመናቸው ምክንያት ከጌታ ለዘላለም ይለያሉ (2ተሰ. 1፡8-9)፤ ጊዜው ሳይደርስ በክርስቶስ እንዲያምኑ ልናስጠነቅቃቸው ይገባናል። አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር የሚቆዩት እስከ መቼ ነው? ይህን ጥይቄ መመለስ የምንችለው ሌሎች ሁለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው። እግዚአብሔር የሚኖረው እስከ መቼ ነው? አገልጋዮቹስ የሚኖሩት እስከ መቼ ነው?

1/ እግዚአብሔር የሚኖረው ለዘላለም ነው (ራእ. 15፡7)።

2/ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደ ነገሥታት ሆነው ለዘላለም ይኖራሉ (ራእ. 22፡5)።

ዘላለም ምን ያህል ጊዜ ነው? ዘላለም በጣም ትልቅ ከምንለው ቁጥር ዓመታት የሚበልጥ ነው። አዳምን ከመፍጠሩ በፊት በዘላለማዊነት ይኖር ነበር። ከሺሁ ዓመት መንግሥት በኋላ እኛ የምንኖረው ወደፊት ባለው ዘላለማዊነት ውስጥ ነው። ስለዚህ ለአዲሱ ሰማይና ለአዲሲቱ ምድር ምንም መጨረሻ የላቸውም። እንዲሁም ለእሳት ባሕር መጨረሻ የለውም (ራእ. 14፡11፤ 19፡3፤ 20፡10)።

እስከ አሁን ያየነው ከራእይ 19፡1 እስከ 21፡5 ያለውን ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ያየነው ስለ ስድስት ታላላቅ ነገሮች ነው።

1/ ስለ ሠርጉ ግብዣ።

2/ ክርስቶስ በኃይልና በክብር እንደሚመጣ።

3/ ስለ መጀመሪያው ትንሣኤ (የሁለተኛው ክፍል)።

4/ ስለ ሺው ዓመት መንግሥት።

5/ ስለ ታላቁ ነጭ ዙፋን።

6/ ስለ አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር።

# ክፍል 8

## አንድ ሺ አስደሳች ዓመታት።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ብዙ የተስፋ ቃሎች በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እናነባለን። ከነዚህ የተስፋ ቃሎች አብዛኛዎቹ ቀደም ብለው ተፈጽመዋል። ስለዚህ የገባውን ቃል እንደሚፈጽም እርግጠኞች መሆን እንችላለን። የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለ ክርስቶስ ብዙ የተስፋ ቃሎችን ጽፈዋል። ከእነዚህ የተስፋ ቃሎች አንዳንዶቹ የሚያወሱት ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደ ምድር ስለ መጣበት ጊዜ ነው። የእስራኤል ገዥ በቤተልሔም እንደሚወለድ እግዚአብሔር ለሚክያስ ነግሮት ነበር። እንደተባለውም ክርስቶስ የተወለደው በቤተልሔም ነበር (ሚክ. 5፥2፤ ማቴ. 2፥6)፤ ልጁ ወይም ዘሩ ለዘላለም ንጉሥ እንደሚሆን እግዚአብሔር ለዳዊት ነግሮት ነበር። ክርስቶስ የዳዊት ዘር ነበር (2ሳሙ. 7፥12፤ 13፥16፤ ማቴ. 22፥42፤ ሮሜ 1፥3)፤ የክርስቶስ እናት ድንግል እንደምትሆን እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ነግሮት ነበር። ማርያም በድንግልናዋ በመንፈስ ቅዱስ እንደጸነሰች እናውቃለን (ኢሳ. 7፥14፤ ማቴ. 1፥20–23)፤ ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር እነዚህን የተስፋ ቃሎች ሁሉ ፈጽሞአል። ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ሌሎችን የተስፋ ቃሎች ይፈጽማል። የተስፋ ቃሎቹ ሁሉ የሚፈጸሙበት ጊዜም ይመጣል።

መዝሙር 22 ስለ ክርስቶስ እንደሚናገር እናውቃለን፤ ምክንያቱም እርሱ ራሱ በመስቀል ላይ በነበረበት ጊዜ፥ በዚህ ምዕራፍ በቁጥር አንድ ላይ ያሉትን ቃሎች ተናግሮአል (ማቴ. 27፥46)፤ እግዚአብሔር በመቃብር ውስጥ እንደማይተወው ተናግሮ ነበር (መዝ. 16፥10)፤ በእርግጥም ከሞት አስነሥቶታል (ሐ.ሥ. 2፥31፤ 13፥35–37)፤ ኢሳይያስ 53 ስለ ክርስቶስ እንደሚናገር እናውቃለን። ምክንያቱም ፊሊጶስ ስለ እርሱ እንደሚናገር አመልክቶአል (ሐ.ሥ. 6፥31–35)፤ በኢሳይያስ 53፥4–5 መሢሕ እንደሚመጣና ስለ ኃጢአታችን መከራ እንደሚቀበል እንረዳለን። ክርስቶስ የሞተበት ምክንያት ይህ እንደሆነ በአዲስ ኪዳን ብዙ ጥቅሶች ያስረዱናል (1ጴጥ. 3፥16)፤ ስለ ክርስቶስ ክብር የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ። ለምሳሌ በኢሳይያስ 32፥1 አንድ ንጉሥ መጥቶ በጽድቅ እንደሚገዛ ይናገራል። እነዚህ የተስፋ ቃሎች ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ አልተፈጸሙም። ነገር ግን በኃይልና በክብር ተመልሶ ይመጣል። እስቲ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን በጥንቃቄ እንመልከት።



ሚክያስ 5፥2 የእስራኤል ገዥ ከቤተልሔም እንደሚመጣ ይናገራል። በእርግጥም ጌታ ኢየሱስ የተወለደው በቤተልሔም ነው (ማቴ. 2፥1)፤ ዘካርያስ 9፥9 በአህያ ላይ ተቀምጦ እንደሚመጣ ይናገራል። በእርግጥም በአህያ ላይ ተቀምጦአል (ማቴ. 21፥4–7)፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ ተፈጽመዋል። እንደዚሁም በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ በመጀመሪያ ለሕዝቡ እንደሚመጣ እናነባለን (1ተሰ. 4፥16)፤ ቀጥሎም ከሕዝቡና ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ይመጣል (1ተሰ. 3፥13)፤ በእነዚህ የዳግም ምፅአት ሁለት ክፍሎች መካከል ያለው ጊዜ ሰባት ዓመት እንደሚሆን ወደፊት በሰፊው እናያለን። የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች የክርስቶስ አካል ስለሆነችው ስለ ቤተክርስቲያን ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ይህን ታላቅ እውነት ለሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው (ኤፌ. 3፥4–6)፤ ጌታም ስለ መነጠቅ ለጳውሎስ ነግሮታል (1ተሰ. 4፥15)፤ በብሉይ ኪዳን ክርስቶስ በኃይልና በክብር እንደሚመጣ የሚናገሩ ብዙ አደናቂ የተስፋ ቃሎች አሉ። በአዲስ ኪዳን ዳግም ምፅአት ሁለት ክፍሎች እንዳሉትና የመጀመሪያው ክፍል መነጠቅ እንደሆነ እንረዳለን።

እስቲ ከብሉይ ኪዳን ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ እንደሚመጣ የሚያመለክቱትን የተስፋ ቃሎች እንመልከት።

1/ ነገሥታት ሁሉ የዳዊት ዘር ለሆነው ንጉሥ ይሰግዳሉ (መዝ. 72፥11)።

2/ የዳዊት ዘር በይሁዳ ይነግሣል (ኤር. 23፥5፤ 33፥15–21)።

3/ የሰው ልጅ በሕዝቦች ሁሉ ላይ ይነግሣል (ዳን. 7፥13–14)።

የዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ በዓለም ላይ እንደሚነግሥ እግዚአብሔር ቃል ገብቶአል። ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ራእ. 11፥15)፤ ክርስቶስ በሚነግሥበት ጊዜ ለሺ ዓመታት በምድር ላይ ሰላም ይሆናል። ንጉሥ ዳዊት ከይሁዳ ነገድ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ከይሁዳ ነገድ ነው። ጌታ በእስራኤልና በዓለም ሕዝቦች ሁሉ ላይ ይነግሣል። በእርሱ መንግሥት ዋና የምትሆነው እስራኤል ነች። ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት አይሁዳውያን በታላቅ መከራ ውስጥ ያልፋሉ፤ ብዙዎቹም ሕይወታቸውን ለማዳን ይሸሻሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ወንጌልን ለመስበክ ወደ ሩቅ አገሮች ይሄዳሉ (ማቴ. 24፥14–16)፤ ጌታ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ አይሁዳውያን እንዲሰበስቡ መላእክትን ይልካቸዋል (ማቴ. 24፥31)፤ በክርስቶስ መንግሥት ዘመን አይሁዳውያን በእስራኤል ምድር በሰላም ይኖራሉ (አሞ. 9፥14–15)፤ ጌታ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ይሠራል (ዘካ. 6፥12–13)፤ ይህን

ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል በራእይ አሳይቶታል (ሕዝ. 40–46)፤ በሺው ዓመት መንግሥት ሰዎች ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ሊሰግዱ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ። ወደ ኢየሩሳሌም የማይመጡትን እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል (ዘካ. 14፥17–19)፤ ጌታ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ በመጀመሪያ የሚደመሰሰው የእግዚአብሔርን ጠላቶች ነው። በመዝሙር 2 በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ላይ በጠላትነት ለለሚነሡ ሰዎች እናነባለን። ክርስቶስ በጽዮን ተራራ በኢየሩሳሌም ላይ እንዲነግሥና ሕዝቦችን ሁሉ እንዲቆጣጠር እግዚአብሔር ሥልጣን ይሰጠዋል (መዝ. 2፥2፤ 3፥6፤ 8፥9)።

ክርስቶስ የሚያስተዳድረው በጽድቅ ነው (ኢሳ. 11፥4–5)፤ ዛሬ እንደሚሆነው ዓይነት ኃጢአተኞች በዓመፃ አይበለጽጉም (ኢሳ. 32፥1–5)፤ ሰዎች ሁሉ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ ይኖርባቸዋል (ኢሳ. 26፥9)፤ በምድር ላይ የሚቋቋመው የክርስቶስ መንግሥት በአንድ በኩል መንግስተ ሰማያትን ይመስላል። ምክንያቱም ወደዚያ የሚገቡት እውነተኞች አማኞች ብቻ ናቸው። አዲስ ሕይወት የሌለው ማንም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም (ዮሐ. 3፥3)፤ እንዲሁም ስሙ በሕይወት መጽሐፍ የተጻፈ ካልሆነ በቀር ማንም ኃጢአተኛ ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም (ራእ. 21፥27)፤ በመንግሥተ ሰማያትና በምድራዊ መንግሥቱ መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ። በመንግሥተ ሰማያት ሰዎች እንደ መላእክት ስለሚሆኑ መጋባት የለም (ማቴ. 22፥30)፤ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር መጥቶ ሲገዛ ወደ ሺው ዓመት መንግሥት እንዲገቡ የሚፈቅድላቸው በምድር የነበሩ የእርሱ ሕዝቦች ይጋባሉ፤ ብዙ ልጆችም ይኖሩአቸዋል። የእነርሱ ልጆችም አድገው ያገባሉ። ብዙ ልጆችም ይኖሩአቸዋል። እነዚህ ሰዎች ሁሉ በጽድቅ ለሚገዛው ንጉሥ መታዘዝ ይኖርባቸዋል። ከእነርሱም በክርስቶስ አምነው ዳግመኛ ይወለዳሉ። ሁሉም ጌታን ያውቃሉ። ነገር ግን አንዳንዶቹ አይወዱትም (ኢሳ. 11፥9፤ ኤር. 31፥34)፤ ዛሬ ብዙ መሪዎች ከሕዝብ ብዛት የተነሣ በዓለም ላይ ረሀብ ይሆናል እያሉ ይሠጋሉ። በክርስቶስ መንግሥት ግን ለሰዎች ሁሉ የሚበቃ ምግብ ይገኛል።

1/ ምድር ጥሩ ሰብል ትሰጣለች። በረሃዎችም ይለመልማሉ (ኢሳ. 35፥1፤ 51፥3፤ ሕዝ. 36፥34–35)።

2/ አራዊት ለማዳ ይሆናሉ (ኢሳ. 11፥8–6)።

3/ ክርስቶስ ሰዎችን ስለሚፈውስ ብዙ ሰዎች በጣም እስኪያረጁ ይኖራሉ (ኢሳ. 65፥20፤ ሚክ. 4፥2)።



## ሌላስ ስለ ክርስቶስ መንግሥት ምን እንማራለን?

1/ በመላው ዓለም ሰላም ስለሚሆን ሕዝቦች የጦር ሠራዊት በማደራጀት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ማባከን አይኖርባቸውም። ጌታ የሰላም አለቃ ይባላል (ኢሳ. 9፥6)።
2/ ክርስቶስ በኃይልና በጽድቅ በሚገዛበት ጊዜ ወንጀል ስለማይኖር ፖሊስ አያስፈልግም።
3/ ሰዎችን የሚያታልሉና ገንዘባቸውንም የሚበዘብዙ ሐሰተኞች ሃይማኖቶች በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ አይኖሩም።

ክርስቶስ ለሺ ዓመት ንጉሥ ሆኖ ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ በዓለም ላይ ታላቅ በረከት ይሆናል። እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ሁሉ ይፈጽማል። ታዲያ አንዳንድ አማኞች የሺ ዓመት መንግሥት የሚባል ነገር የለም ለምን ይላሉ? እነርሱም የሚሉት ክርስቶስ የሚነግሠው በልባችን ውስጥ ነው እንጂ በዓለም ላይ አይደለም ነው። እነዚህ ሰዎች የሚያስተምሩት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንደማይለው አድርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው እንደዚህ ነው።

1/ ጌታ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማል (ዘካ. 14፥4)።

2/ ኢየሩሳሌም የዓለም መካከል ትሆናለች (ኢሳ. 2፥2–4፤ ኤር. 3፥17)።

3/ ጌታም በዚያ ይሆናል (ኢዩ. 3፥17፤ ዘካ. 8፥2–3)።

4/ ጌታ በዚያ ሆኖ ያስተዳድራል (ሚክ. 4፥7)።

ከራሳችን አሳብ ጋር እንዲስማማ ብለን የአንድን ጥቅስ ቀጥተኛ ትርጉም መስወጥ አይገባም። ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣና ለሺ ዓመት ንጉሥ ሆኖ እንደሚያስተዳድር እርግጠኛ ነገር ነው። ክርስቶስ በሚያስተዳድርበት በሺው ዓመት መንግሥት በምድር ላይ ሁሉ ነገር አስደሳች ይሆናል። የሺው ዓመት መንግሥት ከአንድ ሺ ዓመት በኋላ ያበቃል። ምንም እንኳ በሺው ዓመት መንግሥት ሰዎች ታላቅ በረከት ቢያገኙም፥ ከዚያ ወደ ተሻለ ቦታ ስለሚሄዱ እግዚአብሔር የሺውን ዓመት መንግሥት ወደ ፍጻሜ ያደርሰዋል።

ከዚያ በፊት ለለ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንነብባናል። አዲሲቱ ምድር ከዚህችኛይቱ ምድር በጣም የተሻለች ትሆናለች። ይህች ምድር በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር እርግማን በታች ሆናለች። የእግዚአብሔር ልጅ የተሰቀለው በዚህች ምድር ላይ ነው። ከሺ ዓመት በኋላ እንኳ በዚህች ምድር ላይ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ ይነሣሉ። በዚህ ሁሉ ምክንያት እግዚአብሔር ይህችን ምድር በእሳት አጥፍቶ አዲስ ምድር ይፈጥራል።

በሺው ዓመት መንግሥት ጊዜ ጽድቅ ይህን ዓለም ይገዛል። በአዲሲቱ ምድር ግን ጽድቅ ለዘላለም ይኖራል (2ጴጥ. 3፥13)፤ ይህ ዓለም ብዙ የቆየ ነው። ነገር ግን ይጠፋል። አዲሱ ዓለም ግን ለዘላለም ይኖራል።

# ክፍል 9

## ወደፊት የሚመጡ ታላላቅ መሪዎች

ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት አሠቃቂ መከራ እንደሚሆን ተመልክተናል። ሰዎች ይታሰላሉ። እግዚአብሔርንም ስመውጋት ይነሣሉ። ጌታ ከመምጣቱ በፊት በሚሆነው በታላቁ መከራ ዘመን በዓለም ላይ ታላላቅ መሪዎች የሚሆኑት እነማን ናቸው? ጌታ ኢየሱስ የአባቱን ሥልጣን ይዞ እንደመጣ ተናግሮ ነበር። ነገር ግን እስራኤላውያን አልተቀበሉትም። በራሱ ሥልጣን የሚመጣ ሌላ ሰው እንዳለ ተናግሮ ነበር (ዮሐ. 5፥43)፣ የእስራኤል ሕዝብ ይህን ሰው መሪያቸው አድርገው እንደሚቀበሉትም ጌታ ተናግሮአል። ታላቅ መሪ እንደሚመጣና አይሁዳውያንም እንደሚቀበሉት የሚያስረዱ ሌሎች ብዙ ጥቅሶች አሉ። አይሁዳውያን መሢሕ እንደሚመጣና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው በብሉይ ኪዳን የተሰጡትን የተስፋ ቃሎች በመጥቀስ ይናገራሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል አይፈልጉም፣ ነገር ግን ሌላ መሢሕ ለመቀበል ዝግጁ ናቸው። እግዚአብሔር የእስራኤል አዳኝ እንዲሆን ልጁን ልኮአል። ስለሆነም ከእንግዲህ ወዲህ የሚመጣው መሢሕ በራሱ ሥልጣን የሚመጣ ነው።

## የክርስቶስ ተቃዋሚ።

በመከራው ዘመን ብዙ ሐሰተኞች ክርስቶሶች ወይም መሢሖች እንደሚመጡ ጌታ ኢየሱስ ተናግሮአል። በመጨረሻ ግን «የክርስቶስ ተቃዋሚ» የሚባል ታላቅ መሪ ይገለጣል (1ዮሐ. 2፥18–22፣ 4፥3፣ 2ዮሐ. 7)፣ ይህ መሪ የክርስቶስ ጠላት ብቻ አይሆንም። ነገር ግን «ዓለምን ለማዳን የመጣሁ መሢሕ ነኝ» በማለት ራሱን ያስተዋውቃል። ሐሰተኞች መሢሖች እንዳያታልሉን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ጠንቅቀን ማወቅ ይገባናል።

## ሐሰተኛው ነቢይ

በመከራው ዘመን ሐሰተኞች ነቢያትም እንደሚኖሩ ጌታ ኢየሱስ ተናግሮአል (ማቴ. 24፥11–24)፣ እነዚህ ነቢያት «ከእግዚአብሔር የተላክን ነን» በማለት ስለ ሃይማኖት ያስተምራሉ። ነገር ግን ውሸታቸውን ነው። ዮሐንስ በዘመኑ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት እንደነበሩ ተናግሮአል (1ዮሐ. 4፥1)፣ በኋላም መንፈስ ቅዱስ ስለ ሐሰተኛው ነቢይ ተናገረ። ይህ ሰው በጣም ክፉ ከመሆኑ የተነሳ ርኩስ መንፈስ ከአፉ ይወጣል (ራእ. 16፥13)፣ ይህም ከእርሱ አፍ የሚወጣው ርኩስ



መንፈስ ተአምራት ማድረግ ይችላል። የምድር ነገሥታትን በአንድነት ሰብስቦ በእግዚአብሔር ላይ ሰጦር ያስከትታቸዋል። ይህ ነቢይ «አውሬ» ከሚባለው ከታላቅ መሪ ጋር ከነሕይወቱ ወደ እሳት ባሕር ይጣላል። ዘንዶው ወይም ዲያብሎስ ወደዚያው ይሄዳል። እዚያም ለዘላለም ይሠቃያሉ (ራእ. 19፥20፣ 20፥10)።

## የዓመፅ ሰው

በ2ተሰሎንቄ 2፥3–4 ስለ ሌላ ታላቅ መሪ እናነባለን። ይህ መሪ «የዓመፅ ሰው» የሚል ስም የተሰጠው ለእግዚአብሔር ሕግ ስለማይታዘዝ ነው (2ተሰ. 2፥3–8)፣ ኃጢአተኞች ኃጢአትን በኃጢአት ላይ እየጨመሩ ሲሄዱ እግዚአብሔርን ወደ መካድ ይደርሳሉ (2ጢሞ. 3፥13)፣ ይህ ሰው ግን ከሁሉ የከፋ በመሆኑ «ዓመጸኛና ክፉ» የሚል ስም ተሰጥቶታል። ይህ ሰው አምላክ የተባለውን ሁሉ ይቃወማል። ራሱንም ከሁሉ በላይ አድርጎ በእግዚአብሔር ቤት መቅደስ ይቀመጣል። እርሱ ብቻ እንዲመለክም ያዛል (2ተሰ. 2፥4)፣ የእግዚአብሔር ሕግ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ከሆነው ከአንዱ አምላክ በቀር ሰውም ቢሆን መንፈስም ቢሆን ምስልም ቢሆን እንዳናመልክ ያዛል። ይህ ወደ ፊት የሚመጣው የዓለም መሪ ራሱ ክፉ ሆኖ ሰዎች እርሱን እንዲያመልኩ በማድረግ ከባድ ኃጢአት እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል። ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ተቀምጦ ሰዎች እንዲያመልኩት ያዛል? የዓመፅ ሰው መጥቶ ይህን የሚያደርገው በሰይጣልን ኃይል ነው። ሰይጣን ከሰው የበለጠ ኃይል አለው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ኃይል ተወዳዳሪ የሌለው ነው፣ የዓመፅ ሰው ብዙ ተአምራት የማድረግ ችሎታ ይኖረዋል። ሰዎችም ያምኑታል፣ ያመልኩታልም (2ተሰ. 2፥9–12)፣ የዓመፅ ሰው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ያስታል። እነዚህ ሰዎች እውነትን ይጠሉ የነበሩና ለመዳንም ያልፈለጉ ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ሐሰትን እንዲያምኑ አሳልፎ ይሰጣቸዋል። እውነትን በመጥላታቸውና ኃጢአታቸውን በመውደዳቸው ይፈረድባቸዋል። ሰዎችን የሚያስተውም የዓመፅ ሰው ይፈረድበታል። ይህ ሰው ወደ ገሃነመ እሳት እንደሚሄድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቃል (2ተሰ. 2፥3)፣ ጌታ ኢየሱስ በኃይልና በክብር በሚመጣበት ጊዜ ይህን የዓመፅ ሰው በትንፋሹ ያጠፋዋል (2ተሰ. 2፥8)፣ ስለዚህ የዓመፅ ሰው ክፉ ሥራውን የሚያካሂደው ጌታ እስኪመጣ ድረስ ነው።

የዓመፅ ሰው የሚገለጠውና ክፉ ሥራውን በይፋ ማካሄድ የሚጀምረው መቼ ነው? የዓመፅ ሰው የሚገለጠው በእግዚአብሔር

ላይ የመጨረሻ ዓመፅ በሚደረግበት ጊዜ ነው። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች እግዚአብሔርንና ክርስቶስን በይፋ ስለሚቃወሙ ታላቅ የክህደት ጊዜ ይሆናል። አሁን እንኳ ብዙ ክፋት በዓለም ላይ አለ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እንዴት ይህን ያህል ክፋዎችና ዓመፀኞች እንደሚሆኑ ሊገባን አይችልም። ሆኖም አሁን ክፋትን የሚከላከል ታላቅ ኃይል አለ (2ተሰ. 2፥6–7)፤ ይህም ኃይል ሁልጊዜ በምድር ላይ የማይኖረውና ሰዎችን የሚረዳው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (ዘፍ. 6፥3)፤ መንፈስ ቅዱስ በተለየ ሁኔታ ወደ ምድር የወረደው ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት በጴንጠቆስጤ ቀን እንደሆነ ከአሁን በፊት ተረድተናል። መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በምድር ላይ የሚቆየው አማኞች ወደ ሰማይ እስከሚነጠቁ ድረስ ነው። ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ተገኝቶ አሁን እንደሚያደርገው ክፋትን አይከላከልም።

## የመጀመሪያው አውሬ።

በራእይ 13፥1–7 ስለ ሌላ ታላቅ የዓለም መሪ እናነባለን። በዚሁ ምዕራፍ ሌላ አውሬ ስለተጠቀሰ ይኸኛው «የመጀመሪያው አውሬ» የሚል ስም ተሰጥቶታል። ይህ አውሬ የሚወጣው ከባሕር ነው (ራእ. 13፥1)፤ ባሕር የከፋው የአረማውያን ሕዝብ ምሳሌ ነው (ኢሳ. 57፥20)፤ የመጀመሪያው አውሬ አረማዊ ነው ማለት ነው። ይህ አውሬ ሰባት ራሶች፣ ዐሥር ቀንዶች፣ ዐሥር ዘውዶች ይኖሩታል። በዳንኤል 7፥7 የተጠቀሰው አራተኛው አውሬ ዐሥር ቀንዶች ነበሩት። ዘንዶው ደግሞ ሰባት ራሶች፣ ዐሥር ቀንዶች፣ ሰባት ዘውዶች ይኖሩታል (ራእ. 12፥3)፤ ስለዚህ የመጀመሪያው አውሬ እንደ አራተኛው ንጉሥ ማለትም እንደ ሮም ንጉሥ ይሆናል። በሰይጣንም ይመስላል። ደግሞም በዳንኤል 7፥3–6 በተጠቀሱት ሦስት መንግሥታት የሚመሰሉትን ሦስቱን አውሬዎች ይመስላል። የመጀመሪያው አውሬ ዳንኤል እንደጠቀሳቸው ነገሥታት ዓለምን የሚገዛ ታላቅ አረማዊ ንጉሥ ይሆናል።

የመጀመሪያው አውሬ ምን ያደርጋል? ዮሐንስ በአውሬው ሰባት ራሶች ላይ ክፉ ስም አይቶ ነበር (ራእ. 13፥1)፤ ይህም የሚያመለክተው የመጀመሪያው አውሬ እግዚአብሔርን በግልጥ እንደሚቃወምና እንደሚሰደብ ነው (ራእ. 13፥5–6)፤ እግዚአብሔርን ይጠላል። የእግዚአብ ሔርንም ሕዝብ ይቃወማል። ስጥቂት ጊዜም ያሸንፋቸዋል (ራእ. 13፥7)፤ ይህ የመጀመሪያው አውሬ ሰባት ቀንዶች የነበሩትን አራተኛውን ንጉሥ ይመስላል (ዳን. 7፥7)፤ ከቀንዶቹም



አንዱ በእግዚዘብሔር ላይ ታላላቅ የስድብ ቃሎችን ተናገረ (ዳን. 7፥8፥25)። ይህም ትንሽ ቀንድ እግዚአብሔር መጥቶ እስኪያድናቸው ድረስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ አስጨነቀ (ዳን. 7፥21–22)፤ ስለዚህ በራእይ 13 የተጠቀሰው የመጀመሪያው አውሬ በዳንኤል 7 እንደተጠቀሰው እንደ ትንሹ ቀንድ ነው ማለት ነው። የመጀመሪያው አውሬ ይህን ሁሉ ነገር ለማድረግ ሥልጣን የሚያገኘው ከየት ነው? ከሰይጣን ወይም ከዘንዶው መሆኑ ግልጥ ነው (ራእ. 13፥2)፤ የመጀመሪያው አውሬ ዘንዶውን እንደሚመስል ተረድተናል። ሰይጣን እግዚአብሔርን መምሰል ፈልጎ ነበር (ኢሳ. 14፥13–14)፤ እዚህ ላይ ሰዎች እንደሚያመልኩት እናነባለን። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሚያምኑት በቀር በዓለም ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉ የመጀመሪያውን አውሬ ያመልካሉ (ራእ. 13፥3፤ 4፥6)፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያው አውሬ ይህን በማድረግ ብዙ እንዲቆይ እግዚአብሔር አይፈቅድለትም። የመጀመሪያው አውሬ ሥልጣን የሚኖረው ስሦስት ዓመት ተኩል ወይም ለአርባ ሁለት ወሮች ብቻ ነው (ራእ. 13፥5)።

## ሁለተኛው አውሬ።

በራእይ 13፥11–16 ስለ ሌላ ታላቅ የዓለም መሪ እናነባለን። ሁለተኛው አውሬ የሚወጣው ከምድር ነው (ራእ. 13፥11)፤ የመጀመሪያው አውሬ የሚወጣው ከባሕር እንደሆነና ምሳሌነቱም ለአረማውያን እንደሆነ ተረድተናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ምድር ወይም መሬት የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። ስለዚህ ሁለተኛው አውሬ አይሁዳዊ ነው ማለት ነው። ሁለተኛው አውሬ እንደ በግ ሁለት ቀንዶች ይኖሩታል። በዮሐንስ ራእይ «በግ» የሚለው ቃል 29 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። ከዚህ ከራእይ 13፥11 በቀር ሌሎቹ ሁሉ የሚያመለክቱት ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ይህ ሰው በግ ስለሚመስል ብዙ ሰዎች «ክርስቶስ ነው» ይላሉ። ነገር ግን የሚናገረው እንደዘንዶው ነው። ንግግሩም ማንነቱን ይገልጥበታል (ማቴ. 7፥15–20)፤ በልባችን ያለውን የሚያሳየው ቃላችን ስለሆነ በንግግራችን መጠንቀቅ ያስፈልገናል። እስበስዚያ ከአፋችን በሚመጣው ክፉ ቃል ይፈርድብናል (ሉቃ. 6፥45፤ ማቴ. 12፥36–37)፤ ሁለተኛው አውሬ እንደ መጀመሪያው አውሬ ያለ ሥልጣን ይኖረዋል (ራእ. 13፥12)፤ የመጀመሪያው አውሬ ሥልጣኑን የሚያገኘው ከሰይጣን ነው ብለናል (ራእ. 13፥2)፤ የመጀመሪያውን አውሬ ሰዎች ያመልኩታል (ራእ. 13፥4–6)፤ ታዲያ ሰዎች የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያመልኩ የሚያግባባቸው ይህ ሁለተኛው አውሬ ነው (ራእ.

13፥12)፤ ሁለተኛው አውሬ በሰይጣን ኃይል ብዙ ተአምራት ያደርጋል። ብዙ ሰዎችንም ያታልላል (ራእ. 13፥13–14)። በእነዚህ በሁለት ሥራዎቹ ምክንያት ሁለተኛው አውሬ የዓመፅን ሰው ይመስላል (2ተሰ. 2፥9–10)፤ እግዚአብሔር ምስል እንዳናበጅ ወይም ጣዖት እንዳናመልክ አዞናል (ዘጸ. 20፥4–5)፤ ነገር ግን ሁለተኛው አውሬ ሰዎች የመጀመሪያውን አውሬ ምስል እንዲያበጁና እንዲሰግዱለት ያስገድዳቸዋል (ራእ. 13፥14–15)፤ ይህም ምስል መተንፈስና መናገር ይችላል። የማይሰግዱለትንም ሰዎች ይገድላል።

## የአውሬው ምልክት

ሁለተኛው አውሬ ሰዎች የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያከብሩ ሌላ የሚያደርገው ነገር አለ። በቀኝ እጃቸውና በግምባራቸው ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል። ይህ ምልክት በሀብታሞችም በድሆችም ላይ ይሆናል። ምክንያቱም ማንም ሰው ይህ ምልክት ከሌለው ምንም ነገር ሊገዛም ሆነ ሊሸጥ አይችልም። ነገር ግን ይህን ምልክት መቀበል የማይፈልጉት እውነተኞች አማኞች ብቻ ናቸው። ምልክቱም የመጀመሪያው አውሬ ስም ወይም የእርሱ ቁጥር ይሆናል። የመጀመሪያውን አውሬ ስም አናውቅም። ቁጥሩ ግን 666 ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ቁጥሮች የተለየ ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ ሰባት የፍጹምነት ወይም የትክክለኛነት ቁጥር ነው። ስድስት የሰው ቁጥር ነው። ምክንያቱም ሰው እግዚአብሔር የሚፈልግበትን ነገር ሁልጊዜ አያሟላም። ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት ለመግጠም ይተባበራሉ (ራእ. 19፥19)፤ የዓመፅ ሰው በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይቀመጣል። ሰዎችም ያመልኩታል። እንግዲህ 666 እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ሰዎች የሚያመስክት ቁጥር ነው (መዝ. 2፥2–3)፤ ሁለተኛው አውሬ ሰዎች ይህን ምልክት እንዲቀበሉ ያደርጋል። ሰዎችንም በአንድነት አከማችቶ ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት እንዲገጥሙ ያደርጋል። በራእይ 13 የተጠቀሱት ሁለቱ አውሬዎች መጨረሻቸው ምን ይሆናል?

በራእይ 16፥13 እና 20፥10 ስለ ዘንዶው ስለ አውሬውና ስለ ሐሰተኛው ነቢይ እናነባለን። በራእይ 19፥20 ሐሰተኛው ነቢይ ተአምራትን እንደሚያደርግና የአውሬውን ምልክት እንዲቀበሉና ለአውሬው ምስል እንዲሰግዱ ሰዎችን እንደሚያስት እንረዳለን። በራእይ 13 የምናገኘውም ይህንኑ ነው። ስለዚህ ሁለተኛው አውሬ ሐሰተኛው ነቢይ እንደሆነ እንረዳለን። ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ከመጀመሪያው አውሬ ጋር ወደ እሳት ባሕር ይጣላል። ሁለተኛው



አውሬ በግ እንደሚመስልና ሰዎች መሢሑ ነው ብለው እንደሚቀበሉት ተረድተናል። ነገር ግን ንግግሩ የሰይጣን ንግግር ይሆናል። ከዚህም የምንረዳው ሁለተኛው አውሬ የክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም ሐሰተኛው መሢሕ እንደሆነ ነው። ወደ ፊት ታላላቅ መሪዎች እንደሚመጡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብበናል። ሁሉም የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንደሚሆኑም ተመልክተናል።

1/ በራሱ ሥልጣን የሚመጣውን አይሁዳውያን ይቀበሉታል።
2/ የክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም ሐሰተኛ መሢሕ የአይሁዳውያን አዳኝ ነኝ ብሎ ይገለጣል።
3/ ሐሰተኛው ነቢይ ሰዎችን በአንድነት ሰብስቦ በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እንዲያደርጉ ያነሣሣቸዋል።
4/ የዓመፅ ሰው በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይቀመጣል። ሰዎችም ያመልኩታል።
5/ የመጀመሪያው አውሬ የእግዚአብሔርን ሰዎች ያስጨንቃል። ሌሎች ሰዎች ግን ያመልኩታል።
6/ ሁለተኛው አውሬ ብዙ ተአምራት ያደርጋል። ሰዎች የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያመልኩ ያስገድዳል። አይሁዳውያን የክርስቶስን ተቃዋሚ ወይም ሁለተኛውን አውሬ ወይም ሐሰተኛውን ነቢይ ይቀበላሉ። እርሱም የሐሰተኛይቱ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ፊት የሚመጣው ሃይማኖት ታላቅ መሪ ይሆናል። ዛሬ «አንድ የዓለም ቤተ ክርስቲያን ይኑር» የሚሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለእርሱ የሚያዘጋጁ ይመስላሉ።

የመጀመሪያው አውሬ ወደ ፊት የሚደራጀው የዓለም መንግሥት ታላቅ መሪ ይሆናል። በብዙ መንገድ የዓመፅን ሰው ይመስላል። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ የዓመፅን ሰው ያጠፋዋል። አውሬውንም ከነሕይወቱ ወደ እሳት ባሕር ይጥለዋል (2ተሰ. 2፥8፤ ራእ. 19፥20)።

# ክፍል 10
## የግማሽ ሳምንት መከራ

አሁን ደግሞ ብርቱ መከራ ስለሚሆንበት ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን። ታላቅ መከራ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ለመንገሥ ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት ነው። ስለ ታላቁ መከራ ዳንኤል በጥቂት ጽፎአል። ትንሹ ቀንድ የትዕቢት ቃል እየተናገረ ይመጣል። ከእግዚአብሔርም ሕዝብ ጋር ለሦስት ዓመት ተኩል ይዋጋል (ዳን. 7፥20–21፥ 26፥26)፤ በመጨረሻዎቹ ቀናት አስፈሪ ንጉሥ ይነሣል። ከእግዚአብሔርም ቅዱስ ሕዝብ ብዙዎችን ያጠፋል

(ዳን. 6፥23–24)፤ ጌታ ኢየሱስም በአይሁዳውያን ላይ ስለሚመጣው ስለዚህ ታላቅ መከራ ነግሮናል (ማቴ. 24፥9–22)፤ ደግሞም ስለ ታላቁ መከራና ስለ ጥፋት ርኩሰት ቀደም ብለን ተምረናል። ይህ ጊዜ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል (ዳን. 12፥1)፤ ጌታ ኢየሱስ በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የታላቅ መከራና ችግር ጊዜ እንደሚሆን ተናግሮአል (ማቴ. 24፥21)፤ የዮሐንስ ራእይ ስለ ታላቁ መከራ በሰፊው ያስረዳናል። በምዕራፍ 2 እና 3 በቤተ ክርስቲያን ዘመን የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚሆንም ቀደም ብለን በክፍል 6 ተረድተናል። እንዲሁም ከምዕራፍ 19 እስከ 21 ያለውንም አሳብ ተመልከተን ስለ ጌታ ዳግም ምፅአትና ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ተምረናል (ክፍል 7 ይመልከቱ)፤ ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 18 ያለው አሳብ ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላና ጌታ በኃይልና በክብር ከመምጣቱ በፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ያስረዳናል። በእነዚህ ምዕራፎች ስለ ታላቁ መከራ ምን እንማራለን? በመጀመሪያ ምዕራፍ 4 እና 5 ስለ መንግሥተ ሰማያት የሚሰጡትን ምሳሌ እንመለከት። በምዕራፍ 6፥1–17 እና በምዕራፍ 8፥1 ደግሞ ሰባቱ ማኅተሞች ከተፈቱ በኋላ ምን እንደሚሆን እናነባለን። በምዕራፍ 8፥6 እስከ ምዕራፍ 9፥21 እና 11፥15–18 ሰባት መላእክት ሰባት መለከቶች ይነፋሉ። በዚያን ጊዜ አሠቃቂ ነገሮች ይሆናሉ። በምዕራፍ 16 ግን ሰባት መላእክት ሰባቱን ጽዋዎች በምድር ላይ ሲያፈሱ እናነባለን። ሰባቱ ጽዋዎች የእግዚአብሔር ቁጣ ምሳሌ ናቸው። ይህም ከሁሉ የከፋ ጊዜ ይሆናል። እንግዲህ በአጠቃላይ፦

በምዕራፍ 2 እና 3 በአጭሩ የሚያስረዱት ስለ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ታሪክ ነው።
በምዕራፍ 4 እና 5 የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ።
በምዕራፍ 8 እና 7 ስድስት ማኅተሞች ይፈታሉ።
በምዕራፍ 8 እና 8 ሰባተኛው ማኅተም ይፈታል። ስድስት መላእክት መለከት ይነፋሉ።
ምዕራፍ 13 አውሬውና የክርስቶስ ተቃዋሚ።
ምዕራፍ 18 ሰባት መላእክት የእግዚአብሔር ቁጣ መግለጫ የሆኑትን ሰባት ጽዋዎች ያፈሳሉ።
ምዕራፍ 18–21 የጌታ መምጣትና የወደፊት ሁኔታ።

## ሰባቱ ማኅተሞች

ዮሐንስ እንደ ፖስታ በሰባት ማኅተሞች የታሸገ አንድ መጽሐፍ በሰማይ አየ። ማኅተሞቹን ሊፈታ የሚችለው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው (ራእ. 8፥1–2)፤ ጌታ ሦስት ማኅተሞች በፈታ ጊዜ በፈረስ የሚጋልቡ



ሰዎች መጡ። የመጀመሪያው ድል ነሺ ሆኖ ከድል ወደ ድል ለመሄድ ወጣ (ራእ. 6፥2)፤ ሁለተኛው በምድር ላይ ጦርነት አመጣ (ራእ. 6፥3–4)፤ ሦስተኛው ረሀብ አመጣ፤ ለሰዎች በቂ ምግብ አልተገኘም (ራእ. 6፥5–6)። አራተኛው የምድር አንድ አራተኛ ሰው ለመግደል ሥልጣን ነበረው (ራእ. 6፥7–8)፤ ብዙ አማኞች ተገደሉ። ጌታ አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እስኪበቀልላቸው ድረስ ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለባቸው ጠየቁ (ራእ. 6፥9–11)፤ ጌታ ስድስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ነገሥታትና ገዥዎች በጣም ፈሩ፤ ምክንያቱም የጌታ ቁጣ ቀን በቶሎ እንደሚመጣ ተረድተው ስለነበር ነው።

## የመጀመሪያዎቹ አራት መለከቶች

ጌታ ሰባተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ የሰባቱ መለከቶች ተራ ተጀመረ (ራእ. 8፥1–6)፤ መለከቶቹ የባሰ ችግር በምድር ላይ አመጡ። የሰባቱ ማኅተሞች ጊዜ የማቴዎስ ሃያ አራትን የመጀመሪያ ክፍል ይመስላል፤ እርሱም «የምጥ ጣር መጀመሪያ» የተባለው ነው። የመለከቶቹና የጽዋዎቹ ጊዜ የማቴዎስ ሃያ አራትን ሁለተኛ ክፍል ይመስላል፤ እርሱም «ታላቁ መከራ» የተባለው ነው። የመጀመሪያዎቹ አራት መላእክት መለከታቸውን በየተራ ይነፋሉ (ራእ. 8፥7–12) ።

1/ የዛፎች አንድ ሦስተኛ ይቃጠላል።
2/ የዓሣዎች አንድ ሦስተኛ ይሞታል።
3/ የወንዞች አንድ ሦስተኛ ወደ መራር መርዝ ይለወጣል።
4/ የቀን አንድ ሦስተኛ ያለ ብርሃን ይሆናል።

## አምስተኛው መለከት

አራተኛው መልአክ መለከቱን ከነፋ በኋላ አንድ ንስር «የሚቀሩት ሦስት መላእክት መለከታቸውን ሲነፉ በምድር ላይ በጣም አሠቃቂ ነገር ይሆናል» ብሎ ተናገረ (ራእ. 8፥13)፤ አምስተኛው መልአክ መለከት ሲነፋ ሰዎችን ለአምስት ወር የሚያሠቃዩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አንበጦች መጡ። አንበጦቹ የሚወጡት ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ነው (ራእ. 8፥1–3)፤ የንጉሣቸው ስም አጥፊ የተባለው ነው (ራእ. 8፥11)፤ በራእይ 8 የተጠቀሱት አንበጦች የርኩሳን መናፍስት ወይም የአጋንንት ምሳሌዎች ናቸው (ሉቃ. 8፥31)፤ እነዚህ አጋንንት በታላቁ መከራ ጊዜ ሰዎችን ለአምስት ወር ያሠቃያሉ ማለት ነው።

## የመጨረሻዎቹ ሁለት መለከቶች

ስድስተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ ሌሎች ሁለት መላእክት ይለቀቃሉ (ራእ. 9፥13–19)፤ እነዚህ መላእክት ለዚህ የተለየ ጊዜ የተዘጋጁ ናቸው። ሥራቸውም ከዓለም ሰዎች አንድ ሦስተኛውን መግደል ነው። ምናልባት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሲሞቱ የቀሩት ሰዎች ከኃጢአታቸው ይመለሳሉ ብለን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ አይሆንም (ራእ. 9፥20–21)፤ ጌታ ስድስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ነገሥታትና ገዥዎች ይፈራሉ። ነገር ግን ስድስተኛው መልአክ መለከቱን በነፋ ጊዜ ሰዎች ንስሓ መግባት እምቢ ይላሉ። ከዚህ በኋላ ዮሐንስ የተለያዩ ራእዮች አየ። ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ (ራእ. 11፥15–19)፤ ይህም የሚሆነው ጌታ ከመምጣቱና ዓለምን መግዛት ከመጀመሩ በፊት ነው። የዚያን ጊዜ እንኳ ሰዎች ሊቀበሉት አይዘጋጁም። እግዚአብሔርም የባለ ፍርድ ያመጣባቸዋል።

## አምስት የቁጣ ጽዋዎች

በራእይ 12፥14 እንደምናገኘው ዮሐንስ የተለያዩ ራእዮች አይቶአል። በምዕራፍ 13 ስለ ተጠቀሱት ሁለት አውሬዎች ቀደም ብለን አጥንተናል። በራእይ ምዕራፍ 15 የመጨረሻዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች ስለያዙት ሰባት መላእክት እንመለከታለን። እነዚህ መላእክት በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞሉ ሰባት ጽዋዎች ይሰጡአቸዋል። በምዕራፍ 16 የእግዚአብሔርን ቁጣ በምድር ላይ ሲያፈሱ እንመለከታለን።

1/ የአውሬው ምልክት ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ከባድ ቁስል ይወጣባቸዋል።
2/ ዓሣዎች ሁሉ ይሞታሉ።
3/ ወንዞች ወደ ደም ይለወጣሉ።
4/ ፀሐይ በሙቀትዋ ሰዎችን ታቃጥላለች።
5/ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ይሆናል። በምዕራፍ 16፥1–11 ያለውን ስንመለከት፡–
   ሀ/ ከሦስተኛው ጽዋ በኋላ እግዚአብሔር ይከበራል።
   ለ/ ከአራተኛውና ከአምስተኛው ጽዋዎች በኋላ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔርን ይራገማሉ።
   ሐ/ ከአምስተኛው ጽዋ በኋላ ከሥቃይ ብዛት ሰዎች ምላሳቸውን ያኘካሉ።



## ስድስተኛውና ሰባተኛው ጽዋ

ስድስተኛው መልአክ ጽዋውን ያፈስሳል (ራእ. 16፥12–14)፤ የእስያ ነገሥታት እንዲያልፉ ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ይደርቃል። ርኩሳን መናፍስት ሰዎችን በአንድነት ሰብስበው በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እንዲያነሡ ያደርጓቸዋል። እነዚህ ሰዎች ክርስቶስ ሲመጣ ምን እንደሚሆኑ በክፍል 7 ተረድተናል። በመጨረሻ ሰባተኛው መልአክ ጽዋውን በአየር ላይ ያፈስዋል (ራእ. 16፥17–21)፤ ከአዳም መፈጠር ጀምሮ ያልነበረ ታላቅ የምድር መናወጥ ይሆናል። ታላላቅ የበረዶ ድንጋዮች በሰዎች ላይ ይወድቃሉ። አራተኛውና አምስተኛው ጽዋ በፈሰሰ ጊዜ እንዳደረጉት ሁሉ ሰዎች እግዚአብሔርን ይረግማሉ። «ተፈጸመ» የሚል ታላቅ ድምፅ ከሰማይ ይመጣል።

## ታላቁ መከራ የሚቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

የመከራው ዘመን በሁለት የተከፈለ ነው። የሁለተኛው ከመጀመሪያው የባሰ ነው።

1/ የምጥ ጣር መጀመሪያ ወይም ሰባቱ ማኅተሞች።

2/ ታላቁ መከራ ወይም ሰባቱ መለከቶችና ሰባቱ ጽዋዎች። አንዳንድ ጊዜ ታላቁ መከራ የሚለው ቃል ሁለቱንም የመከራ ክፍሎች ያጠቃልላል። ይሁን እንጂ ሁለተኛው ክፍል ከመጀመሪያው ክፍል በጣም አሠቃቂ ነው። እንዲሁም አውሬው ዓለምን የሚገዛው ስአርባ ሁለት ወሮች ወይም ስሦስት ዓመት ተኩል እንደሆነ ተመልከተናል (ራእ. 13፥5)፤ አውሬው እግዚአብሔርን ይሳደባል። ሰዎች እንዲያመልኩት ያደርጋል፤ የእግዚአብሔርንም ሰዎች ይገድላል፤ እግዚአብሔር ሰዎችን በኃጢአታቸው ምክንያት ይቀጣቸዋል። በራእይ 11 እና 12 ስለ አርባ ሁለቱ ወሮች ጊዜ የሚናገሩ ሌሎች ጥቅሶች አሉ።

1/ አረማውያን ለአርባ ሁለት ወሮች ኢየሩሳሌምን ይይዛሉ (ራእ. 11፥2)።

2/ ሁለቱ የእግዚአብሔር ምስክሮች ለ1260 ቀናት ወይም ለአርባ ሁለት ወሮች ትንቢት ይናገራሉ (ራእ. 11፥3)።

3/ እግዚአብሔር አንዲትን ሴት በበረሃ ለ1260 ቀኖች ወይም ለአርባ ሁለት ወሮች ይንከባከባል (ይህች ሴት የእስራኤል ምሳሌ ነች፤ ሰይጣን እርስዋን የሚያሳድደው ክርስቶስ በእስራኤል በመወለዱ ነው)።

## ሰባ ሳምንቶች

አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ለዳንኤል የሰጠውን ትንቢት እንመለከታለን (ዳን. 9፥24–27)፤ በመጀመሪያ ዳንኤል ያስተዋለው እግዚአብሔር ሰባ ሳምንቶችን ወይም 70X7=490 ዓመቶችን እንዳዘጋጀ ነው። (በመጽሐፍ ቅዱስ ሳምንት ሰባት ቀኖች ወይም ሰባት ዓመቶች ሊሆን ይችላል።) 490 ዓመት ሲፈጸም እርቅንና የዘላለም ጽድቅን እንዲያስገኝ ክርስቶስ መሞት ይገባዋል። ለኃጢአታችን እንደሞተ እናውቃለን (ሮም 5፥10–11)፤ ዓስምን ስመግዛት በሚመጣበት ጊዜም የዘላስምን ጽድቅ እንደሚያመጣ እናውቃለን (ኢሳ. 32፥1፤ ኤር. 23፥5–6)፤ ይህ የ490 ዓመት ወቅት የጀመረው ንጉሡ አርጤክስስ ኢየሩሳሌም እንድትታደስ ፈቃድ በሰጠበት ጊዜ እንደነበረ እግዚአብሔር ለዳንኤል ነግሮታል (ዳን. 9፥25፤ ነህ. 2፥1–8)፤ ሰባው ሳምንት በሦስት የተከፈለ ነው። ሰባት ሳምንት፤ ስድሳ ሁለት ሳምንት አንድ ሳምንት። በዳን. 9፥25 ያለው አሳብ የሚያመለክተው እስከ ክርስቶስ ድረስ ያለው ጊዜ 69 ሳምንት እንደሚሆን ነው። ከስድሳ ሁለት ሳምንት በኋላ ክርስቶስ ይወገዳል (ዳን. 9፥26)፤ በእርግጥም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶአል። በሌላ አነጋገር ከንጉሥ አርጤክስስ ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ 483 ዓመት ነበር። ቀጥሎ ዳንኤል የኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደስን የሚገዳ ንጉሥ እንደሚነሣ ተናግሮአል (ዳን. 9፥26)፤ ጥንታዊ የታሪክ መጻሕፍትን ስናነብ በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም እንደፈረሰች እንረዳለን። ነገር ግን በዳንኤል 9፥27 ያለው አሳብ ይህ የሚመጣው ገዥ ከእስራኤል ጋር ለአንድ ሳምንት ወይም ለሰባት ዓመት የሰላም ውል ይደራደራል። ሦስት ዓመት ተኩል ሲሆን የሳምንቱ ግማሽ ያልቃል። ገዥውም ውሉን አፍርሶ አይሁዳውያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዳያቀርቡ ይከለክላል። ከዚህ በኋላ የጥፋት ርኩሰት ይፈጸማል (ማቴ. 24፥15)፤ ይህ የሚሆነው የዓለሙ ገዥ እስራኤልን ከመቃወሙ በፊት ነው። ይህ ገዥ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ብዙዎቹን የእግዚአብሔር ሰዎች ይገድላል። ስለዚህ ከጥፋት ርኩሰት አንሥቶ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ሌላው ግማሽ ሳምንት ወይም ሦስት ዓመት ተኩል ይፈጸማል። እንግዲህ በዳንኤል



9፥26–27 ያለው አሳብ የሚፈጸመው ገና ወደ ፊት እንደሆነ እንመለከታለን።

እንግዲህ ስለ ታላቁ መከራ የተማርነውን በቅድመ ተከተል ተራ ብንመለከት፡–

1/ አንዱ ሳምንት ወይም ሰባቱ ዓመት ገና ወደ ፊት እንደሆነ እናያለን።
2/ ይህ ሳምንት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ከመነጠቅዋ በፊት አይጀመርም።
3/ የዓመፅ ሰው ወይም አውሬው ከአይሁዳውያን ጋር ውል ይደራደራል።
4/ የምጥ ጣር የተባለው የመከራና የችግር ጊዜ ይጀመራል።
5/ በሰባቱ ዓመት እኩሌታ ላይ አውሬው ውሉን ያፈርሳል።
6/ አውሬው የጥፋት ርኩሰት የተባለ ጣዖት በቤተ መቅደስ ያስቀምጣል፤ አይሁዳውያን በተቻለ ፍጥነት ከኢየሩሳሌም ይሸሻሉ።
7/ አውሬው በቤተ መቅደስ ይቀመጣል፤ ሐሰተኛው ነቢይ ሰዎች ለአውሬው እንዲሰግዱ ያደርጋል።
8/ በሰዎች ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ፍርዱን ያዘንማል።
9/ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ የእግዚአብሔርን ሰዎች ያሳድዳሉ፤ ብዙዎቹንም ይገድላሉ።
10/ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ሰዎችን ሰብስበው በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እንዲያነሡ ያደርጋሉ።
11/ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በቅጽበት ዓይን ያጠፋል፤ አውሬውንና ሐሰተኛውን ነቢይ ከነሕይወታቸው ወደ እሳት ባሕር ይጥላቸዋል።

እንግዲህ እንደ እውነቱ ከሆነ ታላቁ መከራ የሚባለው የሳምንቱ ሁለተኛ ግማሽ ወይም የመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል ነው። በታላቁ መከራ የሚሠቃዩት አይሁዳውያንና አረማውያን ናቸው። የአረማውያን አውሬ አይሁዳውያንን ያሳድዳል። እግዚአብሔር ደግሞ ቁጣውን በአረማውያን ላይ ያፈስሳል (ራእ. 6፥8፤ 9፥18)።

## አይሁዳውያንና አረማውያን የሚሠቃዩት ለምንድን ነው?

1/ አይሁዳውያንና አረማውያን የሚሠቃዩት ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበላቸው እግዚአብሔር ስለሚቀጣቸው ነው።

2/ ሰዎች አውሬውንና የአውሬውን ምስል ስላመለኩ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል (ራእ. 14፥9–10)።

3/ ቅዱሳንን ስለ ገደሉ እግዚአብሔር ሰዎችን ይቀጣል (ራእ. 6፥9–11)።

4/ እግዚአብሔር ሰዎችን በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ፈትኖአቸው ነበር። ነገር ግን ወድቀዋል። እግዚአብሔር ሰዎችን በኃጢአት ሲቀጣ የቀሩት አልተመለሱም። በታላቁ መከራ ጊዜም ቁጣውን ሲገልጥ ሰዎች ይበልጡን እግዚአብሔርን ይራገማሉ (ራእ. 16፥10፤ 11፥14)።

አንዳንድ ሰዎች «ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከራ ውስጥ ወይም በግማሹ ውስጥ ታልፋለች» ይላሉ። ሌሎች ደግሞ «ከቤተ ክርስቲያን ከፊሉ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ከፊሉ በምንግሥተ ሰማያት ይሆናል» ይላሉ። ታዲያ እንዴት ነው ቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ ታልፋለችን? አንዳንድ አማኞች «ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊና ቀዝቃዛ ስለሆነች እግዚአብሔር በመከራው ዘመን ክርስቲያኖችን ይቀጣል። ቤተ ክርስቲያንንም አጽድቶ ለመንግሥተ ሰማያት ያዘጋጃታል» ይላሉ። በእርግጥም ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ሆናለች። በጌታ ሳያምኑ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ሰዎችም በብዛት ይገኛሉ። እውነተኞች ክርስቲያኖች ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ዝግጁ የሆኑት በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ ነው (ዮሐ. 5፥24)፤ ክርስቲያኖች ኃጢአት ባለማቋረጥ የሚሠሩ ከሆነም ወዲያው ይቀጣሉ መከራንም ይቀበላሉ፤ (ዕብ. 12፥5–11)፤ ይህንንም የሚያደርገው ስለሚወዳቸው ነው፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሙሽራ የሚያዘጋጃት በፍቅርና በቃሉ ነው (ኤፌ. 5፥26–27)፤ ስለዚህ በታላቁ መከራ ጊዜ እውነተኞች ክርስቲያኖች ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት ይሆናሉ እንጂ መከራውን አይካፈሉም። እግዚአብሔር መከራው እንዳይደርስብን ቃል የገባልን ለምንድን ነው? ከሌሎች ስለተሻልን ወይም ከሌሎች ይበልጥ እግዚአብሔርን ስለምንወድ ይሆን? አይደለም፤ በጸጋው ብቻ ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ስለ መረጠን ልንታበይ ወይም ልንኮራ አንችልም። ይልቁንም ልናመሰግነውና ልናገለግለው ይገባናል።

አንዳንድ አማኞች ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ግማሽ አካል በመከራው ውስጥ ያልፋል ብለው ያስተምራሉ። ለትምህርታቸውም መደገፊያ ጥቅሶች ያቀርባሉ። ለምሳሌ በሉቃስ 21፥36 ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመከራ ውስጥ ኃይል እንዲያገኙ በጸሎት እንዲተጉ አሳስቦአቸው ነበር። ነገር ግን ይህን የተናገረው ለአይሁዳውያን እንጂ ለክርስቲያኖች አልነበረም። በራእይ 3፥10 ጌታ ኢየሱስ አንዳንድ



አማኞችን ከመከራ እንደሚጠብቃቸው ተስፋ ሰጥቶአል። እነዚህም ታገሡ የሚለውን ትእዛዙን የፈጸሙ ናቸው። ምናልባት ሌሎቹ በመከራ ውስጥ ማለፍ አለባቸው ብለን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ለአማኞች ሁሉ የሰጠው ተስፋ እንዳለ አንዘንጋውም (ራእ. 2፥7–11፤ 3፥5)።

1/ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ሁላችን እንለወጣለን (1ቆሮ. 15፥51)፤ ይህም ማለት ክርስቲያኖችን ሁሉ እንጂ በከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ነን የሚሉትን ብቻ አይደለም።

2/ አንዳንድ ሰዎች መንፈሳውያን ያልሆኑ ክርስቲያኖች በታላቁ መከራ ውስጥ ማለፍ አለባቸው ይላሉ። እንደዚህ ከሆነማ መንፈሳውያን ሳይሆኑ የሞቱት ክርስቲያኖች መቀጣት አለባቸው ወይም በመከራ መንጻት አለባቸው ማለት ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ክርስቶስ ሲመጣ በክርስቶስ አምነው የሞቱ ሁሉ ይነሣሉ ነው (1ተሰ. 4፥16)።

3 አማኞች ጌታን ስላገለገሉ ሽልማት ወይም አክሊል ያገኛሉ። መነጠቅ ግን ጌታን በማገልገል የምንቀበለው ሽልማት አይደለም። እርሱ ባለበት እኛም እንድንሆን ጌታ አባቱን ለምኖልናል (ዮሐ. 17፥24)።

# ክፍል 11
## ወቅታዊ ሁኔታዎች

ደመና ጠቁሮ ስናይ ዝናም መዝነሙን እናውቃለን። ወደ ማታ ሰማይ ቀልቶ ካየን የአየር ጠባዩ ጥሩ እንደሚሆን እንገምታለን። ጠዋት ሰማይ ቀልቶ ካየን «ምናልባት ሳይዘንም አይቀርም» እንላለን። የነፋሱንም አቅጣጫ ተመልክተን «ይሞቃል ወይም ይቀዘቅዛል» እንላለን (ማቴ. 16፥2–3፤ ሉቃ. 12፥54–56)፤ የእግዚአብሔር ነቢይ ካልሆነ በቀር ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር የሚያውቅ የለም። ሆኖም ዛሬ የሚሆኑት ነገሮች ቀጥሎ ለሚሆኑት ነገሮች እንድንዘጋጅ ሊረዱን ይችላሉ፤ ጌታ ለቤተ ክርስቲያኑ መቼ እንደሚመጣ አናውቅም። ነገር ግን ጌታ ለቤተ ክርስቲያኑ ከመጣ በኋላ ወይም ከመነጠቅ በኋላ በመከራው ዘመን ምን እንደሚሆን እናውቃለን። ዓለም በቅርብ ጊዜ ለሚሆነው ነገር እየተዘጋጀች ነው። በክፍል 11 እና 12 ስለ መጨረሻው ጊዜ ወይም ስለ መጨረሻዎቹ ቀኖች የሚያወሱትን አንዳንድ ጥቅሶች እንመለከታለን። ከዚያም በኋላ ከነዚህ ነገሮች

በአሁኑ ወቅት የሚፈጸሙት የትኞቹ እንደሆኑ እናመዛዝናለን። በዚህም ሁኔታ ጌታ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚመጣልን እንረዳለን። ስለ መጨረሻው ቀን ወይም ስለ መጨረሻዎቹ ቀኖች መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን በብዙ ቦታ ተናግሮአል።

1/ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሲነሡ መጨረሻው እንደደረሰ እናውቃለን።

2/ በመጨረሻዎቹ ቀኖች ሰዎች በአማኞች ላይ ያላግጣሉ። ስለ ጌታም ተመልሶ መምጣት ይዘብታሉ (2ጴጥ. 3፥3–4፤ ይሁ. 18)።

3/ በዘመናት መጨረሻ ደኅንነታችን ይገለጣል (1ጴጥ. 1፥5)፤ ይህም የሚሆነው አዳኛችን ሲመጣ ነው።

4/ በመጨረሻው ቀን ጌታ አማኞችን ከሞት ያስነሣል (ዮሐ. 6፥39፥ 40፥ 44፥ 54፤ 11፥24)።

ዛሬ ጌታ ተመልሶ ይመጣል ስንላቸው የሚስቁ ብዙ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች ዓለምን ከችግር እናድናለን እያሉ የሚደነፉትን ሐሰተኛች መሪዎችን ወይም መሢሖችን ይከተላሉ። እነዚህ ነገሮች የሚያመለክቱትን በመጨረሻዎቹ ቀኖች መሆናችንን ነው። በመጨረሻዎቹ ቀኖች መሆናችንን የሚያመለክተው ሌላው ነገር በ1ጢሞቴዎስ 4፥1 የተጠቀሰው ነው። ይኸውም ሰዎች ሐሰተኞችን መናፍስትና አጋንንትን በመከተል እምነታቸውን እንደሚተውና መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚጠሉ ነው። እነዚህ መናፍስት እግዚአብሔርን የማይወዱ ወይም ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ናቸው። የሰይጣን ጭፍራዎች እንደ መሆናቸው መጠን የክርስቶስና የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። ሆኖም የክርስቶስ ጠላቶች መሆናቸውን ለሰዎች አይናገሩም። ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ መስሎ መታየትን ነው የሚመርጠው (2ቆሮ. 11፥13–14)፤ ርኩስ መንፈስን ለይተን የምናውቀው በሚያስተምረው ትምህርት ነው። አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት አያስተምሩም። ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይስማማ ትምህርት መቀበል የለብንም። ርኩሳን መናፍስት የሚናገሩት በአስማተኞችና በጠንቋዮች አማካይነት ነው።

አስማተኞች ወይም አጋንንት ጠሪዎች አንዳንድ ጊዜ "ከሞተ ሰው ጋር እናነጋግራችኋለን" ይሉ ይሆናል። ነገር ግን እነርሱን መስማት አይገባም። እንዲሁም ጠንቋዮችን መጠየቅ ወይም የሚሉትን



መስማት አይገባም (ዘዳ. 18፥10–12)፤ አንዳንድ ጊዜ ርኩስ መንፈስ በሰው ውስጥ ሆኖ ለሰዬው የማያውቀውን ብዙ ነገር ሊያስለፈልፈው ይችላል። በታላቁ መከራ አጋማሽ ላይ ሰይጣንና መልአክቱ በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይታሰራሉ (ራእ. 12፥7–9)፤ አሁን እንኳ ጊዜው አጭር መሆኑን ስለሚያውቅ ሰዎችን እንዲያታልሉ ርኩሳን መናፍስቱን ይልካል። ዛሬ ሠለጠኑ በሚባሉት አገሮች እንኳ ብዙ አስማተኞችና ጠንቋዮች ይገኛሉ። እንዲያውም ቤተ ሰይጣን ሠርተው ሰይጣንን በይፋ የሚያመልኩ ሰዎች እየበዙ ሄደዋል። ይህም የሚያመለክተው በዘመኑ መጨረሻ መሆናችንን ነው።

## በየዘመኑ የነበሩ ቅራኔዎች

በመጀመሪያ እግዚአብሔር መላእክትና መናፍስትን ፈጠረ። ሰይጣን በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መልአክ ነበረ። በኋላ ግን ኩራት ተሰማውና እግዚአብሔርን በደለ (ኢሳ. 14፥12–15፤ ሕዝ. 28፥11–16)፤ እግዚአብሔር ወዲያውኑ በሰይጣን ላይ ፈረደበት። ሰይጣንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ።

1/ በዔደን ገነት ሔዋንን አስቶ ኃጢአት እንድትሠራ አደረጋት (ዘፍ. 3)።

2/ ቃየል ወንድሙን አቤልን እንዲገድል የገፋፋው ሰይጣን ነው (1ዮሐ. 3፥12)።

3/ ኢዮብን በእግዚአብሔር ፊት የወነጀለና አሁንም እኛን የሚከስ ሰይጣን ነው (ኢዮ. 1፥9–11፤ ራእ. 12፥10)።

4/ ሰይጣን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳ ሊፈትን ሞክሮአል (ማቴ. 4፥1–11፤ ሉቃ. 4፥1–13)።

5/ በታላቁ መከራ ዘመን በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ሁሉ የሚጠላና እስራኤላውያንንም የሚያሳድድ ሰይጣን ነው (ራእ. 12፥13)፤ ሰይጣን ሥልጣኑን ለአውሬው ይሰጣል። አውሬውም የእግዚአብሔርን ሰዎች ይገድላል (ራእ. 13፥4–7)።

6/ በመጨረሻ በእሳት ባሕር ውስጥ ይጣላል። እዚያም ለዘላለም ይኖራል (ራእ. 20፥10)።

ርኩሳን መናፍስት ሰዎችን እያታለሉ፤ ከእግዚአብሔር ያርቁአቸዋል። ሰዎችም በእግዚአብሔር ማመናቸውን ትተው እነዚህን ሐሰተኞች መናፍስት ያምናሉ (1ጢሞ. 4፥1)፤ በመጨረሻዎቹ ቀኖች ሰዎች ሃይማኖተኞች ይሆናሉ። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ (2ጢሞ. 3፥1–5)፤ ሰይጣን ሰዎችን ለመጨረሻው ዓመፅ ያዘጋጃቸዋል። የዓመፅ ሰው ይገለጣል። ሕዝቦች በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እንዲያነሡ ያደርጋል (2ተሰ. 2፥3)፤ ዛሬ በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እውነተኞች ክርስቲያኖች አሉ። እነዚህ ሁሉ በመገለጥ ጊዜ ጌታ ሲጠራቸው ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። በምድር ላይ የሚቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ግን ከክርስቶስ ስም ይርቃሉ። ይህም ክህደት የሚባለው ነው። አሁን ብዙ ሰዎች «ክርስቲያኖች ነን» ይላሉ። ከመነጠቅ በኋላ ክርስቶስን የማይቀበል ሃይማኖት አባሎች ይሆናሉ። አሁን ደግሞ አስቲ ራእይ ምዕራፍ 17ትን በሙሉ በዝግታ እንመልከተው። ይህ ምዕራፍ የሚነግረን ከመከራው ዘመን በኋላ እግዚአብሔር ስለሚፈርድባት አንዲት አመንዝራ ሴት ነው። አመንዝራ በገንዘብ የምትደሰል ክፉ ሴት ናት (1ቆሮ. 8፥16)፤ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንደክርስቶስ ሙሽራ ናት (ኤፌ. 5፥25–27፤ ራእ. 21፥2–9፤ 22፥17)፤ ስለዚህ ታላቂቱ አመንዝራ ሴት የሐሰተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። እርስዋም «ታላቂቱ ባቢሎን» የተባለችው ናት። ታላቂቱ ባቢሎን ወይም ታላቂቱ አመንዝራ ሴት የሐሰተኞች ሃይማኖቶች ሁሉ ምሳሌ ናት፡–

1/ እርስዋ የተበላሸች ብትሆንም በጣም ሀብታም ናት (ራእ. 17፥4)፤ ብዙ ጊዜ ሐሰተኛ ሃይማኖት የሚያስተምሩ ሀብታሞች ናቸው። ምክንያቱም ከአባሎቻቸው ገንዘብ እየተቀበሉ የብልግና ሕይወት እንዲኖሩ ይፈቅዱላቸዋል።

2/ የሐሰተኞች ሃይማኖቶች መሪዎች ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይጠላሉ። ብዙዎችንም ይገድላሉ(ራእ. 17፥6፤ 16–24)።

3/ የሐሰተኞች ሃይማኖቶች መሪዎች ዘወትር የመንግሥት ሥልጣን መጨበጥ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ታላቂቱ አመንዝራ በዓስም ሕዝቦች ውሃዎች ላይ ተቀምጣ ትታያስች። በዓስም ነገሥታትም ላይ ሥልጣን ታሳያለች (ራእ. 17፥15–18)፤ እውነተኞች ክርስቲያኖች ከሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ቢደባለቁ ግን ዋጋቸውን ያገኛሉ። በራእይ ምዕራፍ 17 እንደምንመለከተው ከሆነ ታላቂቱ አመንዝራ በመጀመሪያ ክብርና ግርማ ይኖራታል። እንዲያውም የዓለም መንግሥታትን በሚገዛው በመጀመሪያው አውሬ ላይ ሥልጣን



ይኖራታል (ራእ. 17፥3)፤ የከፍተኛ ሥልጣን ምልክት የሆነ ልብስ ትለብሳለች (ራእ.17፥4)፤ ነገር ግን የመጀመሪያው አውሬ ዐሥር ቀንዶች በታላቂቱ አመንዝራ ሴት ላይ በጠላትነት ይነሣሣል (ራእ. 17፥16)፤ እነዚህ ዐሥር ቀንዶች የዐሥር ነገሥታት ምሳሌዎች ናቸው፤ እግዚአብሔር በታላቂቱ አመንዝራ ሴት ላይ ይፈርዳል፤ ነገሥታትም እንዲገድሉአት ያደርጋል (ራእ. 17፥17)፤ ሌሎች ነገሥታት ትምህርቷን ተቀብለው ስለነበር ለባቢሎን ያለቅሳሉ፥ ያዝናሉም (ራእ. 18፥9)፤ ነጋዴዎች በሃይማኖታቸው እያሳበቡ ከብረው ስለ ነበር ያለቅሳሉ፥ ያዝናሉም (ራእ. 18፥11)፤ ነገር ግን በሰማይ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ታላቂቱ አመንዝራ በደረሰባት ነገር ደስ ይላቸዋል። ምክንያቱም እርስዋ ብዙዎቹን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለገደለች ነው (ራእ. 19፥1–2)፤ ታላቂቱ አመንዝራ የሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያንና የሃይማኖት ሁሉ ምሳሌ ነች። የመጀመሪያው አውሬ በእርስዋ ላይ በጠላትነት ይነሣል፤ ያጠፋታልም። ዛሬ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች በዓለም ላይ አሉ። ነገር ግን የሚጓዙት በአንድነት ነው። ክርስቲያኖች ነን የሚሉትም ወገኖች በሦስት ታላላቅ ክፍል ተመድበው የታወቁት ናቸው። ዛሬ ሰይጣን እነዚህን የተለያዩ ክፍሎች አንድ ለማድረግ ይጥራል። በመጀመሪያ ተሐድሶ አገኘን የሚሉትን ቀጥሎም ክርስቲያን የተባሉትን ሁሉ፥ ከዚያም ሌሎችን ሃይማኖቶች ይጨምራል። ስምሳሌ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው የተለየ እምነት አለው። እንግዲህ ሰይጣን እንዴት አድርጎ አብያተ ክርስቲያናትን አንድ እንደሚያደርጋቸው የሚያስደንቅ ነው። እስከ አሁን የሆነው እንዲህ ነው።

1/ የሰይጣን አገልጋዮች «መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እውነት አይደለም። ሐሰቶችና ስሕተቶች በውስጡ ይገኛሉ» ብሰው ማስተማር ጀመሩ። በዚህ ዓይነት ሰዎች በእውነት የሚታመኑበት ነገር የላቸውም ማለት ነው።

2/ ምን ማመን እንዳለብን የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ካልሆነ ስለ ምንም ነገር እርግጠኞች ልንሆን አንችልም። ስለዚህ የሰይጣን አገልጋዮች "ሰውን ለመርዳት እስከ ሞከርህ ድረስ የትኛውንም ነገር ብታምን ምንም አይደስም" ይላሉ። የተሰያዩ አብያተ ክርስቲያናት ይህን አሳብ ተቀብለው አንድ መሆን ጀምረዋል።

3/ እነዚህ ሰዎች አንድ መሆን አለብን የሚሉት በዮሐ. 17፥21 ያለውን አሳብ መርሖ በማድረግ ነው። ነገር ግን ጌታችን ይህን

ጸሎት የጸለየው እርሱ ከአባቱ ጋር አንድ በሆነው ዓይነት ደቀ መዛሙርቱም አንድ እንዲሆኑ ነው። ይህም አንድነት መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ ወይም ድርጅታዊ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። አብያተ ክርስቲያናት አንድ ስለመሆን ማውራት ከመጀሩ ከስልሳ ዓመት በላይ ሆኖአቸዋል። ብዙ የሃይማኖት ክፍሎች አንድ ትልቅ የሃይማኖት ክፍል ለመፍጠር በማሰብ በአንድነት ተጣምረዋል። ይህም እርምጃ «የኢኮኖሚካል እንቅስቃሴ» በመባል የሚታወቀው ነው። እንዲህ ዓይነቱን መጣመር የማይወዱ እውነተኞች ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። ምክንያቱም አንዳንድ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርቶችን ማጣት ስለማይፈልጉ ነው። እነዚህ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። ከዚያ በኋላ ዘመናውያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ክርስቶስ የሌለበት አንድ ትልቅ የሃይማኖት ክፍል ለማቋቋም ይችላሉ። እንግዲህ ሰይጣን እነዚህን ታላላቅ የክርስቲያን ሃይማኖት ክፍሎች አንድ ማድረግ ጀምሮአል ማለት ነው። ክርስቲያኖች ያልሆኑ እንዲያውም ክርስቲያኖችን ሲጠሉና ሲያሳድዱ የኖሩ ሌሎች ሃይማኖቶችም አሉ። በመጨረሻዎቹ ቀኖች አሠቃቂ ነገሮች እንደሚሆኑ ተመልክተናል። ርኩሳን መናፍስት በብዛት መጥተው ሐሰት ያስተምራሉ። ሰዎች ከእውነት ተንሸራተው በመውደቅ ክርስቶስ የሌለበት ታላቅ ሃይማኖት ይመሠርታሉ። እነዚህ ነገሮች በመጀመር ላይ መሆናቸውን የዛሬዎቹን ሃይማኖቶች ይዘት በመመልከት እንረዳለን። ነገር ግን ወደፊት ስለሚመጡት መንግሥታት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምረናል? ስለ መንግሥታት ይዞታ በሚቀጥለው ክፍል እንመለከታለን።

# ክፍል 12
## <u>አንዳንድ ነገሮች መሆን ጀምረዋል</u>

ጌታ ኢየሱስ «እነዚህን ነገሮች መሆን ሲጀምሩ ደኅንነታችሁ እንደቀረበ ዕወቁ» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸዋል (ሉቃ. 21፥28)፤ ዛሬ በሃይማኖቶችና በአብያተ ክርስቲያናት የሚሆነውን ስናይ መጨረሻው የቀረበ ይመስለናል። አሁን ደግሞ ስለ ዓለም መንግሥታት ይዞታ እንመለከታለን። ይህም ማለት የአረማውያንን መንግሥታትና የእስራኤልን መንግሥት ይዞታ ነው።

ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር የለም ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይወዱም። ታዲያ ክርስቲያን ምን



ማድረግ ይገባዋል? መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ለአገርህ መንግሥት ታዘዝ ነው (ሮሜ 13፥1–7)፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የመንግሥት ባለ ሥልጣን ለጣዖት እንዲሰግድ ወይም አንድ እምነቱ የማይፈቅድለትን ነገር እንዲያደርግ ያዘው ይሆናል። በዚህ ጊዜ ጴጥሮስና ሦስቱ ሰማዕታት የተናገሩትን ማስታወስና ለክርስቶስ ለመሠቃየት መዘጋጀት ያስፈልጋል (ሐ.ሥ. 4፥19፤ 5፥29፤ ዳን. 3፥18)፤ እንግዲህ ወደ መንግሥታት ይዞታ እንምጣና በመጀመሪያ የዘመናትን አከፋፈል ሁኔታ እንመልከት። የዘመናት አከፋፈል ወይም ዲስፔንሴሽን የሚለው ቃል እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ከሰዎች ጋር የተገናኘበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሕጉን ለእስራኤል ሰጥቶ ስለነበር «የሕግ ዘመን» ብለን መናገር እንችላለን። የሕግ ዘመን የቆየው ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. 1፥17)፤ አሁን ያለንበት ጊዜ «የጸጋ ዘመን» ነው። ምክንያቱም አሁን እግዚአብሔር ጸጋውን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ገልጦልናል። የጸጋ ዘመን የጀመረው በክርስቶስ ሲሆን የሚያልቀው ደግሞ በመነጠቅ ጊዜ ነው። እስከ አሁን ብዙ ክፍለ ዘመናት ነበሩ። ከመከራው ዘመን በኋላም የሺህ ዓመት መንግሥት ይመጣል። ይህም የመጨረሻው ክፍለ ዘመን መሆኑ ነው። እግዚአብሔር በተለያየ ክፍለ ዘመን በተለያየ ሁኔታ ሰዎችን የሚፈትነው ለምድን ነው? ሰዎች በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ፈቃዱን እንዲፈጽሙ እግዚአብሔር ዕድል ሰጥቶአቸዋል። ሰዎች ግን ይህን ማድረግ የቻሉበት ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በተለያየ ክፍለ ዘመን በተለያየ ሁኔታ ሰዎችን ይፈትናል። ሰዎች ግን በመደጋገም ይወድቃሉ። ይህም የሚያሳየው ሰዎች አዳኝ የሚያስፈልጋቸው መሆኑንና በራሳቸው ሥራ ደኅንነት ሊያገኙ ያለመቻላቸውን ነው። አንዳንድ ሰዎች "እግዚአብሔር ሁለተኛ ዕድል ለምን አይሰጠንም?" ይሉ ይሆናል። ወይም ሰዎች ኃጢአት የሚያደርጉት ያለ ምክንያት አይደለም። የሚበሉት በማጣት ይሆናል። ጦርነትም የሚያደርጉት ተጨማሪ መሬት ስለሚያስፈልጋቸው ይሆናል ይላሉ። እግዚአብሔር ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልስ የሚሰጠው በሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ ነው። በዚያን ጊዜ በዓለም ላይ ሰላም ይሆናል። በቂ ምግብም ይኖራል። ሕግ የሚጥስ ካለ ወዲያውኑ ይቀጣል። ሰዎች ኃጢአት ምን እንደሆነና ኃጢአትም ማድረግ እንደማይገባቸው ያውቃሉ። ታዲያ የዚህ ሁሉ ውጤት ምን ይሆናል? ሰዎች እግዚአብሔርን ይወዱ ይሆን? ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ይፈታል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከእርሱ ጋር ተባብረው እግዚአብሔርን ይቃወማሉ (ራእ. 20፥7–9)፤ ይህም የሚያሳየው ሁኔታዎች ቢሻሻሉ እንኳ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደማይወዱ ነው። እንዲያውም በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ የሚያነሣሣቸውን መሪ

ይከተላሉ። በዚህም የምንረዳው ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ዳግመኛ መወለድ እንዳለባቸው ነው።

ጌታ የሚመጣው በሁለት የተለያዩ መንገዶች መሆኑን ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ተረድተናል። እነርሱ «በመጀመሪያ ሲመጣ ሰዎች ይቃወሙታል፤ በኋላ የሚመጣው ግን በኃይልና በክብር ነው» ብለው ነበር። በመጀመሪያ መምጣቱና በኋላ መምጣቱ መካከል ረዥም ጊዜ እንዳለ አሁን ዓይተናል። እንዲሁም በአራተኛው መንግሥትና በመጨረሻው ዘመን መካከል ያለው ጊዜ ረዥም ነው። ክርስቶስ መጥቶ እስኪዋጃቸው ድረስ ትንሹ ቀንድ የእግዚአብሔርን ሰዎች እንደሚያሰጨንቅ ዳንኤል አስቀድሞ ተናግሮአል (ዳን. 7፥19–22)፤ ይህም ትንሽ ቀንድ የተባለው የአራተኛው መንግሥት የሮም ንጉሥ ነው። እርሱ በዓለም ላይ የሚሆነው በመከራው ዘመን ነው። ስለዚህ አራተኛው መንግሥት በመጨረሻዎቹ ቀኖች እንደገና ብርቱ ይሆናል ማለት ነው። በዳንኤል ትንቢት ከተጠቀሱት አራት መንግሥታት መካከል ከሁሉም የሚበልጠው የሮም መንግሥት ነበር። አብዛኞዎቹ የአውሮፓ አገሮችና በሜዲተራኒያን ባሕር ዙሪያ ያሉት አገሮች በዚህ መንግሥት ሥር ነበሩ። ከክርስቶስ ዘመን 500 ዓመታት በኋላ የሮም መንግሥት ኃይሉ ደከመና ወደቀ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአውሮፓ አገሮችን አጠቃሎ የሚያስተዳድር አንድም መንግሥት አልተገኘም። ዛሬ ዐሥር የአውሮፓ አገሮች በከፊል ተጣምረዋል። ሆኖም ሁሉንም አጠቃሎ የሚያስተዳድር አገር የለም። አራተኛው መንግሥት የዐሥር ነገሥታት ምሳሌ የሆኑ ዐሥር ቀንዶች እንደነበሩት እናስታውሳለን (ዳን. 7፥23–24)፤ ትንሹ ቀንድ ከነዚህ ዐሥር ነገሥታት ሦስቱን ያሸንፋል። ዐሥሩንም በበላይነት ያስተዳድራል። ይህም የሚሆነው ጌታ በኃይልና በክብር ከመምጣቱ በፊት ባለው በመከራው ዘመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናት መጨረሻ ታላላቅ የአረማውያን መንግሥታት እንደሚነሡ ይናገራል። ጎግ የተባለ መሪ የማጎግን፥ የሞሳህን፥ የቶቤልን ሕዝብና የሌሎችንም መንግሥታት ሕዝብ አስተባብሮ እስራኤልን ለመውጋት ይነሣል (ሕዝ. 38፥1–6)፤ ማጎግ የሚለው ስም የሚወክለው እንደገና እስራኤልን ለመደምሰስ የሚነሡትን መንግሥታት ሁሉ ነው (ራእ. 20፥8)።

በዳንኤል 11፥40 በመጨረሻው ዘመን የሰሜን ንጉሥ የሚባል እንደሚነሣ እናነባለን። በሚልክያስ 5፥5 የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያጠቃ የአሦራውያን ንጉሥ እንደሚነሣ እናነባለን። አሦር ከእስራኤል በስተሰሜን ስለሆነ የሰሜን ንጉሥ የተባለው የአሦር ንጉሥ ሊሆን ይችላል ማለት ነው። በዳንኤል 11፥40 እንደገና ስለ ደቡብ ንጉሥ እናነባለን። ይህም የግብፅ ንጉሥ ነው። በራእይ 16፥12



ከኤፍራጥስ ወንዝ ባሻገር ስላሉ ስለ ምሥራቅ ነገሥታት እናነባለን። እነዚህ አገሮች በአሁኑ ዘመን ካሉት አገሮች የትኞቹ እንደሆኑ ለይተን ማወቅ አንችልም። ሆኖም እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን መንግሥታትን እንደሚቆጣጠርና አሁን የሚሆነውን አስቀድሞ ተናግሮት እንደነበር እንመለከታለን።

እስራኤልስ ምን ትሆናለች? አሁን በእስራኤል ላይ መሆን ስለ ጀመሩት ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረው ነገር አለን? በእርግጥ አለ። የእስራኤል ሕዝብ በመከራው ዘመን በአገራቸው ላይ እንደሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።

1/ አውሬው ለሰባት ዓመት ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን ይገባል ወይም ውል ይፈርማል (ዳን. 9፥27)፤ ይህም የሚያመለክተው እስራኤል በመንግሥትነት እንደምትታወቅ ነው።

2/ እስራኤል በይሁዳ ምድር ይኖራል (ማቴ. 24፥16)።

3/ የእስራኤል መቅደስ በኢየሩሳሌም ይሆናል። አውሬው በመጀመሪያ ሕዝቡ በመቅደሱ ውስጥ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ይፈቅድላቸዋል። በኋላ ግን በመሠዊያው ላይ የጥፋት ርኩሰት በማድረግ መሥዋዕት እንዳያቀርቡ ይከለክላል (ማቴ. 24፥15)።

ክርስቶስ ከተወለደ ከ70 ዓመት በኋላ የሮም ወታደሮች ኢየሩሳሌምንና መቅደሱን አፈረሱ። የእስራኤል ሕዝብም ወደ ሌሎች አገሮች ተሰደደ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለብዙ መቶ ዓመታት ጠበቃቸው። የራሳቸው አገር ስላልነበራቸው ከሌሎች ሕዝቦች ጋር መኖር ግድ ሆኖባቸው ነበር። እ. ኤ. አ. በ1946 ዓ.ም. እስራኤላውያን ከድሮው ምድራቸው አብዛኛውን ክፍል አግኝተው እንደገና መንግሥት ለመሆን በቅተዋል። ይሁን እንጂ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ ኢየሩሳሌምን በሙሉ አልያዙም ነበር። ደግሞም እስከ አሁን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አልቻሉም። ምክንያቱም ቀድሞ ቤተ መቅደስ ባለበት ቦታ «ዶም ኦፍ ዘ ሮክ» የተባለ የእስላሞች መስጊድ ስላለና እርሱን ለማፍረስ የኢንተርናሽናል ሕግ ስለማይፈቅድላቸው ነው። እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ ማየትና የጌታ መምጫ መቃረቡን ማወቅ እጅግ ያስደስታል። ሆኖም ጌታን ስንጠባበቅ በቅድስናና በትጋት የመኖር ግዴታ እንዳለብን እንዘንጋ (2ጴጥ. 3፥11–12)።

አሁን ደግሞ ዳንኤል በጠቀሰው በሰባተኛው ሳምንት አጋማሽ ላይ ወይም በመከራው ዘመን በመጀመሪያው ሦስት ዓመት ተኩል ላይ

ስለሚሆነው ነገር እንመልከት። ዛሬ በዓለም ላይ የሚፈጸሙት ድርጊቶች የሚያመለክቱት ያንኑ ነው።

1/ ጌታ ኢየሱስ ስለ ምጥ ጣር መጀመሪያ አስረድቶአል (ማቴ. 24፥5–8)።

2/ አውሬው ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን ይገባል ወይም ውል ይደራደራል (ዳን. 7፥27፤ 9፥27)፤ ቤተ መቅደስ እንዲሠሩም ይፈቅድላቸዋል።

3/ ጌታ የመጻሕፍቱን ማኅተም ይፈታል። መከራም በምድር ላይ ይጀመራል (ራእ. 6፥1–17)።

እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙት በመከራው ዘመን የመጀመሪያ ግማሽ ላይ በምጥ መጀመሪያ ነው። ዛሬ የሚደረጉት ነገሮች በመከራው ዘመን በበለጠ በከፋ ሁኔታ ይደረጋሉ። በእርግጥ ጌታ በቅርብ ጊዜ ይመጣል። የሚመጣበት ቀን በውል ማወቅ ባይቻልም ተዘጋጅቶ መጠበቅ ያስመሰግናል። አንዳንድ ነገሮች መሆን ጀምረዋል። ስለዚህ ጌታ ቅርብ ስለሆነ ቀና ብለን እንይ!

## ችሎታችሁን ለኩ

እስካሁን በዚህ በትንቢት መግቢያ የተገለጡትን አስፈላጊ ነገሮች ሳታውቁ አልቀራችሁም። ስለዚህ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደምትችሉ እገምታለሁ። የተረሳችሁ ነገር ቢኖር መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ወይም ከዚህ መጽሐፍ የትኛውንም ክፍል ቢሆን ማየት ትችላላችሁ። መልሱን በወረቀት ጽፋችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ወደ ገጽ 65 በመሄድ ማረጋገጥ ትችላላችሁ።

1/ ዳንኤል ነቢይ መሆኑን የተናገረ ማን ነው?
2/ ዳንኤል በሕልሙ ስንት እንስሳት አየ?
3/ እነዚህ እንስሳት የምን ምሳሌ ናቸው?
4/ ዳንኤል በኖረበት ዘመን ታላቅ ኃይል የነበረው መንግሥት የትኛውነው?
5/ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ታላቅ ኃይል የነበረው መንግሥት የትኛው ነበር?
6/ የአረማውያን ዘመን የተጀመረው መቼ ነው? የሚያልቀውስ መቼ ነው?
7/ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የተጀመረው መቼ ነው?



8/ እስከ መቼ ይቆያል?
9/ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ስንት ክፍለ ጊዜያት አሉ?
10/ በራእይ 2 እና 3 የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የትኛዋ ናት?
11/ በራእይ 2 እና 3 ቢያንስ ሁለት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ጥቀስ።
12/ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ካሉት ሰባቱ ክፍለ ጊዜዎች ክርስቶስ እስኪመጣ የሚዘልቁት ስንቱ ናቸው?
13/ ዛሬ በዓለም ላይ የሚታዩት የትኞቹ ናቸው?
14/ (እውነት ውሸት) እስራኤል ዛሬ መንግሥት ነች።
15/ (እውነት ውሸት) ዛሬ እስራኤል የራስዋ ቤተ መቅደስ አላት።
16/ እስራኤል በምድርዋ ላይ ከተገኘች ምን ያህል ጊዜ ሆናት?
17/ የተጣመሩት የአውሮፓ አገሮች ስንት ናቸው።
18/ ይህ ሁኔታ ምን ያመለክታል?
19/ ዛሬ የዓለም ሃይማኖቶች በአንድነት በመጣመር ላይ ናቸው፤ ይህ ሁኔታ ምን ያመለክታል?
20/ የዳግም ምፅአት የመጀመሪያ ክፍል ምን ይባላል?
21/ መቼ እንደሚሆን የሚያውቅ ማን ነው?
22/ በዚያን ጊዜ ከጌታ ጋር ለመሆን የሚሄዱት እነማን ናቸው?
23/ ከክርስቶስ ጋር የሚገናኙት የት ነው?
24/ ከክርስቶስ ጋር አብረው የሚሆኑት ለምን ያህል ጊዜ ነው?
25/ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ወደ ኋላ የሚቀሩት ክርስቲያኖች ምን ዓይነቶቹ ናቸው?
26/ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቆሙት የትኞቹ አማኞች ናቸው?
27/ አክሊልና ሽልማት የሚቀበሉት እነማን ናቸው?
28/ ዳንኤል ስለ ሰባ ሳምንቶቹ ተናግሮአል፤ እያንዳንዱ ሳምንት ለንት ዓመት ነው?
29/ 69ኛው ሳምንት የተፈጸመው መቼ ነው?
30/ 70ኛው ሳምንት የሚፈጸመው መቼ ነው?
31/ የ70ኛው ሳምንት የመጀመሪያ ክፍል ምን ይባላል? ሁለተኛውስ ክፍል ምን ይባላል?
32/ በ70ኛው ሳምንት መጀመሪያ ክፍል ስንት ማኅተሞች ይፈታሉ?
33/ መለከቶቹ የሚነፉት መቼ ነው?
34/ ጽዋዎቹ ምን የሚይዙ ናቸው?
35/ ወደፊት የሚመጡት ሁለት ታላላቅ መሪዎች እነማን ናቸው?
36/ ከአይሁዳውያን ጋር ቃል ኪዳን የሚገባው የትኛው ነው?
37/ ይህን ቃል ኪዳን የሚጠብቀው ለምን ያህል ጊዜ ነው?
38/ የጥፋት ርኩሰት ምንድን ነው?

39/ አይሁዳውያን የጥፋት ርኩሰት በሚያዩበት ጊዜ ምን ማድረግ ይገባቸዋል?
40/ ሰዎች ይህን ንትሥ ምን ያደርጉታል?
41/ በሰዎች ሁሉ ላይ ምልክት የሚያደርገው ማን ነው?
42/ ታላቂቱ አመንዝራ ሴት የምን ምሳሌ ናት?
43/ ኋላ ምን ትሆናለች?
44/ ሰዎች ሰው የሚያመልኩትና እውነተኛ አማኞችን የሚያሳድዱት ለምን ያህል ጊዜ ነው?
45/ ከክርስቶስ የፍርድ ወንበር በኋላ በሰማይ ምን ይሆናል?
46/ ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ሰዎች እንዴት ያውቃሉ?
47/ ሕዝቦቹን ሲያሠቃዩበት የነበሩትን ሁለት ሰዎች ክርስቶስ ምን ያደርጋቸዋል?
48/ እነዚህን ሁለት መሪዎች የተከተሉትንስ ሰዎች ምን ያደርጋቸዋል?
49/ ሌሎችንስ ሰዎች ምን ያደርጋል?
50/ ሰይጣንንስ ምን ያደርገዋል?
51/ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ንጉሥ የሚሆነው ለምን ያህል ጊዜ ነው?
52/ ክርስቶስ በሚነግሥበት ጊዜ ምን ይሆናል? (አዎ) (አይደለም) ብለህ ጻፍ።
በዓለም ላይ ጦርነቶች ይሆናሉ?
በቂ ምግብ ይገኛል?
ሐሰተኛ ሃይማኖት ይኖራል?
እግዚአብሔር የሚመለክበት ቦታ ይኖራልን?
53/ ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ምን ይሆናል?
54/ በዚያን ጊዜ ምን ያደርጋል?
55/ እግዚአብሔር ሰይጣንን የት ይጥለዋል?
56/ በታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ጊዜ በክርስቶስ ፊት የሚቆሙት እነማን ናቸው?
57/ ወዴት ይጥላቸዋል?
58/ ሰማይና ምድር ምን ይሆናሉ?
59/ አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር ምን ያህል ይቆያሉ?
60/ ዘላለም ምን ያህል ጊዜ ነው?



## የጥያቄ መልሶች

1/ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።
2/ አራት።
3/ አራት መንግሥታት።
4/ ባቢሎን።
5/ ሮም።
6/ የአረማውያን ዘመን የተጀመረው እግዚአብሔር እስራኤልን ለባቢሎን ሥልጣን አሳልፎ በሰጠበት ጊዜ ነው፤ የሚቆየውም ክርስቶስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ነው።
7/ መንፈስ ቅዱስ በጴንጠቆስጤ ቀን በወረደ ጊዜ ነው።
8/ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እስከሚመጣ ድረስ ነው።
9/ ሰባት።
10/ ኤፌሶን፥ ሎዶቅያ።
11/ ሰምርኔስ፥ ጴርጋሞን፥ ትያጥሮን፥ ሰርዴስ፥ ፊላደልፍያ።
12/ አራት።
13/ አራቱም።
14/ እውነት።
15/ ውሸት።
16/ ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ።
17/ ዐሥር።
18/ ከብዙ ዘመናት በፊት አብዛኛዎቹን የአውሮፓ አገሮች ታስተዳድር ነበር፤ ጌታ ኢየሱስ በክብሩ ከመምጣቱ በፊት የአራተኛው መንግሥት ኀኸ ታላቅ ኃይል ይኖረዋል፤ ዐሥር ቀንዶች ያሉው እንስሳ የዚህ ኀኸ ምሳሌ ነው።
19/ በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ መኖራችንን ያመለክታል።
20/ መነጠቅ።
21/ እግዚአብሔር አብ።
22/ አማኞች ሁሉ።
23/ በደመና።
24/ ለዘላለም።
25/ እውነተኛ አማኞች ሳይሆኑ የክርስቶስ ነን የሚሉት ብቻ ናቸው።
26/ ሁሉም ናቸው።
27/ ጌታን በትጋትና በታማኝነት ያገለገሉ ብቻ ናቸው።
28/ ሰባት ዓመት።
29/ መሲሕ በተወለደ ጊዜ።
30/ ክርስቶስ ዓለምን ለመግዛት ሲመጣ።
31/ የምጥ ጣር መጀመሪያ ታላቁ መከራ።
32/ ሰባት።

33/ በ70ኛው ሳምንት ሁለተኛ ክፍል።
34/ የእግዚአብሔር ቁጣ።
35/ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ።
36/ አውሬው።
37/ ሦስት ዓመት ተኩል።
38/ አንድ ንጉሥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ጣዖት በማቆም አይሁዳውያን እግዚአብሔርን እንዳያገለግሉ ያደርጋል።
39/ በተቻላቸው መጠን መሸሽ አለባቸው።
40/ ያመልኩታል።
41/ ሁለተኛው አውሬ።
42/ ሐሰተኛ ሃይማኖት።
43/ እግዚአብሔር ይፈርድባታል፤ ዐሥሩም ነገሥታት ያጠፏታል።
44/ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ።
45/ የበጉ የሠርግ ግብዣ።
46/ በኃይልና በክብር ይመጣል፤ ሰዎች ሁሉ ያዩታል።
47/ ወደ እሳት ባሕር ይጥላቸዋል።
48/ ያጠፉቸዋል።
49/ ይፈርድባቸዋል፤ አማኞች ወደ መንግሥቱ ይገባሉ፤ ሌሎቹ ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ።
50/ ሰይጣን ለሺ ዓመት በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይታሠራል።
51/ ሺ ዓመት።
52/ ጦርነት አይኖርም፤ በቂ ምግብ ይኖራል፤ ሐሰተኛ ሃይማኖት አይኖርም፤ አዎ ኢየሩሳሌም።
53/ ይፈታል።
54/ ሰዎችን ሰብስቦ በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እንዲያነሡ ያደርጋል።
55/ በእሳት ባሕር።
56/ ክፉ ሰዎች ሁሉ።
57/ ወደ እሳት ባሕር።
58/ ይቃጠላሉ።
59/ ለዘላለም።
60/ መጨረሻ የለውም።



# ዳግም ምፅአት

(ተጨማሪ)

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የተለያየ ትምህርት እንሰማለን። «ትክክለኛው የቱ ነው?» ብለን መጨነቃችንም አይቀርም። መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መመሪያችን አድርገን ከተቀበልን ትምህርቱ ግራ የሚያጋባ አይደለም። የሚያስፈልገው ነገር እንደ ቤሪያ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናትና መመርመር ነው።

በቤሪያ ያሉት አይሁዳውያን በተሰሎንቄ ካሉት ይልቅ ቅን አመለካከት ያላቸው ስለነበሩ ቃሉን በታላቅ ደስታ ተቀበሉ፤ የቃሉንም እውነተኛነት ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር (ሐሥ. 17፥11)፤ ከሁሉ በፊት መልስ ማግኘት ያለብን "በእርግጥ ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል ወይ?" ለሚለው ጥያቄ ነው። አዎ! ኢየሱስ በክብርና በድል አድራጊነት ተመልሶ ይመጣል።

ይህንንም ካለ በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ ወጣ፤ ደመናም ከአይናቸው ሰወረው፤ እርሱ በሚሄድበት ጊዜ እነርሱ ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች አጠገባቸው ቆመው «እናንተ የገሊላ ሰዎች ለሰምን ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ቆማችኋል? ይህ ወደ ሰማይ ሲወጣ ያያችሁት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ ባያችሁት ዐይነት ተመልሶ ይመጣል» አሉአቸው (ሐሥ. 1፥9–11)። እንዲሁም ክርስቶስ የብዙዎችን ኃጢአት ለማስወገድ አንድ ጊዜ ተሠውቶአል፤ ዳግምም ኃጢአት ለመሸከም ሳይሆን እርሱን የሚጠባበቁትን ለማዳን ሁለተኛ ጊዜ ይገለጣል (ዕብ. 9፥28)፤ ከሃያ ሰባቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ ሦስቱ ስለ ኢየሱስ ተመልሶ መምጣት ያወሳሉ፤ የዚህ ዘመን መጨረሻ የሚሆነው በሃይድሮጅን ቦምብ ወይም በኑክሌር ቦምብ ፍንዳታ አይደለም።

የዚህ ዘመን ፍጻሜ የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ ክብሩ ተመልሶ ሲመጣ ነው፤ ምንም እንኳን ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን በውል የታወቀ ባይሆንም መምጣቱ ሲቃረብ የሚፈጸሙ ምልክቶች እንዳሉ እርሱ ራሱ ነግሮናል። ስለ መጨረሻዎቹ ቀኖች ወይም ስለ አሕዛብ ዘመን ፍጻሜ በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም በብዙ ቦታ ተገልጦአል። እንደገናም እንዲህ አለኝ «ዳንኤል ሆይ የዓለም መጨረሻ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ መጽሐፉን ዘግተህ አሽገው፤ የትንቢቱንም ቃል በምስጢር ያዝ፤ በዚያን ጊዜ ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይራወጣሉ፤ ምርምርና

ዕውቀትም ይበዛል» (ዳን. 12፥4)፤ እርሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ «ዳንኤል ሆይ! የዓለም መጨረሻ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ መጽሐፉ ተዘግቶ ስለታሸገ የትንቢቱ ቃል ሚስጥር ሆኖ ስለሚጠበቅ እንግዲህ አንተ ሂድ፣ ብዙዎች ነጥረውና ጠርተው በመውጣት እንከን የሌለባቸው ይሆናሉ።»

ዐመፀኞች ግን ምንም ስለማያስተውሉ በክፋት ላይ ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ፤ የማስተዋል ችሎታ የሚኖራቸው ጠቢባን ብቻ ናቸው (ዳን. 12፥9–10)፤ የአሕዛብ ዘመን ሲፈጸም መጽሐፉ ይከፈታል፤ ስለ ትንቢት ያለውም ዕውቀት ይበዛል። በተለይ ስለ ዳንኤል መጽሐፍና ስለ ሌሎችም የትንቢት መጻሕፍት የሚኖረን የዕውቀት አድማስ እየሰፋ ይሄዳል፤ ይህንንም የምንረዳው «ጠቢባን ብቻ ያስተውሉታል» ከሚለው አነጋገር ነው። ይህ ማለት በመንፈስ ቅዱስ አእምሮአቸው የበራ እንጂ የትምህርት ዕውቀት ያላቸውን አይደለም። ምክንያቱም ዐመፀኞችና ከሐዲዎች ሊረዱት አይችሉም፤ እነርሱንማ የዚህ ዓለም አምላክ የተባለው ዲያብሎስ ልባቸውን አሳውሮታል። ማኅተሙን ፈትተው ምስጢሩን ሊተረጉሙ የሚችሉ መንፈስ ቅዱስ አእምሮአቸውን ያበራላቸው መንፈሳውያን ሰዎች ብቻ ናቸው።

እነርሱ ወደ መጨረሻው ጊዜ እንደደረስን ይነግሩናል። የአሕዛብ ዘመን ፍጻሜ መቃረቡንም ያስታውቁናል። ከእነርሱም ብዙዎች በሰይፍ ይገደላሉ፤ ሌሎችም ተማርከው ወደየአገሩ ይወሰዳሉ፤ የአረማውያን ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአረማውያን የተረገጠች ትሆናለች (ሉቃ. 21፥24፤ 25–33)፤ ማሕተሙ ተፈትቶ በሚተረጎምበት ዘመን መገኘታችን ምንኛ የታደልን ነን።

ከጴንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ መንፈሳዊ መነቃቃቶች ተደርገዋል፤ ብዙ ዐይነት ምልክቶች ተሰጥተዋል። ነገር ግን ስለ ዳግም ምፅአት የተሰጠው ትምህርት በጣም አነስተኛ ነበር። ስለ ዳግም ምፅአት የተጻፉትም መጻሕፍት እጅግ አነስተኞች ነበሩ። ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ (Reformation) ጊዜ እንኳ እነ ሉተር፣ እነ ካልቪን፣ እነ ዝዊንግሊ ስለ ዳግም ምፅአት ይህን ያህል የጎላ ትምህርት አልሰጡም። ስለ ዳግም ምፅአት በስፋው መነገር ከተጀመረ ገና መቶ ዓመቱ ነው። ከዚያ ወዲህ ማኅተሙ መፈታት ተጀመረ፤ በሌሊትም «እነሆ ሙሽራው መጥቶአል የሚለው ድምጽ ተሰማ» ያም ጊዜ ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት የተገኘበት ነበር።



ከዚያን በፊት ሙሽራው ስለዘገየ ብልሆቹና ሞኞቹ ልጃገረዶች በአንድነት ለብዙ መቶ ዓመታት አንቀላፍተው ነበር። የተባረከው ተስፋችንም በጥርጣሬ ደመና ውስጥ ተሸፍኖ ነበር። አሁን ግን በመላው ዓለም የተባረከው ተስፋችን ከጨለማ ውስጥ ብቅ ማለት ጀምሮአል። ብልሆቹ ልጃገረዶችም ሙሽራውን ለመቀበል በመዘጋጀት መብራታቸውን እየኮስተሩ ነው። በማሰሮአቸውም በመብራታቸውም ዘይት ሞልተዋል። ጌታ የመምጫው ቀን እንደማይታወቅ ቢነገረንም ጥቂት ፍንጭ ሰጥቶናል። ስለዚህ የቤቱ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ አታውቅምና ተጠንቀቁ፤ ምናልባትም ወደ ማታ ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮኽ ወይም ጠዋት በማለዳ ይመጣ ይሆናል፤ በድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ትጉ (ማር. 13፥25–36)፤ በዚህ ጥቅስ መሠረት የጌታ መምጫ ጊዜ ሌሊት እንጂ ቀን እንደማይሆን እንገምታለን፤ በሌሊት ውስጥ ካሉት አራት ክፍለ ጊዜያት በአንደኛው ሊመጣ ይችላል፤ ስለዚህ ወገባችን የታጠቀ፣ መብራታችንም የበራ መሆን አለበት (ማር. 13፥38፤ ሉቃ. 12፥35፤ ማቴ. 24፥44፤ 25፥13)።

ዛሬ እኛ የምንገኘው በሌሊቱ አራተኛ ክፍል ላይ ነው፤ ከንጋት በፊት ያለችው የመጨረሻዋ ሰዓት ላይ ነን፤ በሌላ አነጋገር ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ነን፤ ይህች ሰዓት ደግሞ በጣም የጨለመች ነች። (The Darkest Hour Is Before Dawn) ከንጋት በፊት ያለው ጊዜ በጣም ጨለማ ነው።

በቅርቡም የተባረከው ተስፋችንና የንጋት ኮከብ የሆነው ኢየሱስ ይገለጣል (ራእ. 22፥16)፤ ከእርሱም ጋር ተገናኝተን በሠርጉ ግብዣ ላይ ለመታደም በመነጠቅ ወደ ሰማይ እንወጣለን። ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች ቅደም ተከተል ተራ ብናውቅ የጌታን መምጫ ምልክቶች በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን። ስለዚህ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮች ቅደም ተከተል ተራ ይህን ይመስላል፦

1 መነጠቅ ወይም መለወጥ የተባለው ሲሆን የመጀመሪያውንም ትንሣኤ ያጠቃልላል (1ተሰ. 4፥13–18)።

2 የታላቁ መከራ ዘመን (ዳን. 9፥27፤ ማቴ. 24፥21፤ ኤር. 30፥4–7)።

3 የክርስቶስ የፍርድ ወንበር (2ቆር. 5፥10)።

4 የአርማጌዶን ጦርነት (ራእ. 14፥20)።

5 የአሕዛብ ፍርድ (ማቴ. 25፥31–46፤ ራእ. 20፥11–15)።

6 በታላቁ መከራ ጊዜ የተገደሉ ቅዱሳን ትንሣኤ (ዳን. 12፥1-2)።

7 የከፉዎች መጣል ወይም መወገድ (ራእ. 19፥20፤ 20፥1-3)።

8 የሺሁ ዓመት የክርስቶስ መንግሥት (ኢሳ. 11፤ ራእ. 20)።

9 የመጨረሻው በመፅ (ራእ. 20)።

10 የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ (ራእ. 20፥11-15)።

11 የመሬት መቃጠል (2ጴጥ. 3፥7-10)።

12 አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር (ራእ. 21-22)።

13 የዳኑትና ያልዳኑት ዘላለማዊ ሁኔታ (ማቴ. 25፥41፤ ራእ. 2፥1-2)።

ስለዚህ፡-

1 በጸሎት በመትጋት እንጠባበቅ (ሉቃ. 21፥34-36)።

2 በመጠን በመኖር እንጠባበቅ (1ጴጥ. 4፥7፤ 5፥6)።

3 በቅድስና በመኖር እንጠባበቅ (ሮም 13፥11-14)።

4 በትዕግሥትና በተስፋ በመጽናት እንጠብቅ (2ጴጥ. 3፥10-14)።

## <u>የእምነት ሁኔታ በዳግም ምፅአት</u> (1ጢሞ. 1፥16-19)

ከምንጊዜውም ይልቅ ባስንበት ዘመን እምነትና መልካም ሕሊና ጠፍቶአል። ጌታ ሊመጣ ሲቀርብ እምነት ጨርሶ ይጠፋል (ሉቃ. 16፥8)፤ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን? በመጨረሻዎቹ ቀናት በእግዚአብሔር ማመን እጅግ ከባድ ከመሆኑ የተነሣ የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል የሚለው አነጋገር መቀበልና ጌታን እያገለገሉ በቅድስና መኖርን ሳይሆን ቃል በቃል «እግዚአብሔር» ወይም «ኢየሱስ» የሚለውን ስም የሚጠራ ይድናል ማለት ነው። ምክንያቱም ስሙን መጥራት ከባድ የሚሆንበት ጊዜ ስለሚመጣ፣ ለመዳን የሚፈልግ ዋጋ ከፍሎ ስሙን ይጠራል፤ ከታላቁ



መከራ በፊት አማኞች ይነጠቃሉ፤ ከንጥቀት በኋላ ወይም ቤተ ክርስቲያን ከምድር ላይ ከተወሰደች በኋላ በእምነት መኖር እጅግ ከባድ ይሆናል፤ በየዘመኑ መጨረሻ የጌታ መምጫ አሁን ይሆን? የሚል ጥያቄ ቀርቦአል። አሁንም የሚቀርበው ጥያቄ ይኸው ነው።

የፖለቲካ ሰዎች ሳይቀሩ የአርማጌዶን ጦርነት ሊነሣ ነው ይላሉ። በእነርሱ አባባል የመጨረሻው ጊዜ ተቃርቦአል ማለታቸው ነው። በእርግጥ የመጨረሻውን ቀን የሚያውቅ የለም (ማቴ. 24፥36)፤ ሆኖም ብዙ ምልክቶች ተሰጥቶአል።

1 ጌታ ራሱ የሰጠው ምልክት (ማቴ. 24፥7-14)።

2 ጳውሎስ የሰጠው ምልክት (2ተሰ. 2፥1-12፤ 2ጢሞ. 3፥1-5)።

3 ጴጥሮስ የሰጠው ምልክት (2ጴጥ. 3፥1-16)።

4 ዮሐንስ የሰጠው ምልክት (1ዮሐ. 2፥16፤ 2ዮሐ. 7-10)።

5 ይሁዳ የሰጠው ምልክት (3-16)።

6 ዳንኤል የሰጠው ምልክት (ዳን. 12፥4)፤ ይህ ጥቅስ ሰዎች የሁከትና የጭንቀት ሕይወት እንደሚኖራቸው ያመለክታል።

6.1 ለውጥ ይበዛል፤ በየጊዜው ለውጥ ይካሄዳል፤ የኑሮ፣ የቤተሰብ፣ የኅብረተሰብ፣ የፖለቲካ፣ የሳይንስ፣ የሌሎች ነገሮች ለውጥ ይጣደፋል።

6.2 አለመግባባት ይበዛል፤ ሰውና ሰው አብሮ መኖር ያቅተዋል፤ አንዱ ሌላውን መረዳት አይችልም፤ ሰው ሁሉ ደሴት ይሆናል፤ ግላዊነት ይበዛል። በቤት፣ በጎረቤት፣ በመሥሪያ ቤት፣ በገበያ፣ በመንገድ አለመግባባት ይበዛል፤ ጦርነት ይጧጧፋል።

6.3 ፍቅረ ነዋይ (Materialism)ይበዛል፤ እንደነከሌ እንኑር የሚለው ሃሳብ በልጦ ቁሳቁስን እንድንወድ ያደርገናል፤ ባለን አንረካም፤ በቃኝ የሚል የለም (1ጢሞ. 6፥10፤ ዕብ. 13፥5)

6.4 ፍርሃትና ጭንቀት ይበዛል፤ ዓለም እንደሚጨነቀው እኛም እንጨነቅ ይሆናል። ነገር ግን እኛ ስለ ወሬትዋ ስለ ዘመናት ከመጨነቅ ይልቅ፣

1. በቅድስና እንኑር (ሮሜ 13፥11–14፤ 2ጴጥ. 3፥13–14፤ 1ተሰ. 5፥1–6፤ 4፥3)።
2. በትጋት እናገልግል (ሮሜ 12፥11–12፤ ገላ. 6፥9–10፤ 2ጴጥ. 3፥14)።
3. እየተጠባበቅን እንጸልይ (ሉቃ. 21፥36)።
4. በትዕግሥት እንጽና (ያዕ. 5፥7–8)።

## ወደ ፊት ስለሚሆኑት ነገሮች

አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ አሳብ ስላላቸውና ስለማይስማሙ ስለ እነርሱ ማንሣት ትቶ ስለተፈጸሙት ትንቢቶች ብቻ ማስተማር በቂ ነው የሚሉ አሉ። እንደ እነርሱ አባባል ቢሆን ጳውሎስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቃሚ የሆኑት አንዳንዶቹ ናቸው፤ ስለሆነም ትንቢትን መረዳት ስለማትችሉና የተለያየ አሳብም ስለሚኖራችሁ ስለትንቢት ጨርሶ ማንሣት የለባችሁም ብሎ በጻፈልን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን ጳውሎስ እንዲህ ብሎ አልጻፈም፤ እርሱ የጻፈው ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ለትምህርታችን ጠቃሚ ናቸው በማለት ነው (2ጢሞ. 3፥16)፤ እግዚአብሔር ስለ ትንቢቶች እንዳንማር ቢፈልግ ኖሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲሰፍሩ ባልፈቀደ ነበር። በእርግጥ ከትንቢቶች አብዛኞዎቹ ተፈጽመዋል፤ ጥቂቶቹ ደግሞ ወደፊት የሚፈጸሙ ናቸው።

የዓለም ታሪክ ቅርጽ የሚገኘው በትንቢት ነው፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሦስተኛው ትንቢት ነው። የቀረውም ሁለት ሦስተኛው አጅ ቢሆን አብዛኛው የሚናገረው ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ነው። ክርስቶስ እንደሚወለድ ከመወለዱ 700 ዓመት በፊት ተነግሮ ነበር፤ ተፈጽሞአል። በመንፈስ ቅዱስ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እንደሚወርድ ተነግሮ ነበር። ያም በጴንጠቆስጤ ቀን ተፈጽሞአል። ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ከሰማይ እንደሚመጣ ተነግሮአል። ያም በእግዚአብሔር ጊዜ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። በእርግጥ ማንም ሰው በራሱ ሥልጣን ስለዳግም ምፅአት እንዲህ ይሆናል ብሎ መናገር አይችልም።

ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን አንተ ማን ነህ? መሲሕ ነህን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ቢል መስለስት «አንተ እንዳልከው ነው፤ ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ታዩታላችሁ፤ እንዲሁም በሰማይ ደመና ሆኖ ሲመጣ ታያላችሁ»፤ ተመልሼ እመጣለሁ በማለቱም እንደ መናፍቅ ቆጥረው ገደሉት። አዎ! መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መወለዱ፥ መከራ ስለ መቀበሉ፥ ስለ



መሞቱ፥ ስለ መነሣቱ፥ ስለ ማረጉ ብቻ ሳይሆን ተመልሶ ስለ መምጣቱም ያስተምረናል። እንዲያውም ተመልሶ ስለ መምጣቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 300 ጊዜ ተጠቅሶአል። ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ስለዳግም ምፅአት በሰፊው የማታስተምረው ስለምንድነው? ቤተ ክርስቲያንን ሊያነቃቃ የሚችል ከዚህ የበለጠ ትምህርት ስለሌለ ሰይጣን ይህ ትምህርት እንዳይሰጥ ይከለክላል። የጌታን መምጣት በሚጠባበቅ ክርስቲያን ላይ ዓለም፥ ሥጋ፥ ሰይጣን ምንም ዐይነት ተጽእኖ ቢያደርሱበትም በድል አድራጊነት ይኖራል።

አንዳንድ ሰዎች የትንቢት ነገር ለካህናትና ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች እንጂ ለተራው ምዕመን አይደለም ይላሉ። እንደገናም ሌሎች ሰዎች የትንቢት ነገር መንፈሳዊ ምሳሌ የሚሆን እንጂ ቃል በቃል የሚወሰድ አይደለም ይላሉ። ጴጥሮስ ግን ትንቢት ከሰው ፈቃድ ከቶ አልመጣም፥ ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው ይለናል (2ጴጥ. 1፥21)፤ ጌታችን ተመልሶ እንደሚመጣ የተናገሩትም እነዚያ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው። ከእነርሱ አንዱ ዳንኤል የብረቱን፥ የነሐሱን፥ የሸክላውን፥ የብሩንና የወርቁን፥ ምስል ስለ ሰባበረችው ድንጋይ ተናግሮአል። ያች ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆና ምድርን የምትሞላው ጌታ ተመልሶ ሲመጣ ነው። መወለዱን ለድንግል ማርያም ያበሠረ መልአክ ነው። በተወሰደም ጊዜ በቤተልሔም መላእክት ዘመሩለት፤ ዳግም ስለ መምጣቱ የተናገሩ መላእክት ናቸው (ሐሥ 1፥9–11)፤ አንዳንድ ሰዎች ጨርሶ ስለዳግም ምጽአት መስማት አይፈልጉም።

ሌሎች ደግሞ እጅግ ከመምጠቃቸው የተነሣ የሚመጣበትን ቀን እስከ መናገር ይደርሳሉ። መምጣቱ የተረጋገጠ ቢሆንም የሚመጣበትን ቀን ማንም ሊያውቅ አይችልም (ማቴ. 24፥27፥36፤ ሐሥ. 1፥7)፤ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አልገለጠልንም፤ ነገር ግን የተገለጠውን እንኳ ከተቀበልን ይበቃናል (ዘዳ. 29፥29)።

ስለተሰወሩት ነገሮች መጨነቅ ትተን ስለተገለጡት ነገሮች እንማር፤ ያልተፈፀሙ ትንቢቶችን በተፈፀሙት ትንቢቶች መተርጎም እንችላለን።

የጌታ መወለድ ተነግሮ ነበር ተፈጽሞአል፤ ዳግም ምፅአቱም ተነግሯል፤ ስለዚህ ይፈጸማል፤ በአይሁዳውያን ላይ መርገሞች እንደሚደርሱ ተነግሮ ነበር፥ ተፈጽሞአል። በረከቶችም እንደሚደርሱ ተነግሮአል እርሉም የሚፈጸምበት ጊዜ አለ፤ የእስራኤላውያን መበተን ተፈጽሞአል፤ መሰብሰባቸውም ተፈጽሞአል፤ ጽዮን እንደምትወድቅ

ተነግርአል፤ ዳግመኛም እንደምትታደስ ተነግርአል፤ እስራኤል ዳግመኛም እንደምትታደስ ተነግርአል፤ እስራኤል እንደምትጣል ተነግርአል፤ ተመልሳ እንደምትቋቋም ተነግርአል፤ ከመጀመርያ መምጣቱ ጋር የተያያዙ ነገሮች እንደተፈጸሙ ሁሉ ከዳግም ምፅአቱ ጋር የተያያዙትን ነገሮችም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

የብሉይ ኪዳን ትንቢት ሁሉ በአዲስ ኪዳን የተደገፈ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

## የዳግም ምፅአት ምን በመባል ይታወቃል

1 የጌታ ቀን (1ተሰ. 5፥2–8)።

2 የክርስቶስ ቀን (1ቆር. 5፥5)።

3 የእግዚአብሔር ቀን (2ጴጥ. 3፥12)።

4 ያ ቀን (2ተሰ. 1፥10)።

5 የመጨረሻ ቀን (ዮሐ. 12፥48)።

## ጌታ ለምን ይመጣል?

1 ቃሉን ለማጽናት (ዮሐ. 14፥3)።

2 ሙታንን ለማስነሣት (1ተሰ. 4፥13–18)።

3 ሞትን ለመደምሰስ (1ቆር. 15፥25–26)።

4 የተዋጁትን ለመሰብሰብ (ማቴ. 24፥31)።

5 በዓለም ለመፍረድ (ማቴ. 25፥32–46)።

6 ምዕመናንን ለማክበር (ፊል. 3፥20–21)።

7 የእግዚአብሔርን ሰዎች ለመሸለም (ማቴ. 16፥27)።



## የመምጣቱ ጊዜ

1 በሰዎች የታወቀ አይደለም (ማቴ. 24፥27፥36)።

2 ወንጌል ከተዳረሰ በኋላ (ማቴ. 24፥14)።

3 የክርስቶስ ተቃዋሚ ከተገለጠ በኋላ (2ተሰ. 2፥3)።

4 የመጨረሻው መለከት ከተነፋ በኋላ (1ቆር. 15፥61–52)።

6 ቀናቱ የኖህን ቀናት ሲመስሉ (ማቴ. 24፥37–39)።

## የአመጣጡ ሁኔታ

1 በደመና ሆኖ (ማቴ. 24፥30)።

2 በሚንበለበል እሳት (2ተሰ. 1፥7–8)።

3 ከመላእክቱ ጋር (ማቴ. 25፥31)።

4 እንደሌባ በድንገት (1ተሰ. 5፥2–3)።

5 በክብር ይመጣል (ማቴ. 25፥31)።

## ምዕመናን ምን ማድረግ አለባቸው

1 መጠባበቅ (1ቆር. 1፥7)።

2 መናፈቅ (ቲቶ 2፥14)።

3 መዘጋጀት (ማቴ. 24፥42–61)።

4 መውደድ (2ጢሞ. 4፥6)።

5 ተግቶ መሥራት (ሉቃ. 19፥13–18)።

6 ተግቶ መጸለይ (ራእ. 22፥20)።

## የዘመን መጨረሻ ምልክቶች

1 ዘባቾች ይበዛሉ (2ጴጥ. 3፥3–4)።

2 ክሕደትና ወደ ኋላ ማፈግፈግ ይበዛል (2ተሰ. 2፥3)።

3 ሐሰተኞች መምህራን ይበዛሉ (2ጴጥ. 2፥1–2)፤ ሰዎች ከእውነት እየራቁ በመሄድ ጆሮ የሚያሳክክ ትምህርት የሚሰጧአቸውን ይፈልጋሉ (2ጢሞ. 4፥1)።

4 የመናፍስት ትምህርትና የሰይጣን አምልኮ ይበዛል (1ጢሞ. 4፥1)።

5 አስጨናቂ ዘመን ይሆናል (2ጢሞ. 3፥1–5)።

8 የሀብት ክምችት ይበዛል (ያዕ. 5፥1–8)።

7 ለብ ያለ የክርስትና ሕይወት ይታያል (2ጢሞ. 3፥5፤ ራእ. 3፥14–22)።

8 የበለስ ዛፍ ምልክት (ማቴ. 24፥1–3፤ ሉቃ. 21፥24)።

## የአሕዛብ ዘመን ፍጻሜ

9 የሕዝቦች ጭንቀት (ሉቃ. 21፥24–27፤ ኤፌ. 8፥11–12፤ ሐጌ 2፥6–7)።

10 የኖኅ ዘመን ይመስላል (ሉቃ. 17፥28–30)።

ሴሰኝነት፥ ብኩንነት፥ ጥድፊያ፥ ለእግዚአብሔር ጊዜ አለማግኘት ይሆናል፤ በምድር ቤት ስለመሥራት እንጂ በሰማይ ቤት ስለመስራት የሚያስብ የለም።

ልጆቻቸው በምድር ታዋቂዎች እንዲሆኑ እንጂ ከጌታ ጋር እንዲገናኙ የሚጨነቅ ወላጅ የለም።

11 የክርስቶስ ተቃዋሚ ይገለጣል (ዮሐ. 2፥18፤ 4፥3፤ 2ዮሐ. 7፤ 2ተሰ. 2)።



12 ወንጌል በስፋት ይሰበካል (ማቴ. 24፥14)።

13 ፍቅር ይቀዘቅዛል (ማቴ. 24፥12)።

14 የቤተ መቅደስ መታደስ፦

ሀ ሰሎሞን ያሠራው (2ሳሙ. 7፥13፤ 1ነገ. 5፥5–8፤ 8፥13፤ 2ነገ. 12፥5፤ 22፥5፤ 24፥13፤ 25፥8)።

ለ ዕዝራ ያሠራው (ዕዝ. 2፥68፤ 4፥1–8፤ ሐጌ 1፥2፤ ዮሐ. 2፥20፤ ሐ.ሥ. 3፥10)።

ሐ ሄሮድስ ያሠራው (ማቴ. 24፥1፤ ማር. 11፥15፤ ሉቃ. 2፥27፤ 21፥5፤ ዮሐ. 2፥20፤ ሐ.ሥ. 3፥20)።

መ በመጨረሻ ሊሠራ ያለው (ሕዝ. 42፥15–20፤ 47፥8–12፤ 48፥35፤ ራእ. 22፥1–2፤ ዘካ. 14፥8)።

## ማ ራ ና ታ !